## *መቅድም፤*

ዘለዓለማዊ፡ ልዑል፡ እግዚአብሔር፥ የሕግና፡ የሥርዐት፡ ባለቤት፡ በመኾኑ፥ በአርኣያው፡ የፈጠረው፡ የሰው፡ ዘር፡ ኹሉ፡ በሕግና፡ በሥርዐት፡ እንዲያመልኩት፥ እንዲገዙለት፡ ይሻል።

አዳምንና፡ ሔዋንን፡ ፈጥሮ፥ በልጅነት፡ አክብሮ፥ በገነት፡ ሲያኖራቸው፥ ሕግን፡ ሰጥቷቸው፡ ሳለ፥ ዲያብሎስ፡ በተንኰል፡ ሕጉን፡ እንዲተላለፉ፥ እንዲያፈርሱ፡ በማድረጉ፥ አዳም፡ ለዘላለም፡ ሕያው፡ ኾኖ፡ እንዳይኖር፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ከዔዴን፡ ገነት፡ አስወጣው። ወደ፡ ሕይወት፡ ዛፍ፡ የሚወስደውን፡ መንገድ፡ ለመጠበቅ፥ ኪሩቤልን፡ የነበልባል፡ ሰይፍን፡ አሲዞ፡ ከዔዴን፡ ገነት፡ ምሥራቅ፡ አስቀመጠ። ከሥርዐት፡ ውጭ፥ ሕግ፡ አፍራሽ፡ የኾነው፡ ሰው፥ በጥፋቱ፡ (በኀጢአቱ)፡ ተፈርዶበት፥ ከገነት፡ ተባረረ። *ዘፍ.፥ ፫፥ ፳፬*

*'በዚህ፡ ምክንያት፥ ኀጢአት፡ ባንድ፡ ሰው፡ ወደ፡ ዓለም፡ ገባ፤ በኀጢአትም፡ ሞት። እንደዚሁም፡ ኹሉ፥ ኀጢአትን፡ ስላደረጉ፥ ሞት፡ ለሰው፡ ኹሉ፡ ደረሰ።' ሮሜ.፥ ፭፥ ፲፪*

የድኅነት፡ ምላሹም፤ *'ኹሉ፡ በአዳም፡ እንደሚሞቱ፥ እንዲሁ፡ ኹሉ፡ በክርስቶስ፡ ደግሞ፡ ሕያዋን፡ ይኾናሉ።' ፩፡ ቆሮ.፡ ፲፭፥ ፳፪* እንዳለ፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ።

በነቢያት፡ እያናገረ፤ *'እንሆ፥ ከእስራኤል፡ ቤትና፡ ከይሁዳ፡ ቤት፡ ጋራ፡ ቃል፡ ኪዳን፡ የምገባበት፡ ወራት፡ ይመጣል።' ኤር.፥ ፴፩፥ ፴፩፤ ዕብ.፥ ፰፥ ፰* ባለው፡ መሠረት፥ ባጪር፡ ቁመት፥ በጠባብ፡ ደረት፡ ተወስኖ፥ እምቅድመ፡ ዓለም፡ (ከዓለም፡ በፊት)፡ በመለኮት፡ የአብ፡ የባሕርይ፡ ልጁ፡ (ወልደ፡ አብ)፥ ድኅረ፡ ዓለም፡ (ከዓለም፡ በኋላ)፡ በተዋሕዶ፡ የከበረ፥ በሥጋ፡ የማርያም፡ ልጅ፡ (ወልደ፡ ማርያም)፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወደዚህ፡ ዓለም፡ በመምጣቱ፥ ዕርቅ፥ ሰላም፥ ድኅነት፥ ካሳ፡ ተደረገ። የአበው፡ ተስፋ፥ የነቢያት፡ ትንቢትና፡ ምሳሌው፡ ተፈጸመ። እረኞችና፡ (ኖሎትና)፡ መላእክት፡ ተባብረው፡ አመሰገኑ። *ሉቃ.፥ ፪፥ ፲*

በደብረ፡ ሲና፡ (በሲና፡ ተራራ)፡ ላይም፡ ተገልጾ፥ ሕገ፡ ኦሪትን፥ ሥርዐተ፡ ኦሪትን፡ የሠራ፡ ፈጣሪ፥ በኋለኛው፡ ዘመን፥ ቃል፡ እግዚአብሔር፡ ወልድ፥ አለመቀላቀል፥ አለመጠፋፋት፥ በተዋሕዶ፡ ከቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ተወልዶ፥ ሕገ፡ ወንጌልን፡ አስተምሮ፥ ሥርዐተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንን፡ መሠረተ። *ማቴ.፥ ፭፥ ፳፩–፵፰፤ ፯፥ ፩–፲፰*

በክርስቶስ፡ ደም፡ የተመሠረተችውም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ያምልኮ፡ መግለጫዎቿ፤

- ባምስቱ፡ **አዕማደ፡ ምስጢር**፡ (መሠረተ፡ እምነት)፡ እውነት፤

  **ምስጢረ፡ ሥላሴ፤**

  **ምስጢረ፡ ሥጋዌ፤**

  **ምስጢረ፡ ጥምቀት፤**

  **ምስጢረ፡ ቍርባን፤**

**ምስጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፤**

ሲኾኑ ፥

- በ፯ቱ ፡ **ሥርዐታተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን** ፡ (ሀብታት) ፤

**ጥምቀት ፤**

**ሜሮን ፤**

**ቍርባን ፤**

**ክህነት ፤**

**ተክሊል ፤**

**ንስሓ ፤**

**ቀንዲል ፤**

ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተመሠረተች ።

አዕማድና ፡ ሀብታት ፡ የሚለያዩትም ፥ አዕማድ ፡ ትምህርተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሲያሳዩን ፥ ሀብታት ፡ ግን ፥ በያንዳንዱ ፡ ሀብት ፡ አማካይነት ፡ ለሰው ፡ የተሰጠው ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ *መንፈስ ፡ ቅዱስ* ፡ ነው ።

ከ፯ቱ ፡ ሀብታት ፡ አንዱ ፥ **ምስጢረ ፡ ቍርባን** ፡ ወይም ፡ **መሥዋዕት** ፡ ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ስም ፡ ይጠራል ። ሰው ፥ ካምላኩ ፡ ይቅርታንና ፡ ምሕረትን ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚቀርበው ፡ መባእ ፡ ቍርባን ፥ በኦሪቱ ፥ ደም ፡ የሚያስፈስስ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ **መሥዋዕት** ፤ በእኽል ፡ ውሃ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ **ቍርባን** ፡ ይባላል ።

ክርስቲያኖች ፡ ግን ፥ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚያቀርቡት ፥ *መሥዋዕትም* ፡ ቍርባንም ፡ ነው ። በኅብስትና ፡ በወይን ፡ አምሳል ፡ ስለሚቀርብ ፥ *ቍርባን* ፡ ይባላል ።

አማናዊ ፡ (እውነተኛ) ፡ *ሥጋና ፡ ደመ ፡ መለኮት* ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ደግሞ ፥ **መሥዋዕት** ፡ ይባላል ። *፩ ፡ ቆሮ. ፥ ፲፩ ፥ ፲*

የተመሠረተውም ፥ ኀጢአትን ፡ ለማስተስረይ ፥ ሰውን ፡ ከፈጣሪው ፡ ለማስታረቅና ፥ ዘላለማዊን ፡ ሕይወት ፡ ለመስጠት ፡ ነው ። *ዮሐ. ፥ ፮ ፡ ፮ ፥ ፵፯–ፍ. ፡ ም. ፤ ማቴ. ፥ ፳፮ ፥ ፳፯ ፤ ዕብ. ፥ ፱ ፥ ፳፪*

ይህም ፡ ሲባል ፥ በዝግጅት ፥ በንስሓ ፤ ማለትም ፥ ወደ ፡ ሰርግ ፡ የተጠራ ፡ ኹሉ ፥ የሥጋ ፡ ልብሱንና ፡ መላ ፡ ሰውነቱን ፡ አጽድቶ ፡ እንደሚኼድ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰርግ ፡ ጥሪ ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፥ የነፍሱን ፡ እድፍ ፡ በንስሓ ፡ ሳሙና ፡ ማጽዳት ፡ አለበት ። ያለዕውቀት ፥ በንቀት ፥ እንደ ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ የሚቀበሉት ፡ አይደለም ። ራስን ፡ መመርመር ፡ ያሻዋል ። ስሕተት ፡ በተፈጸመ ፡ ቊጥር ፡ ኑዛዜ ፡ ያሻዋል ። *፩ ፡ ቆሮ. ፥ ፲፩ ፥ ፳፰* በጌታ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ኀጢአቴ ፡ ይሰረያል ፡ ብሎ ፡ አፍ ፡ ከልብ ፡ ማመን ፥ ልብንም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ማድረግ ።

ይህም ፡ የቍርባን ፡ ሥርዐት ፥ ቅዳሴ ፡ (ምስጋና) ፥ ጸሎት ፥ ዝማሬ ፥ ምልጃ ፡ ያሻዋል ። ቡራኬያት ፥ የረስዮ ፡ እማሬያት ፥ ዑደት ፡ ይፈጸማል ። አስፈጻሚውም ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡

ያለው፡ ነው። ቡራኬው፥ በውስጥ፥ ሥጋውን፡ ደሙን፡ ፳፩፡ ጊዜ፥ ሕዝቡን፡ ፳፩፡ ጊዜ፥ ፵፪፡ ጊዜ፡ ይባርካል።

የቅዳሴ፥ የመባረክ፥ የእማሬ፥ የጸሎት፥ የምልጃ፡ ሥርዐት፡ በሦስት፡ ሲከፈል፤

- የመዠመሪያው፡ የካህኑ፡ (የገባሬ፡ ሠናዩ፡ ቄስ)፡ አገልግሎት፡ በሚሰጥባቸው፡ በአልባሳትና፡ በንዋያተ፡ ቅድሳት፡ ላይ፡ የሚጸለይ፡ የውስጥ፡ ጸሎት፡ *'ሚመጠን፡ ግርምት'*፡ ብሎ፥ የቃጭል፡ ድምፅ፡ እስከሚሰማበት፡ ድረስ፥ አንዱ፡ የቡራኬና፡ የእማሬ፥ የጸሎት፥ የምልጃ፡ ክፍል፡ ነው፤
- ወንጌል፡ ተነቦ፥ ሕዝቡ፡ ወንጌል፡ ሲሳለሙ፥ *'ነአምን፡ በቃለ፡ ወንጌልከ፡ ቅዱስ'*፡ ብለው፥ የቃጭል፡ ድምፅ፡ እስከሚሰማበት፡ እስከ፡ *'ፃኡ፡ ንኡሰ፡ ክርስቲያን'*፡ ኹለተኛ፡ የቡራኬና፡ የጸሎት፡ ክፍል፡ ነው፤
- ከዚያ፡ በኋላ፡ ሦስተኛው፡ ክፍል፥ *'ጸልዩ፡ በእንተ፡ ሰላም'*፡ ከተባለና፥ ቀሳውስት፡ ከቀሳውስት፥ ዲያቆናት፡ ከዲያቆናት፥ ሕዝቡ፡ ከሕዝቡ፡ ጋራ፡ እጅ፡ ከተነሣሡ፡ በኋላ፥ የጽርስፎራው፡ (የቍርባኑ)፡ የምስጋና፥ የቡራኬና፡ የጸሎት፡ ሥርዐት፡ ይቀጥላል፤ ይህም፡ በሐዋርያት፡ እግር፡ የተተኩት፡ ቅዱሳን፡ አባቶች፡ ያዘጋጇቸው፡ ፲፬፡ የቍርባን፥ የምስጋና፡ ሥርዐት፡ ሲኖሩት፥ አንዱ፥ ለዕለቱ፡ ተስማሚው፡ ተመርጦ፡ ይቀደሳል።

ይህም፡ ሥርዐት፤ **ይ፡ ካ**፡ (**ይበል፡ ካህን**)፥ **ይ፡ ዲ**፡ (**ይበል፡ ዲያቆን**)፥ **ይ፡ ሕ**፡ (**ይበሉ፡ ሕዝብ**)፥ በሦስት፡ ተከፍሎ፥ ኹሉም፡ በየተራው፡ እየተቀባበለ፥ ወደ፡ ፈጣሪው፡ የሚያቀርበው፡ የኅብረት፥ ያንድነት፡ ጸሎት፥ ያንድ፡ የክርስቶስን፡ ሥጋና፡ ደም፡ የሚቀበሉበት፡ ሥርዐት፡ ነው። የሚቀበሉትም፡ ከገባሬ፡ ሠናዩ፡ ቀዳሽ፡ ካህን፡ ዠምሮ፡ ራሱ፡ ተቀብሎ፥ በተዋረድ፡ ኹሉንም፡ ያቀብላል።

ለዚህ፡ የምእመናን፡ የኅብረት፡ ጸሎት፥ ያውሮጳ፡ ሊቀ፡ ጳጳስ፡ የነበሩት፡ ብፁዕ፡ አቡነ፡ ዮሐንስ፥ በነበረባቸው፡ ታላቅ፡ የክህነት፡ ኀላፊነት፥ ያለረፍት፥ በትጋት፥ ምእመናን፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ እንዲገቡ፥ በንስሓ፡ እንዲመለሱ፡ ከሚያደርጉት፡ የጠባቂነት፥ የማስተማር፡ ሥራ፡ በላይ፥ የቅዳሴ፡ ተሰጥዎ፡ መቀበያ፡ መጻሕፍት፡ በማዘጋጀት፥ እንሆ፥ ላ፪ኛ፡ ጊዜ፡ ረቂቁን፡ አዘጋጅተው፡ ወደ፡ ኅትመት፡ በመኼጃው፡ ሰዓት፥ በዕረፍተ፡ ሞት፡ ተገተዋል። ኾኖም፥ አበ፡ ብዙኃን፡ (የብዙዎች፡ አባት)፥ ምእመናንን፡ ለመንግሥተ፡ ሰማያት፡ ባለቤትነት፥ ለንስሐና፡ ለቅዱስ፡ ቍርባን፥ ለክርስትና፥ ለተክሊል፥ ለሜሮን፥ ለቀንዲል፥ ለክህነት፡ ያበቁ፡ አባት፡ ስለ፡ ነበሩ፥ ይህች፡ የቅዳሴ፡ ተሰጥዎ፡ ለመታሰቢያ፡ ስትዘጋጅ፤ ፈጣሪ፥ ነፍሰ፡ አቡነ፡ ዮሐንስን፡ በተድላ፡ ገነት፡ ያኖርልን፡ ዘንድ፡ ፈቃዱን፡ እየለመንን፡ ነው፨

**በኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋሕዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፥**
**የለንደን፡ ደብረ፡ ጽዮን፡ ቅድስት፡ ማርያም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን።**
**ሚያዝያ፡ ፫፡ ቀን፥ ፲፱፻፺፯፡ ዓ.፡ ም.።**

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፨

፩ ፤ ይበል ፡ ካህን ፤ ሚመጠን ፡ ግርምት ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፤ ወዕጹብት ፡ ዛቲ ፡ ሰዓት ፤ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይወርድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እመልዕልተ ፡ ሰማያት ፥ ወይጼልሎ ፡ ለዝንቱ ፡ መሥዋዕት ፥ ወይቄድሶ ።

በጽሙና ፡ ወበፍርሀት ፡ ቁሙ ፡ ወጸልዩ ፡ ከመ ፡ ሰላሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሃሉ ፡ ምስሌየ ፡ ወምስለ ፡ ኵልክሙ ።

፪ ፤ ይበሉ ፡ ሕዝብ ፤ አሜን ።

### ዘዘወትር ፨

፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ እምነ ፡ በሓ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ስርጉት ፡ አረፋቲሃ ፥ ወሥዕልት ፡ በዕንቍ ፡ ጳዝዮን ፤ እምነ ፡ በሓ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

### ዘቀደሚት ፨

፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ መስቀል ፡ አብርሀ ፤ በከዋክብት ፡ አሰርገወ ፡ ሰማየ ፤ እምኵሉሰ ፡ ፀሓየ ፡ አርአየ ፤ መስቀል ፡ አብርሀ ፤ በከዋክብት ፡ አሰርገወ ፡ ሰማየ ።

### ዘሰንበት ፨

፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ለጽድቅ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፥ ወዘያከብር ፡ ሰንበተ ። ኢይበል ፡ ፌላሲ ፡ ዘገብአ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈልጠኒኑ ፡ እምሕዝቡ ። ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ለጽድቅ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ ወዘያከብር ፡ ሰንበተ ።

፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (በአሐዱ) ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ እምእመናን ፡ ዘቦአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ወኢሰምዐ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቅዱሳተ ፡ ወኢተዐገሠ ፡ እስከ ፡ ይፌጽሙ ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ወኢተመጠወ ፡ እምቍርባን ፡ ይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ እስመ ፡ አማሰነ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፥ ወአስተሐቀረ ፡ ቁመተ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ ሰማያዊ ፥ ንጉሠ ፡ ሥጋ ፡ ወመንፈስ ፥ ከመዝ ፡ መሀሩነ ፡ ሐዋርያት ፡ በአብጥሊሶሙ ።

## ምዕራፍ፡ ፩ ፨

፩፤ ይበል፡ ካህን፤ ይህ ች፡ ቀን፡ ምን፡ ያኽል፡ የምታስፈራ፡ ናት፤ ይህ ችስ፡ ሰዓት፡ ምን፡ ያኽል፡ የምታስጨንቅ፡ ናት፤ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ የሚወርድባት፤ ይህን፡ መሥዋዕቱን፡ የሚሰውርባትና፡ የሚያከብርባት።

በጽሙናና፡ በመፍራት፡ ቁሙ፤ የእግዚአብሔር፡ ሰላም፡ ከኔና፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ይኾን፡ ዘንድ፡ ጸልዩ።

፪፤ ይበሉ፡ ሕዝብ፤ አሜን።

### የዘወትር ፨

፫፤ ይ፡ ሕ፤ ሰላም፡ ላንቺ፡ ይኹን፡ እናታችን፡ ቅድስት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፤ ግድግዳዎ ቿ፡ ያጌጡ፥ በብሩሕ፡ ዕንቊ፡ የተሸለሙ፡ ናቸው። ሰላም፡ ላንቺ፡ ይኹን፡ እናታችን፡ ቅድስት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን።

### የቅዳሜ ፨

፬፤ ይ፡ ሕ፤ መስቀል፡ አበራ፤ ሰማይን፡ በኮከቦች፡ አስጌጠ፤ ከኹሉም፡ ፀሓይን፡ አሳየ፤ መስቀል፡ አበራ፤ ሰማይን፡ በኮከቦች፡ አስጌጠ።

### የእሑድ ፨

፭፤ ይ፡ ሕ፤ በጎን፡ የሚያደርግ፥ ሰንበትንም፡ የሚያከብር፡ ኹሉ፡ ጻድቅ፡ ነው። ወደ፡ እግዚአብሔር፡ አምልኮ፡ የገባ፡ መጻተኛ፤ *'ከሕዝቡ፡ ኹሉ፡ ይለየኛ፡ ይኾን?'* አይበል፤ በጎን፡ ያደረገ፥ ሰንበትንም፡ የሚያከብር፡ ጻድቅ፡ ነው።

፮፤ ይ፡ ሕ፤ (በአንድ) ሃሌ፡ ሉያ፤ በቅዳሴ፡ ጊዜ፡ ከምእመናን፡ ወገን፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ የገባ፡ ሰው፡ ቢኖር፥ ቅዱሳት፡ መጻሕፍትን፡ ሰምቶ፡ የቅዳሴውን፡ ጸሎት፡ እስኪጨርሱ፡ ባይታገሥ፥ ከቊርባንም፡ ባይቀበል፥ ከቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይለይ፥ የእግዚአብሔርን፡ ሕግ፡ አፍርሷልና፤ የነፍስና፡ የሥጋ፡ ንጉሥ፡ በሚኾን፡ በሰማያዊ፡ ንጉሥ፡ ፊት፡ መቆምንም፡ አቃሏልና። ሐዋርያት፡ በሲኖዶሳቸው፡ እንዲህ፡ አስተማሩን።

(ህየንተ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ እምትንሣኤ ፡ እስከ ፡ በዓለ ፡ ፶ ።)

፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (በአሐዱ) ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ዮሴፍ ፡ ወኒቆዲሞስ ፡ ገነዝዎ ፡ ለኢየሱስ ፡ በሰንዱናት ፡ ለዘተንሥአ ፡ እሙታን ፡ በመንክር ፡ ኪን ።

፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አንቲ ፡ ውእቱ ፡ መሶበ ፡ ወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ መና ፡ ኅቡዕ ፤ ኅብስት ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማያት ፡ ወሃቤ ፡ ሕይወት ፡ ለኵሉ ፡ ዓለም ።

፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ (ወእምዝ ፡ ይቁም ፡ ካህን ፡ ርቱዐ ፡ ሰፊሖ ፡ እዴሁ ፡ ወገጹ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ወይበል ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ።) አሐዱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፥ አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፥ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ በአማን ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፤ በአማን ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፤ በአማን ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲፩ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ወይሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ።

ይ ፡ ካ ፤ እስመ ፡ ጸንዐት ፡ ምሕረቱ ፡ ላዕሌነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ወጽድቁሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓለም ።

፲፪ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ከማሁ) ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፲፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

(ከትንሣኤ ፡ እስከ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፤ በ**እመቦ** ፡ ፈንታ ።)

፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (በአንድ) ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ዮሴፍና ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ድንቅ ፡ በሚኾን ፡ ጥበብ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣ ፡ ኢየሱስን ፡ በበፍታ ፡ ገነዙት ።

፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ንጹሕ ፡ የወርቅ ፡ መሶብ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፤ በውስጧ ፡ የተሰወረ ፡ መና ፡ የነበረባት ፤ ከሰማያት ፡ የወረደ ፡ ኅብስት ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ ድኅነትን ፡ የሚሰጥ ።

፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ (ከዚህ በኋላ ፥ ካህኑ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ይቁም ፤ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መልሶ ፡ አሰምቶ ፡ እንዲህ ፡ ይበል ፤) አንዱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

፲ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አብ ፡ በውነት ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ ወልድም ፡ በውነት ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በውነት ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አሕዛብ ፡ ኹላችኹም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ይ ፡ ሕ ፤ ሕዝብም ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑታል ።

ይ ፡ ካ ፤ ምሕረቱ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ጸንታለችና ።

ይ ፡ ሕ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይኖራል ።

፲፪ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፤ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፤ አሜን ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (እንደዚሁ) ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፤ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፤ አሜን ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፲፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፲፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (አቡነ ፡ ዘበሰማያት ።)

፲፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ኅሡ ፡ ወአስተብቍዑ ፡ ከመ ፡ ይምሐረነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሣሀል ፡ ላዕሌነ ። ወይትወከፍ ፡ ጸሎተ ፡ ወስእለተ ፡ እምነ ፡ ቅዱሳኒሁ ፡ በእንቲኣነ ፡ በዘይሤኒ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ይረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ንንሣእ ፡ እምሱታፌ ፡ ምስጢር ፡ ቡሩክ ፤ ወይስረይ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኪርያላይሶን ። (እግዚኦ ፡ ተሣሀል ።)

፲፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፲፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ያበውኡ ፡ መባአ ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ተወከፍ ፡ መባኦሙ ፡ ለአኃው ፥ ወተወከፍ ፡ መባኦን ፡ ለአኃት ፥ ለነኒ ፡ ተወከፍ ፡ መባአነ ፡ ወቍርባነነ ።

፳ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ (በትሑት ፡ ዜማ ።) ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፳፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ትእዛዘ ፡ አበዊነ ፡ ሐዋርያት ፤ ኢያንብር ፡ ብእሲ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ቂመ ፡ ወበቀለ ፡ ወቅንአተ ፡ ወጽልአ ፡ ላዕለ ፡ ቢጹ ፡ ወኢ ፡ ላዕለ ፡ መኑሂ ።

፳፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሀት ።

፲፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (አባታችን ሆይን ፡ ይድገሙ ።)

፲፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይምረን ፡ ዘንድ ፡ በኛም ፡ ላይ ፡ ይቅር ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ሹ ፥ ለምኑ ። ስለኛ ፡ ከቅዱሳን ፡ ጸሎትን ፡ ልመናንም ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ባማረ ፡ ነገር ፡ ቡሩክ ፡ ከሚኾን ፡ ምስጢር ፡ አንድነት ፡ እንድንቀበል ፡ የበቃን ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኪርያላይሶን ። (ጌታ ፡ ሆይ ፤ ይቅር ፡ በል ።)

፲፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፲፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ መባ ፡ ስለሚያገቡ ፡ ሰዎች ፡ ጸልዩ ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ የወንድሞችን ፡ መባ ፡ ተቀበል ፤ የእኅቶችንም ፡ መባ ፡ ተቀበል ፤ የኛንም ፡ መባችንንና ፡ ቍርባናችንን ፡ ተቀበል ።

፳ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ (በትሑት ፡ ዜማ ።) ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፳፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ያባቶቻችን ፡ የሐዋርያት ፡ ትእዛዝ ፤ ሰው ፡ በልቡ ፡ ቂምንና ፡ በቀልን ፥ ቅንአትንና ፡ ጠብን ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፡ አይያዝ ።

፳፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በፍርሀት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ።

፲፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሖከ ።

፲፬ ፤ ዲያቆን ፡ አው ፡ ቀሲስ ፤ በእንተ ፡ ቅድሳት ፡ ሰላማዊት ፡ ሰላመ ፡ ናስተበቍዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስተሳልመነ ፡ በሣህሉ ፡ ዚኣሁ ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (ለለ ፡ ምዕራፉ ።) አሜን ። ኪርያላይሶን ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፲፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ንስግድ ፡ (ሠለስተ ፡ ጊዜ) ።

ይ ፡ ሕ ፤ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ሠለስቲ ፡ አሐዱ ፡ (ሠለስተ ፡ ጊዜ) ።

፲፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኪ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማኅደረ ፡ መለኮት ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ሰአሊ ፡ ለነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፳ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አንቲ ፡ ውእቱ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ማዕጠንት ፡ ዘወርቅ ፡ እንተ ፡ ፆርኪ ፡ ፍሕመ ፡ እሳት ፡ ቡሩክ ፡ ዘነሥአ ፡ እመቅደስ ፡ ዘይሰሪ ፡ ኀጢአተ ፡ ወይደመስስ ፡ ጌጋየ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሰብአ ፡ እምኔኪ ፡ ዘአዕረገ ፡ ለአቡሁ ፡ ርእሶ ፡ ዕጣነ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ሥሙረ ። ንሰግድ ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ አቡከ ፡ ኄር ፡ ሰማያዊ ፡ ወመንፈስከ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ፡ እስመ ፡ መጻእከ ፡ ወአድኀንከነ ።

፳፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ በፊትኽ ፡ እንሰግዳለን ፥ እናመሰግንኻለንም ።

፳፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፤ አንድ ፡ ስለምታደርግ ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይቅርታው ፡ አንድ ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ፡ ሰላምን ፡ እንማልዳለን ።

፳፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (በየምዕራፉ) አሜን ። ኪርያላይሶን ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

፳፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፳፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ እንስገድ ፡ (ሦስት ፡ ጊዜ) ።

ይ ፡ ሕ ፤ ሦስት ፡ ሲኾኑ ፡ አንድ ፡ ለሚኾኑ ፡ ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንስገድ ፡ (ሦስት ፡ ጊዜ) ።

፳፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ላንቺ ፡ ይገባል ።

ይ ፡ ሕ ፤ የመለኮት ፡ ማደሪያ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፳፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ለምኚልን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አምላክን ፡ የወለድሽ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ።

፴ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አንቺ ፡ ነሽ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ቡሩክ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ የተቀበላት ፡ የእሳትን ፡ ፍሕም ፡ የተሸከምሽ ፡ የወርቅ ፡ ጥና ፡ አንቺ ፡ ነሽ ። ኀጢአትን ፡ የሚያስተሰርይ ፡ በደልንም ፡ የሚያጠፋ ፡ ይኸውም ፡ ካንቺ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ራሱን ፡ ያማረ ፡ መሥዋዕትና ፡ ዕጣን ፡ አድርጎ ፡ ላባቱ ፡ ያሳረገ ። ይኸውም ፡ ካንቺ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ቸር ፡ ሰማያዊ ፡ ከሚኾን ፡ አባትኽ ፡ ጋራ ፡ ከማሕየዊ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስኽም ፡ ጋራ ፡ እንሰግድልኻለን ፥ መጥተኽ ፡ አድነኸናልና ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ካ ፤ (እንዘ ፡ የዐውድ ፡ ኅበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በበ ፡ አንቀጹ ።)
ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ይደሉ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ይደልዎሙ ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ይ ፡ ዲ ፤ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕሩይ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

፲፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

(ንባበ ፡ መልእክተ ፡ ጳውሎስ ።)

፲፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ሠናየ ፡ መልእክት ፡ ፈዋሴ ፡ ዱያን ፡ ዘነሣእከ ፡ አክሊለ ፡ ሰአል ፡ ወጸሊ ፡ በእንቲአነ ፡ ያድኅን ፡ ነፍሳተነ ፡ በብዝኃ ፡ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤

(ንባበ ፡ መልእክታተ ፡ ሐዋርያት ።)

፳ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ዘኅቡር ፡ ህላዌከ ፡ ዕቀብ ፡ ማኅበረነ ፡ በእንተ ፡ ቅዱሳን ፡ ኀሩያን ፡ አርዳኢከ ፡ ናዝዘነ ፡ በሣህልከ ፡ በእንተ ፡ ቅዱስ ፡ ስምከ ።

፴፩ ፤ ይ፡ ካ፤ (በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሲዞር፡ በየደጃፉ።) ልዩ፡ ሦስት፡ ለሚኾኑ፡ ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስም፡ ኹል፡ ጊዜ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይገባል።

ይ፡ ሕ፤ ለአብ፥ ለወልድና፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ምስጋና፡ ይገባቸዋል።

ይ፡ ዲ፤ ኹል፡ ጊዜም፡ ለተካከሉ፡ ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስ፥ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘላለሙ።

ይ፡ ሕ፤ አሜን።

፴፪፤ ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ ለኹላችኹ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

(የጳውሎስ፡ መልእክት፡ ንባብ።)

፴፫፤ ይ፡ ሕ፤ አክሊልን፡ የተቀበልኽ፥ ዱያንን፡ የምታድን፥ መልእክትኽ፡ የበጀ፡ ቅዱስ፡ ሐዋርያ፡ ጳውሎስ፡ ሆይ፤ በይቅርታውና፡ በቸርነቱ፡ ብዛት፡ ስለ፡ ቅዱስም፡ ስሙ፡ ሰውነታችንን፡ ያድን፡ ዘንድ፡ ስለኛ፡ ለምን፥ ጸልይም።

፴፬፤ ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ ለኹላችኹ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

ይ፡ ዲ፤ (የሐዋርያት፡ መልእክቶች፡ ንባብ።)

፴፭፤ ይ፡ ሕ፤ ባሕርይኽ፡ አንድ፡ የሚኾን፡ ልዩ፡ ሦስት፡ ሆይ፤ አንድነታችንን፡ ጠብቅ፤ ስለ፡ ተመረጡ፡ ክቡራን፡ ደቀ፡ መዛሙርትኽ፡ በይቅርታኽ፡ አጽናን፤ ክቡር፡ ስለሚኾን፡ ስለ፡ ስምኽ።

፶፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፤ (ንባበ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ።)

፶፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ አብ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ።

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘአንተ ፡ ቃለ ፡ አብ ፡ ሕያው ።

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘተአምር ፡ ኵሎ ።

፶፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፶፱ ፤ (ወእምዝ ፡ ይፃኡ ፡ ኅቡረ ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ መንጦላዕት ፡ ወይበሉ ፡ በተባርዮ ፡ እንዘ ፡ ይትቀነዩ ።) ዝ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ባርኮት ፡ ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ዕጣን ፡ ኅሩይ ፡ ጊዜ ፡ ሰብሖቱ ፡ ለመድኅኒነ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ክርስቶስ ።

፷ ፤ ዕጣን ፡ ይእቲ ፡ ማርያም ፤ ዕጣን ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ዘውስተ ፡ ከርሣ ፡ ዘይትሜዐዝ ፡ እምኵሉ ፡ ዕጣን ፡ ዘወለደቶ ፡ መጽአ ፡ ወአድኀነነ ።

፷፩ ፤ ዕፍረት ፡ ምዑዝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ንዑ ፡ ንስግድ ፡ ሎቱ ፡ ወንዕቀብ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ከመ ፡ ይስረይ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ።

፴፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ። (የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ንባብ ።)

፴፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኹሉን ፡ የያዝኽ ፡ አብ ፡ ሆይ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

የሕያው ፡ አብ ፡ ቃል ፡ የምትኾን ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ሆይ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

ኹሉን ፡ የምታውቅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

፴፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፴፱ ፤ (ከዚህ ፡ በኋላ ፥ ባንድነት ፡ ወደ ፡ መጋረጃው ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፥ በዜማ ፡ እየተቀባበሉ ፡ እንዲህ ፡ ይበሉ ፤) የማመስገን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የተመረጠ ፡ የዕጣን ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ መድኀኒታችንን ፡ ክርስቶስን ፡ ማመስገኛ ፡ ጊዜ ።

፵ ፤ ማርያም ፡ ዕጣን ፡ ናት ። ዕጣን ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ በማሕፀኗ ፡ ያደረው ፡ ከተመረጠ ፡ ዕጣን ፡ ኹሉ ፡ የሚሸት ፡ ነውና ፡ የወለደችው ፥ መጥቶ ፡ አዳነን ።

፵፩ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መዐዛ ፡ ያለው ፡ ሽቱ ፡ ነው ፤ ኑ ፡ እንስገድለት ፥ ትዛዞቹንም ፡ እንጠብቅ ፥ ኀጢአታችንን ፡ ያስተሰርይልን ፡ ዘንድ ።

፹፪ ፤ ተውህቦ ፡ ምሕረት ፡ ለሚካኤል ፡ ወብሥራት ፡ ለገብርኤል ፡ ወሀብተ ፡ ሰማያት ፡ ለማርያም ፡ ድንግል ።

፹፫ ፤ ተውህቦ ፡ ልቡና ፡ ለዳዊት ፡ ወጥበብ ፡ ለሰሎሞን ፡ ወቀርነ ፡ ቅብዕ ፡ ለሳሙኤል ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቀብዕ ፡ ነገሥተ ።

፹፬ ፤ ተውህቦ ፡ መራኁት ፡ ለአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወድንግልና ፡ ለዮሐንስ ፡ ወመልእክት ፡ ለአቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፹፭ ፤ ዕፍረት ፡ ምዕዝት ፡ ይእቲ ፡ ማርያም ፡ እስመ ፡ ዘውስተ ፡ ከርሣ ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምኵሉ ፡ ዕጣን ፡ መጽአ ፡ ወተሠገወ ፡ እምኔሃ ።

፹፮ ፤ ለማርያም ፡ ድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ሠምራ ፡ አብ ፡ ወአሰርገዋ ፡ ደብተራ ፡ ለማኅደረ ፡ ፍቁር ፡ ወልዱ ።

፹፯ ፤ ተውህቦ ፡ ሕግ ፡ ለሙሴ ፡ ወክህነት ፡ ለአሮን ፤ ተውህቦ ፡ ዕጣን ፡ ኅሩይ ፡ ለዘካርያስ ።

፹፰ ፤ ደብተራ ፡ ስምዕ ፡ ገብርዋ ፡ በከመ ፡ ነገረ ፡ እግዚእ ፡ ወአሮን ፡ ካህን ፡ በማእከላ ፡ ያዐርግ ፡ ዕጣነ ፡ ኅሩየ ።

፹፱ ፤ ሱራፌል ፡ ይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ወኪሩቤል ፡ ይሴብሕዎ ፡ ይጸርሑ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ።

፺ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኀበ ፡ አእላፍ ፡ ወክቡር ፡ በውስተ ፡ ረበዋት ።

፺፩ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዕጣን ፡ ኦ ፡ መድኅኒነ ፡ እስመ ፡ መጻእከ ፡ ወአድኀንከነ ፡ ተሣሀለነ ።

(ዓዲ ፡ ህየንተ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ እምትንሣኤ ፡ እስከ ፡ በዓለ ፡ ፶ ።)

፺፪ ፤ ክርስቶስ ፡ ተንሥአ ፡ እሙታን ፤ ሞተ ፡ ወኬደ ፡ ለሞት ፤ ለእለ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ወሀበ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ዕረፍተ ።

(ኪዳን)

፺፫ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ቅዱስ ።

፵፪፤ ለሚካኤል፡ ምሕረት፡ ተሰጠው፥ ለገብርኤልም፡ ማብሠር፥ ለድንግል፡ ማርያምም፡ ሰማያዊ፡ ሀብት።

፵፫፤ ለዳዊት፡ ልቡና፥ ለሰሎሞንም፡ ጥበብ፥ ለሳሙኤልም፡ ነገሥታቱን፡ የቀባ፡ ርሱ፡ ነውና፡ የሸቱ፡ ቀንድ፡ ተሰጠው።

፵፬፤ ላባታችን፡ ለጴጥሮስ፡ መክፈቻ፥ ለዮሐንስም፡ ድንግልና፥ ላባታችን፡ ለጳውሎስም፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ ብርሃኗ፡ ርሱ፡ ነውና፡ መልእክት፡ ተሰጠው።

፵፭፤ መዐዛ፡ ያላት፡ ሽቱ፡ ማርያም፡ ናት፤ በማሕፀኗ፡ ያለው፡ ከዕጣን፡ ኹሉ፡ የሚበልጥ፡ ነውና፡ መጥቶ፡ ከርሷ፡ ሰው፡ ኾነ።

፵፮፤ ንጽሕት፡ ድንግል፡ ማርያምን፡ አብ፡ ወደዳት፡ ለተወደደ፡ ልጁም፡ ማደሪያ፡ ልትኾን፡ አስጌጻት።

፵፯፤ ለሙሴ፡ ሕግ፡ ለአሮንም፡ ክህነት፡ ተሰጠው። ለካህኑ፡ ለዘካርያስም፡ የተመረጠ፡ ዕጣን፡ ተሰጠው።

፵፰፤ የምስክር፡ ድንኳን፡ አደረጋት። ጌታ፡ እንደ፡ ተናገረ፡ ካህኑ፡ አሮንም፡ በመካከሷ፡ የተመረጠውን፡ ዕጣን፡ ያሳርጋል።

፵፱፤ ሱራፌል፡ ይሰግዱለታል፥ ኪሩቤልም፡ ያመሰግኑታል።

፶፤ እግዚአብሔር፡ በአእላፍ፡ መላእክት፡ ዘንድ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ነው፡ እያሉ፡ ይጮኻሉ፤ ባለቆችም፡ ዘንድ፡ ክቡር፡ ነው።

፶፩፤ መድኀኒታችን፡ ሆይ፤ ዕጣን፡ አንተ፡ ነኽ፤ መጥተኽ፡ አድነኽናልና፡ ይቅር፡ በለን።

(ዳግመኛም፡ ከትንሣኤ፡ እስከ፡ በዓለ፡ ፶፡ በዝ፡ **ው.አ.ቱ**፡ ፈንታ።)

፶፪፤ ክርስቶስ፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ ተነሣ፤ ሞቶ፡ ሞትን፡ አጠፋው፤ በመቃብር፡ ላሉ፡ የዘላለም፡ ዕረፍት፡ የሚኾን፡ ሕይወትን፡ ሰጠ።

(የኪዳን፡ ጸሎት፤)

፶፫፤ ይ፡ ካ፤ ቅዱስ።

፵፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ኀያል ፡ ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፡ ዘተወልደ ፡ እማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ተሣሀለነ ፡ እግዚኦ ።

ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ኀያል ፡ ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፤ ዘተጠምቀ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ። ተሣሀለነ ፡ እግዚኦ ።

ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ኀያል ፡ ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፡ ዳግመ ፡ ይመጽእ ፡ በስብሐት ፡ ይኰንን ፡ ሕያዋነ ፡ ወሙታነ ፡ ተሣሀለነ ፡ እግዚኦ ።
ስብሐት ፡ ለአብ ፥ ስብሐት ፡ ለወልድ ፥ ስብሐት ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፥ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ፡ ወአሜን ፤ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ተሣሀለነ ።

፵፭ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ጸጋ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

ይ ፡ ካ ፤ ንሰብሖ ፡ ለአምላክነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ርቱዕ ፤ ይደሉ ።

ይ ፡ ካ ፤ አጽንዑ ፡ ኅሊና ፡ ልብክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

፵፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኪያከ ፡ ንሴብሕ ፡ እግዚኦ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ኪያከ ፡ ንዌድስ ፡ እግዚኦ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

፶፬፤ ይ፡ ሕ፤ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ፡ ኀያል፥ ቅዱስ፡ ሕያው፥ የማይሞት። ከቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ የተወለደ። አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ፡ ኀያል፥ ቅዱስ፡ ሕያው፡ የማይሞት፤ በዮርዳኖስ፡ የተጠመቀ፥ በመስቀል፡ ላይ፡ የተሰቀለ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ፡ ኀያል፥ ቅዱስ፡ ሕያው፡ የማይሞት፤ በሦስተኛው፡ ቀን፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ የተነሣ። በምስጋና፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ወጣ። ባባቱም፡ ቀኝ፡ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በጌትነት፡ ይመጣል፥ በሕያዋንና፡ በሙታን፡ ይፈርድ፡ ዘንድ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን። ለአብ፡ ምስጋና፡ ይኹን፤ ለወልድ፡ ምስጋና፡ ይኹን፤ ለመንፈስ፡ ቅዱስም፡ ምስጋና፡ ይኹን። ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘላለሙ፤ አሜን፤ አሜን፤ ይኹን፤ ይኹን።

ልዩ፡ ሦስት፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፤ ይቅር፡ በለን።

፶፭፤ ይ፡ ካ፤ የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ከኹላችኹም፡ ጋራ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

ይ፡ ካ፤ አምላካችንን፡ እናመስግነው።

ይ፡ ሕ፤ እውነት፡ ነው፤ ይገባል።

ይ፡ ካ፤ የልቡናችኹን፡ ሐሳብ፡ አጽኑ።

ይ፡ ሕ፤ በሰማይ፡ ባለ፡ አባታችን፡ ዘንድ፡ ዋጋ፡ አለን፤ አቤቱ፡ ወደ፡ ፈተና፡ አታግባን።

፶፮፤ ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ አንተን፡ እናመሰግናለን።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ አንተን፡ እናመሰግናለን።

ይ፡ ሕ፤ አሜን።

፵፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኦ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ መሐረነ ፤

ኦ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ መሀከነ ፤

ኦ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሣሀለነ ።

፵፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ቦአ ፡ መልአክ ፡ ኀቤሃ ፡ ወቆመ ፡ ቅድሜሃ ፥ ወይቤላ ፡ ተፈሥሒ ፤ ተፈሥሒ ፤ ተፈሥሒ ፥ ኦ ፡ ምልዕተ ፡ ጸጋ ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምስሌኪ ።

ይ ፡ ካ ፤ ቡርክት ፡ አንቲ ፡ እምአንስት ።

ይ ፡ ሕ ፤ ወቡሩክ ፡ ፍሬ ፡ ከርሥኪ ።

ይ ፡ ካ ፤ ተንብሊ ፡ ወሰአሊ ፡ ለነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ኀበ ፡ ፍቁር ፡ ወልድኪ ።

ይ ፡ ካ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመ ፡ ይስረይ ፡ ለነ ፡ ኀጣውኢነ ።

፵፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፶ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ይረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ለሰሚዐ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ።

፶፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤

(ቅድመ ፡ ወንጌል ፡ ምስባክ ፡ አእሚሮ ፡ ዘለለ ፡ ዕለቱ ፡ እመዝሙረ ፡ ዳዊት ።)

፶፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ቁሙ ፡ ወአጽምዑ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱሰ ፡ ዜናሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፶፯፤ ይ፡ ሕ፤ ልዩ፡ሦስት፡ሆይ፤ ማረን፤

ልዩ፡ሦስት፡ሆይ፤ ራራልን፤

ልዩ፡ሦስት፡ሆይ፤ ይቅር፡በለን።

፶፰፤ ይ፡ ካ፤ መልአክ፡ወደ፡ርሷ፡ገብቶ፥ በፊቷ፡ቁሞ፦ ጸጋን፡ የተመላሽ፡ሆይ፤ ደስ፡ይበልሽ፤ ደስ፡ይበልሽ፤ ደስ፡ይበልሽ፤ አላት።

ይ፡ ሕ፤ እግዚአብሔር፡ካንቺ፡ጋራ፡ነው።

ይ፡ ካ፤ ከሴቶች፡ተለይተሽ፡የተባረክሽ፡ነሽ።

ይ፡ ሕ፤ የማሕፀንሽም፡ፍሬ፡የተባረከ፡ነው።

ይ፡ ካ፤ ለምኚልን፤ አማልጂንም።

ይ፡ ሕ፤ ወደ፡ተወዳጅ፡ልጅሽ።

ይ፡ ካ፤ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

ይ፡ ሕ፤ ኀጢአታችንን፡ያስተሰርይልን፡ዘንድ።

፶፱፤ ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ይቅር፡በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ለኹላችኹ፡ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ጋራ።

፷፤ ይ፡ ዲ፤ ክቡር፡ስለሚኾን፥ ስለ፡ወንጌል፡ጸልዩ።

ይ፡ ሕ፤ የከበረ፡ወንጌልን፡ለመስማት፡የበቃን፡ያድርገን።

፷፩፤ ይ፡ ዲ፤

(ከወንጌል፡አስቀድሞ፡ለየቀኑ፡የሚገባውን፡ዐውቆ፡ከዳዊት፡አወጻጽቶ፡ይስበክ።)

፷፪፤ ይ፡ ዲ፤ ሃሌ፡ሉያ፤ ጌታችን፡መድኀኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ የተናገረውን፡ቅዱስ፡ወንጌልን፡ቁማችኹ፡ስሙ።

፳ር ፤ ይ ፡ ካ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፳፬ ፤ ይ ፡ ካ ፤ (በልዑል ፡ ዜማ ።) ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘሰበከ ፡ ዮሐንስ ፡ ቃለ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።

(በማቴዎስ ፥ በማርቆስ ፡ ወበሉቃስ ፡ ዘዜነወ ፡ ይበል ።)

፳፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ስብሐት ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ።

፳፮ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ተፈሥሑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘረድአነ ፥ ወየብቡ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ፤ ንሥኡ ፡ መዝሙረ ፤ ወሀቡ ፡ ከበሮ ፡ መዝሙር ፡ ሐዋዝ ፡ ዘምስለ ፡ መሰንቆ ።

(በጾም ፡ ህየንተ ፡ ተፈሥሑ ።)

በወንጌል ፡ መራሕከነ ፥ ወበነቢያት ፡ ናዘዝከነ ። ዘለሊከ ፡ አቅረብከነ ፡ ስብሐት ፤ ለከ ።

(ወይሳለሙ ፡ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወንጌለ ።)

፳፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ነዋ! ወንጌለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፤ መንግሥቱ ፡ ወጽድቁ ፡ ዘአወፈየኒ ፡ አወፈይኩከ ።

(ወየሀቦ ፡ ለዲያቆን ።)

ይ ፡ ዲ ፤ ነስሑ ፡ ወእመኑ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

(ወእምድኅረ ፡ አንበበ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ።)

፳፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ዘማቴዎስ ፤ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኀልፍ ፥ ወቃልየሰ ፡ ኢየኀልፍ ፥ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ ለአርዳኢሁ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ነአምን ፡ አበ ፡ ዘበአማን ፥ ወነአምን ፡ ወልደ ፡ ዘበአማን ፥ ወነአምን ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ዘበአማን ፤ ህልወ ፡ ሥላሴሆሙ ፡ ነአምን ።

፳፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ዘማርቆስ ፤ ዘቦ ፡ እዝን ፡ ሰሚዐ ፡ ለይስማዕ ።

፳፫፤ ይ፡ ካ፤ እግዚአብሔር፡ ከኹላችኹ፡ ጋራ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፳፬፤ ይ፡ ካ፤ (በታላቅ፡ ዜማ፤) ዮሐንስ፡ የሰበከው፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ቃል፡ ቅዱስ፡ ወንጌል፡ ይህ፡ ነው።

(በማቴዎስና፡ በማርቆስ፡ በሉቃስም፡ **ዘዜነወ**፡ ይበል።)

፳፭፤ ይ፡ ሕ፤ ጌታዬና፡ አምላኬ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፤ ኹል፡ ጊዜ፡ ላንተ፡ ምስጋና፡ ይገባል።

፳፮፤ ይ፡ ሕ፤ በረዳን፡ በእግዚአብሔር፡ ደስ፡ ይበላችኹ፤ የያዕቆብንም፡ አምላክ፡ አመስግኑ፤ መዝሙሩን፡ ያዙ፤ ከበሮውንም፡ ስጡ፤ መዝሙር፡ ከበገና፡ ጋራ፡ የተስማማ፡ ነው።

(በጾም፡ በ**ተፈሥሒ**፡ ፈንታ።)

በወንጌል፡ መራኸን፤ በነቢያትም፡ አጸናኸን። አንተ፡ ቅሉ፡ ላቀረብከን፡ ምስጋና፡ ይገባል።

(ካህናቱና፡ ሕዝቡም፡ ኹሉ፡ ወንጌልን፡ ይሳለሙ።)

፳፯፤ ይ፡ ካ፤ ወደ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ የምታገባ፡ ወንጌል፡ እንሆ!

ይ፡ ካ፤ መንግሥቱንና፡ ጽድቁን፡ የሰጠኝን፡ ሰጠኹኽ።

(ብሎ፡ ለዲያቆኑ፡ ይስጠው።)

ይ፡ ዲ፤ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ቀርባለችና፥ ንስሓ፡ ግቡ።

(የወንጌልን፡ ቃል፡ ካነበበም፡ በኋላ።)

፳፰፤ ይ፡ ካ፤ በማቴዎስ፤ ሰማይና፡ ምድር፡ ያልፋል፥ ቃሌ፡ ግን፡ አያልፍም፥ አለ፡ ጌታ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ።

ይ፡ ሕ፤ አብን፡ በውነት፡ እናምናለን፤ ወልድን፡ በውነት፡ እናምናለን፤ መንፈስ፡ ቅዱስንም፡ በውነት፡ እናምናለን፤ የማይለወጥ፡ ሦስትነታቸውን፡ እናምናለን።

፳፱፤ ይ፡ ካ፤ በማርቆስ፤ ዦሮ፡ ያለው፡ መስማትን፡ ይስማ።

ይ ፡ ሕ ፤ እሉ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሱራፌል ፡ የዐርጉ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐተ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፫ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ዘሉቃስ ፤ ይቀልል ፡ ኀልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እምትደቅ ፡ አሐቲ ፡ ቃል ፡ እምኦሪት ፡ ወእምነቢያት ።

ይ ፡ ሕ ፤ መኑ ፡ ይመስለከ ፡ እምን ፡ አማልክት ፥ እግዚኦ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘትገብር ፡ መንክረ ፤ አርአይኮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ኀይለከ ፤ ወአድኀንኮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ በመዝራዕትከ ። ሖርከ ፡ ውስተ ፡ሲኦል ፥ ወአዕረገ ፡ ዔዋ ፡ እምህየ ፤ ወጸገብከነ ፡ ምዕረ ፡ ዳግመ ፡ ግዕዛነ ፥ እስመ ፡ መጻእከ ፡ ወአድኀንከነ ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንሴብሐከ ፥ ወንጸርሕ ፡ ኀቤከ ፡ እንዘ ፡ ንብል ፡— ቡሩክ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፥ እስመ ፡ መጻእከ ፡ ወአድኀንከነ ።

፫፩ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ዘዮሐንስ ፤ ዘየአምን ፡ በወልድ ፡ ቦ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፤ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፤ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፤ ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ፩ ፡ ዋሕድ ፡ ለአቡሁ ። ቃለ ፡ አብ ፡ ሕያው ፤ ወቃል ፡ ማሕየዊ ። ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተንሥአ ፤ ወሥጋሁኒ ፡ ኢማሰነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ✣

፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ፃኡ ፡ ንኡሰ ፡ ክርስቲያን ።

ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሠሃሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ሰላመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥ አሐቲ ፡ ቅድስት ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ርትዕት ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

፻ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኪርያላይሶን ። (እግዚኦ ፡ ተሠሃሀል ።)

ይ፡ ሕ፤ እሊህ፡ ኪሩቤልና፡ ሱራፌል፡ ምስጋናን፡ ያቀርቡለታል፡— አብ÷ ወልድ÷ መንፈስ፡ ቅዱስ፤ ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ፡ አንተ፡ እግዚአብሔር፡ ነኽ፡ እያሉ።

፸፤ ይ፡ ካ፤ በሉቃስ፤ ከኦሪትና፡ ከነቢያት፡ አንዲቱ፡ ቃል፡ ከምትወድቅ፡ የሰማይና፡ የምድር፡ ማለፍ፡ ይቀላል።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፤ ካማልክት፡ ወገን፡ የሚመስልኽ፡ ማነው? ተኣምራትን፡ የምታደርግ፡ አንተ፡ ነኽ፤ ለወገኖችኽ፡ ኀይልኽን፡ አሳየኻቸው፤ ወገኖችኽንም፡ በክንድኽ፡ አዳንካቸው። ወደ፡ ሲኦል፡ ኼደኽ፡ ከዚያ፡ ምርኮን፡ አወጣኽ፤ ዳግመኛም፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ነጻነትን፡ ሰጠኸን። መጥተኽ፡ አድነኸናልና÷ ስለዚህ፡ እናመሰግንኻለን፤ አቤቱ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፤ ቡሩክ፡ ነኽ፡ እያልን፡ እንጮኻለን÷ መጥተኽ፡ አድነኸናልና።

፸፩፤ ይ፡ ካ፤ በዮሐንስ፤ በወልድ፡ ያመነ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው።

ይ፡ ሕ፤ ቃል፡ በቅድምና፡ ነበረ። ይህ፡ ቃል፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ነው፤ ያ፡ ቃል፡ ሥጋ፡ ኾነ፤ በኛም፡ ዐደረ። ላባቱ፡ እንዳንድ፡ ልጅ፡ የሚኾን፡ ክብሩንም፡ አየን። የሕያው፡ የአብ፡ ቃል፡ ነው፤ ቃልም፡ ማሕየዊ፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ተነሣ፤ ሥጋውም፡ አልጠፋም።

## ምዕራፍ፡ ፪

፩፤ ይ፡ ዲ፤ የክርስቲያን፡ ታናናሾች፡ ውጡ።

ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ ለኹላችኹ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፪፤ ይ፡ ዲ፤ ሐዋርያት፡ ለሰበሰቧት፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለቀናች፡ ላንዲት፡ ክብርት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሰላም፡ ጸልዩ።

፫፤ ይ፡ ሕ፤ ኪርያላይሶን። (ጌታ፡ ሆይ፤ ይቅር፡ በል።)

፴ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ፤

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፲ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፥ ወማኅበርነ ፡ በውስቴታ ።

፳ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ማኅበረነ ፡ ባርክ ፤ ዕቀብ ፡ በሰላም ።

፳ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ንበል ፡ ኵልነ ፥ በጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፥ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ።

## አመክንዮ ፡ ዘሐዋርያት ።

ይ ፡ ሕ ፤ ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ አምላክ ፥ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፥ እስመ ፡ አልቦ ፡ ውስተ ፡ ህላዌሁ ፡ አመክንዮ ።

በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ፥ አላ ፡ ባሕቲቱ ፡ ህልው ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡ አልቦቱ ፡ ጥንተ ፡ ወኢተፍጻሜተ ፥ ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍእ ፤ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ቀሪበ ፡ ኀቤሁ ።

ኢኮነ ፡ ክልኤተ ፥ ወኢሠለስተ ፥ ወኢይትዌሰክ ፥ አላ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘይነብር ፡ ለዓለም ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ስዉረ ፡ ዘኢይትአመር ፤ ዳእሙ ፡ ጥዩቀ ፡ አእመርናሁ ፡ በኦሪት ፡ ወበነቢያት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፥ ወሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ።

አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ዘተወልደ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፥ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ሰራዊት ፡ ወሀሊመታት ፡ ወሥልጣናት ።

፴፤ ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ ለኹላችኹ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፳፩፤ ይ፡ ዲ፤ ክብርት፡ ስለምትኾን፡ ስለዚች፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፥ በውስጧ፡ ስላሉ፡ አንድነታችንም፡ ጸልዩ።

፳፪፤ ይ፡ ሕ፤ አንድነታችንን፡ ባርክ፤ በሰላም፡ ጠብቅ።

፳፫፤ ይ፡ ዲ፤ በእግዚአብሔር፡ ጥበብ፡ ኹነን፥ ኹላችን፡ የሃይማኖትን፡ ጸሎት፡ እንበል።

## የሐዋርያት፡ አመክንዮ ፨

ይ፡ ሕ፤ የጌታችንና፡ ያምላካችን፡ የመድኀኒታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አባት፡ በሚኾን፥ ፍጥረቱን፡ ኹሉ፡ በፈጠረ፡ ባንድ፡ አምላክ፡ እናምናለን፤ በባሕርዩ፡ ምክንያት፡ የለበትምና።

አስቀድመን፡ እንደ፡ ተናገርን፥ በዘመኑ፡ ኹሉ፡ ይኖራል፡ እንጂ፥ ጥንት፡ ወይም፡ ፍጻሜ፡ የለውምና፥ የማይጠፋ፡ ብርሃን፡ አለው፤ ወደ፡ ርሱም፡ መቅረብ፡ የሚቻለው፡ የለም።

ኹለተኛ፡ አይደለም፥ ሦስተኛም፡ አይደለም፥ አይጨመርበትም፤ ብቻውን፡ ለዘላለሙ፡ የሚኖር፡ አንድ፡ ነው፡ እንጂ፤ የማይታወቅ፥ የተሰወረ፡ አይደለምና፥ ኹሉን፡ የያዘና፡ ከፍጥረቱም፡ ኹሉ፡ በላይ፡ የሠለጠነ፡ መኾኑን፡ በኦሪትና፡ በነቢያት፡ ፈጽመን፡ ዐወቅነው፡ እንጂ።

የጌታችንና፡ የመድኀኒታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አባት፡ እግዚአብሔር፡ አንድ፡ ነው፤ ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ የተወለደ፥ ከርሱ፡ ጋራ፡ የተካከለ፡ የሚኾን፡ አንድ፡ ልጅ፡ ሰራዊትንና፡ ሢመታትን፡ ሥልጣናትንም፡ ኹሉ፡ የፈጠረ።

ዘሠምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ወነሥአ ፡ ሥጋ ፡ እማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወተሐፅነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀጢአት ፡ ወአበሳ ፡ ወአልቦ ፡ ግሕሉት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ።

ወእምዝ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ በሥጋ ፥ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፤ ወዐርገ ፡ ሰማያተ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ዘፈነዎ ፥ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ ኀይል ፡ ወፈነወ ፡ ለነ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘወፅአ ፡ እምአብ ፥ ወአድኀነ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ዘህልው ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ።

ንብል ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሠናይ ፡ ፍጥረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአልቦ ፡ ግዱፍ ፡ ወመንፈስሰ ፡ ሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ይእቲ ፡ ንጽሕት ፡ ወቅድስት ፡ በኵሉ ።

ወንሕነሰ ፡ ንብል ፡ ከመ ፡ ሰብሳብ ፡ ንጹሕ ፡ ወልደት ፡ ዘአልቦ ፡ ርኵስ ፥ እስመ ፡ ፈጠሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወለሔዋን ፡ ከመ ፡ ይብዝኍ ፡ ሕዝብ ፡ ንለቡ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ውስተ ፡ ሥጋነ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ኢትመውት ፡ ወኢትማስን ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ።

ንሕነሰ ፡ ናስቄርር ፡ ኵሎ ፡ ግብሮሙ ፡ ለዕልዋነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኵሎ ፡ ፍልጠተ ፡ ወዓሊወ ፡ ሕግ ፡ እስመ ፡ ርኵሳን ፡ እሙንቱ ፡ በኀቤነ ።

ወካዕበ ፡ ነአምን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ጻድቃን ፡ ወኃጥአን ፡ ወዕለተ ፡ ኵነኔ ፡ አመ ፡ ይትፈደይ ፡ ኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ።

ወዓዲ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢኮነ ፡ ሕጹጸ ፡ እምትስብእቱ ፡ ወኢምንተኒ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ በጽድቅ ፡ ወዐረቀ ፡ ትዝምደ ፡ ሰብእ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊቀ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለአብ ።

ኢንትግዘር ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ ዘይፌጽም ፡ ኦሪተ ፡ ወነቢያተ ።

በኋለኛው፡ ዘመን፥ ሰው፡ ይኾን፡ ዘንድ፡ የወደደ፥ ያለዘርዐ፡ ብእሲ፡ ቅድስት፡ ከምትኾን፡ ከመቤታችን፡ ከድንግል፡ ማርያም፡ ሥጋን፡ ነሣ። ያለኀጢአትና፡ ያለበደል፡ እንደ፡ ሰው፡ አደገ። ባንደበቱም፡ ሐሰት፡ የለበትም።

ከዚህ፡ በኋላ፥ በሥጋ፡ ታመመ፤ ሞተም፤ በሦስተኛውም፡ ቀን፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ ተነሣ፤ ወደላከውም፡ ወደ፡ አብ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ዐረገ፤ ኀይል፡ ባለውም፡ ቀኝ፡ ተቀመጠ፤ ከአብ፡ የሠረጸ፡ጰራቅሊጦስ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ሰደደልን፤ ዓለሙንም፡ ኹሉ፡ አዳነ፥ ከአብና፡ ከወልድ፡ ጋራ፡ ህልው፡ የሚኾን።

እንግዲህ፡ የእግዚአብሔር፡ ፍጥረት፡ ኹሉ፡ በጎ፡ እንደ፡ ኾነ፥ የሚጣልም፡ እንደሌለ፡ እንናገራለን፤ የሥጋ፡ ሕይወት፡ የምትኾን፡ ነፍስ፡ ግን፡ ንጽሕት፥ ቅድስት፡ ናት።

እኛስ፡ ጋብቻ፡ ንጹሕ፡ እንደ፡ ኾነ፥ ልደትም፡ ርኵሰት፡ እንደሌለበት፡ እንናገራለን፤ ሕዝቡ፡ ይበዙ፡ ዘንድ፥ እግዚአብሔር፡ አዳምንና፡ ሔዋንን፡ ፈጥሯቸዋልና። ከሥጋ፡ ጋራ፡ የማትሞትና፡ የማትበሰብስ፡ ነፍስ፡ በሥጋችን፡ እንዳለን፡ እናስተውል።

እኛስ፡ የሃይማኖት፡ ለዋጮችን፥ ሥራቸውን፡ እንጸየፋለን፤ መለየታቸውንም፡ ኹሉ፥ ሕግን፡ መለወጣቸውንም፤ እነርሱ፡ በኛ፡ ዘንድ፡ የረከሱ፡ ናቸውና።

ዳግመኛም፡ የሞቱ፡ የጻድቃንና፡ የኃጥአን፡ ትንሣኤ፡ እንዳለ፡ እናምናለን፤ ኹሉ፡ እንደ፡ ሥራው፡ ፍዳውን፡ የሚቀበልበት፡ የፍርድ፡ ቀንም፡ እንዳለ፡ እናምናለን።

ዳግመኛ፥ ክርስቶስ፡ ሰው፡ ከመኾኑ፡ የተነሣ፥ ምንም፡ ምን፡ ሕጸጽ፡ እንደሌለበት፡ እናምናለን፤ በውነት፡ ሰው፡ የኾነ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ነው፡ እንጂ። የአብ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ የሚኾን፡ ርሱ፡ የሰውን፡ ባሕርይ፡ ከእግዚአብሔር፡ ጋራ፡ አስታረቀ።

እንግዲህ፡ እንደ፡ አይሁድ፡ አንገዘር፤ ኦሪትንና፡ ነቢያትን፡ የሚፈጽማቸው፡ እንደ፡ መጣ፡ እናውቃለን።

ዘኪያሁ ፡ ይሴፈዉ ፡ ምጽአቶ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምይሁዳ ፡ እምሥርወ ፡ ዕሤይ ፡ ዘሥልጣኑ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ለዘ ፡ ስብሐት ፡ ወአኰቴት ፤ ዕበይ ፡ ወባርኮት ፤ ውዳሴ ፡ ወማሕሌት ፤ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

## ጸሎት ፡ ሃይማኖት ፡ (ዘሊቃውንት) ፨

፲ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ነአምን ፡ በ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ።

ወነአምን ፡ በ፩ዱ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋሕድ ፡ ዘሀልው ፡ ምስሌሁ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ።

ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ አምላክ ፡ ዘእምአምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ዘተወልደ ፡ ወአኮ ፡ ዘተገብረ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ።

ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮነ ፡ ወዘእንበሌሁሰ ፡ አልቦ ፡ ዘኮነ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ዘበሰማይኒ ፡ ወዘበምድርኒ ።

ዘበእንቲአነ ፡ ለሰብእ ፡ ወበእንተ ፡ መድኀኒትነ ፡ ወረደ ፡ እምሰማያት ፡ ተሰብአ ፡ ወተሠገወ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ።

ኮነ ፡ ብእሴ ፡ ወተሰቅለ ፡ በእንቲአነ ፡ በመዋዕለ ፡ ጲላጦስ ፡ ጰንጤናዊ ። ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ።

ዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ። ዳግመ ፡ ይመጽእ ፡ በስብሐት ፡ ይኰንን ፡ ሕያዋነ ፡ ወሙታነ ። ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥቱ ።

ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ ፡ ማሕየዊ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፡ ንስግድ ፡ ለዘ ፡ ወንሰብሖ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ዘነበበ ፡ በነቢያት ።

ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ።

አሕዛብ፡ ኹሉ፡ የርሱን፡ መምጣት፡ ተስፋ፡ የሚያደርጉት፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከይሁዳ፡ ከዕሤይም፡ ሥር፡ የተገኘ፥ ሥልጣኑ፡ በትከሻው፡ ላይ፡ የኾነ፡ ነው፤ ክብር፥ ምስጋናና፡ ገናንነት፥ ቡራኬና፡ ውዳሴ፥ መመስገን፡ ለርሱ፡ ይገባዋል፤ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘላለሙ፤ አሜን።

## የሃይማኖት፡ ጸሎት፡ (የሊቃውንት)

፫፤ ይ፡ ሕ፤ ኹሉን፡ በያዘ፥ ሰማይንና፡ ምድርን፥ የሚታይና፡ የማይታየውን፡ በፈጠረ፡ ባንድ፡ አምላክ፡ በእግዚአብሔር፡ አብ፡ እናምናለን።

ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ በነበረ፡ የአብ፡ አንድ፡ ልጁ፡ በሚኾን፡ ባንድ፡ ጌታ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስም፡ እናምናለን።

ከብርሃን፡ የተገኘ፡ ብርሃን፤ ከውነተኛ፡ አምላክ፡ የተገኘ፡ አምላክ፤ የተፈጠረ፡ ያይደለ፥ የተወለደ፤ በመለኮቱ፡ ከአብ፡ ጋራ፡ የሚተካከል።

ኹሉ፡ በርሱ፡ የኾነ፥ ያለርሱ፡ ግን፡ ምንም፡ ምን፡ የኾነ፡ የለም፥ በሰማይም፡ ያለ፡ በምድርም፡ ያለ።

ስለኛ፡ ስለ፡ ሰው፥ ስለ፡ መዳናችን፡ ከሰማይ፡ ወረደ፤ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ የተነሣ፡ ከቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያምም፡ ፈጽሞ፡ ሰው፡ ኾነ።

ሰው፡ ኾኖ፡ በጳንጤናዊ፡ በጲላጦስ፡ ዘመን፡ ስለኛ፡ ተሰቀለ፥ ታመመ፥ ሞተ፥ ተቀበረም፤ በሦስተኛውም፡ ቀን፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ ተነሣ፥ በቅዱሳት፡ መጻሕፍት፡ እንደ፡ ተጻፈ።

በክብር፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ዐረገ፤ ባባቱም፡ ቀኝ፡ ተቀመጠ። ዳግመኛ፡ ሕያዋንን፡ ሙታንንም፡ ይገዛ፡ ዘንድ፡ በጌትነት፡ ይመጣል። ለመንግሥቱም፡ ፍጻሜ፡ የለውም።

ጌታ፡ ማሕየዊ፡ በሚኾን፡ ከአብ፡ በሠረጸ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስም፡ እናምናለን። እንስግድለት፡ እናመሰግነውም፡ ዘንድ፡ ከአብና፡ ከወልድ፡ ጋራ፡ በነቢያት፡ የተናገረ።

ከኹሉ፡ በላይ፡ በምትኾን፡ ሐዋርያት፡ በሰበሰቧት፡ ባንዲት፡ ቅድስት፡ ቤተ፡ ክርስቲያንም፡ እናምናለን።

ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ጥምቀት ፡ ለስርየተ ፡ ኀጢአት ። ወንሴፎ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወሕይወተ ፡ ዘይመጽእ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

(ወተኀፅቦተ ፡ እዴሁ ፡ ለቀሲስ ፡ አምሳለ ፡ ኀፅበተ ፡ እዴሁ ፡ ለጲላጦስ ፡ ለነጺሕ ፡ እምደመ ፡ ንጹሕ ። ከማሁ ፡ ይምዕድ ፡ ካህን ፡ ሕዝበ ፡ በመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ወበመልእክተ ፡ ጳውሎስ ፡ ወበመልእክተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወበመጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ወበወንጌል ። ወበምክንያቱሰ ፡ ለዝ ፡ ለነጺሕ ፡ እምኀጢአተ ፡ ሕዝብ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይነሥእ ፡ እምስጢር ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ኢይደልዎ ፡ ካህን ፡ ንጹሕ ፡ እምኀጢአቱ ፡ እምድኅረ ፡ ነገረ ፡ ዘንተ ፡ ምዕዳነ ።)

፲፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ዘአስተሐቀረ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዘሠሐቀ ፡ ወዘተናገረ ፡ አው ፡ ዘቆመ ፡ በእከይ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለያእምር ፡ ወይጠይቅ ፡ ከመ ፡ አምእዶ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአንሰሐስሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ህየንተ ፡ ቡራኬ ፡ መርገም ፡ ወህየንተ ፡ ስርየተ ፡ ኀጢአት ፡ እሳት ፡ ገሃነም ፡ ይረክብ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፲፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤

(ከካህኑ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ተቀብለው ።)

ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡ ለሰብእ ።

፲፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ሰላም ፡ ፍጽምት ፡ ወፍቅር ፡ ተአምኁ ፡ በበይናቲክሙ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ንትአማኃ ፡ በበይናቲነ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ።

(በዝየ ፡ ይትአምኁ ፡ ቀሳውስት ፡ ምስለ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ምስለ ፡ ዲያቆናት ፡ ወሕዝብ ፡ ምስለ ፡ ሕዝብ ፡ ወአንስት ፡ ምስለ ፡ አንስት ።)

ኀጢአትን ፡ ለማስተስረይ ፡ ባንዲት ፡ ጥምቀት ፡ እናምናለን ። የሙታንንም ፡ መነሣት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፤ የሚመጣውንም ፡ ሕይወት ፤ ለዘላለሙ ፤ አሜን ።

(ቄሱ ፡ እጁን ፡ መታጠቡ ፥ ከንጹሕ ፡ ደም ፡ ለመንጻት ፡ ጲላጦስ ፡ እጁን ፡ የመታጠቡ ፡ አምሳል ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ካህኑ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙርና ፡ በጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ በሐዋርያት ፡ መልእክትና ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ በወንጌልም ፡ ሕዝቡን ፡ ይመክራል ። የዚህም ፡ ምክንያቱ ፥ ከሕዝቡ ፡ ኀጢአት ፡ ለመንጻት ፡ ነው ፤ ካህኑ ፡ ይህን ፡ ምክሩን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥ ሳይገባው ፡ ቅዱስ ፡ ምስጢርን ፡ ከሚቀበል ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።)

፲፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ይህን ፡ የቄሱን ፡ ቃል ፡ ያቀለለ ፡ ወይም ፡ የሣቀና ፡ የተነጋገረ ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በክፋት ፡ የቆመ ፡ ቢኖር ፥ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዳሳዘነው ፡ በርሱም ፡ እንደ ፡ ተነሣሣ ፡ ይወቅ ፥ ይረዳ ፤ ስለ ፡ በረከት ፡ ፈንታ ፡ መርገምን ፥ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ስርየት ፡ ፈንታም ፡ ገሃነመ ፡ እሳትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቀበላል ።

፲፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኲላችኊ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፲፫ ፤ ይ ፡ ካ ፤

(ከካህኑ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ተቀብሎ ።)

በሰማይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፤ በምድርም ፡ ሰላም ፥ የሰው ፡ ፈቃድ ።

፲፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ፍጽምት ፡ ስለምትኾን ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ጸልዩ ፤ ርስ ፡ በርሳችኊ ፡ በተለየች ፡ እማኄ ፡ እጅ ፡ ተነሣሡ ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ርስ ፡ በርሳችን ፡ በተለየች ፡ እማኄ ፡ እጅ ፡ እንነሣሣ ፡ ዘንድ ፡ የበቃን ፡ አድርገን ።

(በዚህ ፡ ጊዜ ፥ ቀሳውስት ፡ ከቀሳውስት ፡ ጋራ ፥ ዲያቆናትም ፡ ከዲያቆናት ፡ ጋራ ፥ ሕዝቡም ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፥ ሴቶችም ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ እጅ ፡ ይነሣሡ ።)

# ቅዳሴ ፡ ሐዋርያት ✤

፮ ፤ ይ ፡ ካ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አእኵትዎ ፡ ለአምላክነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ርቱዕ ፡ ይደሉ ።

ይ ፡ ካ ፤ አልዕሉ ፡ አልባብክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በእንተ ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ እገሌ ፡ ወብፁዕ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ እገሌ ፡ እንዘ ፡ የአኵቱከ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ወበስእለቶሙ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ቀዳሜ ፡ ሰማዕት ። ዘካርያስ ፡ ካህን ፡ ወዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፤ ወበእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ወሰማዕት ፡ እለ ፡ አዕረፉ ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት ። ማቴዎስ ፡ ወማርቆስ ፥ ሉቃስ ፡ ወዮሐንስ ፥ ፬ቱ ፡ ወንጌላውያን ። ማርያም ፥ ወላዲተ ፡ አምላክ ፥ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ወእንድርያስ ፥ ያዕቆብ ፡ ወዮሐንስ ፥ ፊልጶስ ፡ ወበርተሎሜዎስ ፥ ቶማስ ፡ ወማቴዎስ ፥ ታዴዎስ ፡ ወናትናኤል ፡ ወያዕቆብ ፡ ወልደ ፡ እልፍዮስ ፡ ወማትያን ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ወያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ እኁሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ ጳውሎስ ፥ ጢሞቴዎስ ፥ ሲላስ ፡ ወበርናባስ ፥ ቲቶ ፥ ፊልሞና ፡ ወቀሌምንጦስ ፥ ፸ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ አርድእት ፥ ፭፻ ፡ ቢጽ ፡ ፫፻፲ ፡ ወ፰ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ይብጽሐነ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ኪያነ ፡ ሐውጽ ። ወተዘከር ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሰላማ ፡ ወበክቡር ፡ ደም ፡ እንተ ፡ በክርስቶስ ፡ ተገብረ ። ተዘከር ፡ ኵሎ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፥ ጳጳሳተ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳተ ፡ ወዲያቆናተ ፡ ቃል ፡ ዘበአማን ።

፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ መሐሮሙ ፡ እግዚኦ ፡ ወተሣሀሎሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፥ ጳጳሳት ፥ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፥ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፥ ወኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

## የሐዋርያት፡ ቅዳሴ ፨

፩፤ ይ፡ ካ፤ እግዚአብሔር፡ ከኹላችኹ፡ ጋራ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፪፤ ይ፡ ካ፤ አምላካችንን፡ አመስግኑት።

ይ፡ ሕ፤ እውነት፡ ነው፤ ይገባል።

ይ፡ ካ፤ ልቡናችኹን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጉ።

ይ፡ ሕ፤ በአምላካችን፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ አለን።

፫፤ ይ፡ ዲ፤ ብፁዕ፡ ቅዱስ፡ ስለሚኾን፡ ስለ፡ ርእሰ፡ ጳጳሳቱ፡ ስለ፡ አባ፡ እገሌ፡ ብፁዕም፡ ስለሚኾን፡ ስለ፡ አባ፡ እገሌ፡ በጸሎታቸውና፡ በልመናቸው፡ ሲያመሰግኑኽ፡ የሰማዕታት፡ መዠመሪያ፡ እስጢፋኖስ፥ ካህኑ፡ ዘካርያስና፡ መጥምቁ፡ ዮሐንስ። በሃይማኖት፡ ስላረፉ፡ ስለ፡ ቅዱሳንና፡ ስለ፡ ሰማዕታት፡ ኹሉ፡ ፬ቱ፡ ወንጌላውያን፥ ማቴዎስና፡ ማርቆስ፥ ሉቃስና፡ ዮሐንስ። አምላክን፡ የወለደች፡ ማርያም፥ ጴጥሮስ፡ የተባለ፡ ስምዖን፥ እንድርያስም፥ ያዕቆብና፡ ዮሐንስ፥ ፊልጶስና፡ በርተሎሜዎስ፥ ቶማስና፡ ማቴዎስ፥ ታዴዎስና፡ ናትናኤል። የእልፍዮስ፡ ልጅ፡ ያዕቆብ፥ ማትያንም፥ ዐሥራ፡ ኹለቱ፡ ሐዋርያት፥ የኢየሩሳሌም፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ፥ የጌታችን፡ ወንድም፡ ሐዋርያ፡ ያዕቆብ፥ ጳውሎስ፥ ጢሞቴዎስ፥ ሲላስና፡ በርናባስ፥ ቲቶ፥ ፊልሞና፥ ቀሌምንጦስም፥ ሰባ፡ ኹለቱ፡ አረድእት፥ ዐምስት፡ መቶ፡ ባልንጀሮች፥ ሃይማኖታቸው፡ የቀና፡ ሦስት፡ መቶ፡ ዐሥራ፡ ስምንት፡ ሊቃውንት፥ የኹሉም፡ ጸሎት፡ ይድረሰን፤ ከነርሱም፡ ጋራ፡ እኛን፡ ጐብኝ። ከኹሉ፡ በላይ፡ የምትኾን፡ የሐዋርያትንም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዐስብ፤ በፍቅሯ፥ በክርስቶስም፡ በተደረገው፡ በከበረ፡ ደም። በውነት፡ የቃልን፡ መንገድ፡ የሚያቀኑ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳቱን፥ ጳጳሳቱን፥ ኤጲስ፡ ቆጶሳቱን፥ ቀሳውስቱንና፡ ዲያቆናቱን፡ ዐስብ።

፬፤ ይ፡ ዲ፤ አቤቱ፤ የጳጳሳቱን፡ አለቆች፥ ጳጳሳቱንና፡ ኤጲስ፡ ቆጶሳቱን፥ ቀሳውስቱንና፡ ዲያቆናቱን፥ የክርስቲያኑንም፡ ወገኖች፡ ኹሉ፡ ማራቸው፤ ይቅርም፡ በላቸው።

፷ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ተንሥኡ ።

፷፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ውስተ ፡ ጽባሕ ፡ ነጽሩ ።

፷፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ንነጽር ።

፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ አውሥኡ ።

፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ ፍጹም ፤ ምሉእ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ።

፲ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ። ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ ኦ ፡ ሊቅ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ። ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ። በከመ ፡ ተዘከርኮ ፡ ለፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ እንዘ ፡ ሀሎከ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ።

፲፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ አንሥኡ ፡ እደዊክሙ ፡ ቀሳውስት ።

ይ ፡ ካ ፤ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አመ ፡ ያገብእዎ ፡ ነሥአ ፡ ኅብስተ ፡ በእደዊሁ ፡ ቅዱሳት ፡ ወብፁዓት ፡ እለ ፡ እንበለ ፡ ነውር ።

፲፪ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ነአምን ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።

ይ ፡ ካ ፤ አንቃዕደወ ፡ ሰማየ ፡ ኀቤከ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ አእኰተ ፡ ባረከ ፡ ወፈተተ ።

ይ ፡ ካ ፤ ወወሀቦሙ ፡ ለእሊኣሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ብልዑ ፡ ዝ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋየ ፡ ውእቱ ፡ ለዘበእንቲኣክሙ ፡ ይትፌተት ፡ ለኅድገተ ፡ ኀጢአት ።

፲፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ፤ አሜን ፤ አሜን ፤ ነአምን ፡ ወንትአመን ፤ ንሴብሐከ ፡ ኦ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።

ይ ፡ ካ ፤ ወከማሁ ፡ ጽዋዐኒ ፡ አእኰቶ ፡ ባሪኮ ፡ ወቀዲሶ ፡ መጠዎሙ ፡ ለእሊኣሁ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ስትዩ ፡ ዝ ፡ ጽዋዕ ፡ ደምየ ፡ ውእቱ ፡ ለዘበእንቲኣክሙ ፡ ይትከዓው ፡ ለቤዛ ፡ ብዙኃን ።

፳፭፤ ይ፡ ዲ፤ የተቀመጣችኹ፡ ተነሡ።

፳፮፤ ይ፡ ዲ፤ ወደ፡ ምሥራቅ፡ ተመልከቱ።

፳፯፤ ይ፡ ዲ፤ እናስተውል።

፳፰፤ ይ፡ ዲ፤ ተሰጥዎውን፡ መልሱ።

፶፬፤ ይ፡ ሕ፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ፍጹም፡ አሸናፊ፡ እግዚአብሔር፥ የጌትነትኽ፡ ምስጋና፡ በሰማይና፡ በምድር፡ የመላ፡ ነው።

፲፤ ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ በመንግሥትኽ፡ ዐስበን፤ ሊቀ፡ ሆይ፤ አቤቱ፡ በመንግሥትኽ፡ ዐስበን፤ ቅዱስ፡ በሚኾን፡ በዕፀ፡ መስቀል፡ ላይ፡ ሳለኽ፡ ፈያታዊ፡ ዘየማንን፡ እንዳሰብከው፡ አቤቱ፡ በመንግሥትኽ፡ ዐስበን።

፲፩፤ ይ፡ ዲ፤ ቀሳውስት፡ እጆቻችኹን፡ አንሡ።

ይ፡ ካ፤ ርሱን፡ በያዙባት፡ በዚያች፡ ሌሊት፥ ነውር፡ በሌለባቸው፡ ንኡዳት፥ ክቡራት፥ ብፁዓትም፡ በሚኾኑ፡ እጆቹ፡ ኅብስቱን፡ አንሥቶ፡ ያዘ።

፲፪፤ ይ፡ ሕ፤ ይህ፡ እንደ፡ ኾነ፡ በውነት፡ እናምናለን።

ይ፡ ካ፤ ወዳንተ፡ ወዳባቱ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ቀና፡ ብሎ፡ አመሰገነ፤ ባረከ፤ ፈተተ።

ይ፡ ካ፤ ለወገኖቹ፥ ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሰጣቸው፡— ንሡ፤ ብሉ፤ ይህ፡ ኅብስት፡ ለኀጢአት፡ ማስተስረያ፡ ሊኾን፡ ስለናንተ፡ የሚፈተት፡ ሥጋዬ፡ ነው፡ አላቸው።

፲፫፤ ይ፡ ሕ፤ አሜን፤ አሜን፤ አሜን፤ እናምናለን፤ እንታመናለንም። ጌታችንና፡ አምላካችን፡ ሆይ፤ እናመሰግንኻለን፤ ይህ፡ ርሱ፡ እንደ፡ ኾነ፡ በውነት፡ እናምናለን።

ይ፡ ካ፤ እንዲሁም፡ ጽዋውን፡ አመስግኖ፥ ባርኮ፥ አክብሮ፥ ለወገኖቹ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሰጣቸው፡— ንሡ፤ ጠጡ፤ ይህ፡ ጽዋ፡ ለብዙ፡ ሰዎች፡ ቤዛ፡ ሊኾን፥ ስለናንተ፡ የሚፈስ፡ ደሜ፡ ነው፡ አላቸው።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ፤ አሜን ፤ አሜን ፤ ነአምን ፡ ወንትአመን ፤ ንሴብሐከ ፡ ኦ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።

ይ ፡ ካ ፤ ወሶበ ፡ ትገብርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ተዝካረ ፡ ዚአየ ፡ ግበሩ ።

፲፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ንዜኑ ፡ ሞተከ ፡ እግዚኦ ፡ ወትንሣኤከ ፡ ቅድስተ ፤ ነአምን ፡ ዕርገተከ ፡ ወዳግመ ፡ ምጽአተከ ፤ ንሴብሐከ ፡ ወንትአመነከ ፡ ንስእለከ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ ኦ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ይእዜኒ ፡ እግዚኦ ፡ ንዜክር ፡ ሞተከ ፡ ወትንሣኤከ ፡ ንትአመነከ ፡ ወናቀርብ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ ወዘንተ ፡ ጽዋዐ ፡ እንዘ ፡ ነአኵተከ ፡ ወቦቱ ፡ ረሰይከ ፡ ለነ ፡ ለተድላ ፡ ንቁም ፡ ቅድሜከ ፡ ወለከ ፡ ንትከሀን ፡ ንስእለከ ፡ እግዚኦ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ ከመ ፡ ትፌኑ ፡ ቅዱሰ ፡ መንፈሰ ፡ ወኀይለ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ ወላዕለ ፡ ዝ ፡ ጽዋዕ ።

ይረስዮ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሞ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ፤ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፤

እግዚኦ ፡ መሀከነ ፤

እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በኵሉ ፡ ልብ ፡ ናስተብቍዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ኅብረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ይጸግወነ ።

፲፯ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ሀሎ ፡ ህልወ ፡ ወይሄሉ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ካ ፤ ደሚረከ ፡ ተሀቦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ ይኩኖሙ ፡ ለቅድሳት ፡ ወለምልአተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወለአጽንዖ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘበአማን ፡ ከመ ፡ ኪያከ ፡ ይቀድሱ ፡ ወይወድሱ ፡ ወለወልድከ ፡ ፍቁርከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ፡ ሕ፤ አሜን፤ አሜን፤ አሜን፡ እናምናለን፤ እንታመናለንም። ጌታችንና፡ አምላካችን፡ ሆይ፤ እናመሰግንኻለን፤ ይህ፡ ርሱ፡ እንደ፡ ኾነ፡ በውነት፡ እናምናለን።

ይ፡ ካ፤ ይህን፡ በምታደርጉበት፡ ጊዜ፡ የኔን፡ መታሰቢያ፡ አድርጉ።

፲፬፤ ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ሞትኽን፥ ቅድስት፡ ትንሣኤኽንም፡ እንነግራለን። ዕርገትኽን፡ ዳግመኛም፡ መምጣትኽን፡ እናምናለን፤ እናመሰግናለን፥ እናምንኻለንም። ጌታችንና፡ አምላካችን፡ ሆይ፤ እንለምንኻለን፥ እንማልድኻለንም።

ይ፡ ካ፤ አኹንም፥ አቤቱ፥ ሞትኽንና፡ ትንሣኤኽን፡ እናስባለን፤ እናምንኻለን። እያመሰገንኽ፡ ይህን፡ ኅብስት፥ ይህንም፡ ጽዋ፡ እናቀርብልኻለን፤ በፊትኽ፡ እንቆም፡ ዘንድ፥ አንተንም፡ እናገለግል፡ ዘንድ፡ በርሱ፡ ተድላን፡ አደረግኽልን። አቤቱ፡ እንለምንኻለን፥ እንማልድኻለንም፤ በዚህ፡ ኅብስት፡ ላይ፡ ቅዱስ፡ መንፈስኽን፥ ኀይልኽንም፡ ታሳድር፡ ዘንድ፥ በዚህም፡ በጽዋው፡ ላይ።

የጌታችንና፡ ያምላካችን፡ የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሥጋና፡ ደም፡ ያደርገው፡ ዘንድ፡ ለዘላለሙ።

፲፭፤ ይ፡ ሕ፤ አሜን፤ አቤቱ፡ ማረን፤

አቤቱ፡ ራራልን፤

አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

፲፮፤ ይ፡ ዲ፤ በፍጹም፡ ልብ፡ አምላካችንን፡ እግዚአብሔርን፡ እንማልደው፥ ያማረ፡ የመንፈስ፡ ቅዱስን፡ አንድነት፡ ይሰጠን፡ ዘንድ።

፲፯፤ ይ፡ ሕ፤ በፊት፡ እንደ፡ ነበረ፡ ለዘላለሙ፡ ለልጅ፡ ልጅ፡ ይኖራል።

ይ፡ ካ፤ ከርሱ፡ ለሚቀበሉ፡ ኹሉ፡ አንድ፡ አድርገኽ፡ ለንጽሕና፡ መንፈስ፡ ቅዱስንም፡ ለመመላት፡ እውነተኛውንም፡ ሃይማኖት፡ ለማጽናት፡ ስጣቸው፤ አንተን፡ ይቀድሱና፡ ያመሰግኑ፡ ዘንድ፡ ልጅኽን፥ ወዳጅኽን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስንም፥ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋራ።

ይ፡ ሕ፤ አሜን።

፲፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚኣከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወፈውሰነ ፡ በዝንቱ ፡ ጵርስፎራ ፡ ከመ ፡ ብከ ፡ ንሕየው ፡ ዘለኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ከማሁ ።)

፲፱ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ። ወይትባረክ ፡ ስመ ፡ ስብሐቲሁ ፤ ለይኩን ፤ ለይኩን ፤ ቡሩክ ፡ ለይኩን ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ከማሁ ።)

፳ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ፈኑ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌነ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ከማሁ ።)

፳፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፳፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ይትቀደስ ፡ ስምከ ፤ ትምጻእ ፡ መንግሥትከ ፤ ወይኩን ፡ ፈቃድከ ፡ በከመ ፡ በሰማይ ፡ ከማሁ ፡ በምድር ። ሲሳየነ ፡ ዘለለ ፡ ዕለትነ ፡ ሀበነ ፡ ዮም ። ኅድግ ፡ ለነ ፡ አበሳነ ፡ ወጌጋየነ ፡ ከመ ፡ ንሕነኒ ፡ ንኅድግ ፡ ለዘአበሰ ፡ ለነ ። ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ፤ አላ ፡ አድኅነነ ፡ ወባልሐነ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፤ እስመ ፡ ዚኣከ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥት ፡ ኃይል ፡ ወስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

፳፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ። (ሠለስተ ፡ ጊዜ ።)

(ወእምዝ ፡ በተባርዮ ፡ ኵሎሙ ፡ ይበሉ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ።)

፲፰፤ ይ፡ ካ፤ ያንተ፡ በሚኾን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አንድ፡ እንኾን፡ ዘንድ፡ ስጠን፤ በዚህም፡ ጽርስፎራ (በሥጋው፡ በደሙ)፡ አድነን፤ ለዓለሙ፡ ኹሉ፡ በምትኾን፡ ባንተ፡ ለዘላለሙ፡ ሕያዋን፡ እንኾን፡ ዘንድ።

ይ፡ ሕ፤ (እንደ፡ ርሱ።)

፲፱፤ ይ፡ ካ፤ የእግዚአብሔር፡ ስሙ፡ ምስጉን፡ ነው፤ በእግዚአብሔር፡ ስም፡ የሚመጣውም፡ ምስጉን፡ ነው። የጌትነቱ፡ ስም፡ ይመስገን፤ ይኹን፤ ይኹን፤ የተመሰገነ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ (እንደ፡ ርሱ።)

፳፤ ይ፡ ካ፤ የመንፈስ፡ ቅዱስን፡ ጸጋ፡ ላክልን።

ይ፡ ሕ፤ (እንደ፡ ርሱ።)

፳፩፤ ይ፡ ዲ፤ ለጸሎት፡ ተነሡ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን።

ይ፡ ካ፤ ሰላም፡ ለኹላችኹ፡ ይኹን።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፳፪፤ ይ፡ ዲ፤ ጸልዩ።

ይ፡ ሕ፤ አባታችን፡ ሆይ፤ በሰማይ፡ የምትኖር፥ ስምኽ፡ ይቀደስ፤ መንግሥትኽ፡ ትምጣ፤ ፈቃድኽ፡ በሰማይ፡ እንደ፡ ኾነ፡ እንዲሁም፡ በምድር፡ ትኹን፤ የለት፡ እንጀራችንን፡ ስጠን፡ ዛሬ፤ በደላችንንም፡ ይቅር፡ በለን፥ እኛ፡ የበደሉንን፡ ይቅር፡ እንደምንል። አቤቱ፡ ወደ፡ ፈተናም፡ አታግባን፤ ከክፉ፡ አድነን፡ እንጂ፤ መንግሥት፡ ያንተ፡ ናትና፤ ኀይልም፡ ምስጋናም፡ ለዘላለሙ።

፳፫፤ ይ፡ ሕ፤ አምላካችን፡ ሆይ፤ እንደ፡ ቸርነትኽ፡ ነው፡ እንጂ፥ እንደ፡ በደላችን፡ አይደለም። (ሦስት፡ ጊዜ።)

(ከዚህ፡ በኋላ፥ ኹሉም፡ እየተቀባበሉ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ይበሉ።)

ሰራዊተ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፻ ፡ ፻ ፡ ፻ ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወይኬልልዎ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ። ፻ ፡ ፻ ፡ ፻ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ። ፻ ፡ ፻ ፡ ፻ ፡ በአሚነ ፡ ዚኣሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንገኒ ።

(ወቦ ፡ ዘይብሉ ፡)

ሐዋርያት ፡ ተለዉ ፡ አሠሮ ።

## ዘቅዳሴ ፡ እግዚእ ✥

፲፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ሰራዊተ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ይቀዉሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወይኬልልዎ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፤ በአሚነ ፡ ዚኣሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንገኒ ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ (እንዘ ፡ ይበውእ ፤) አርኅዉ ፡ ኆኃተ ፡ መኳንንት ።

ይ ፡ ዲ ፤ እለ ፡ ትቀውሙ ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

ይ ፡ ዲ ፤ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሀት ።

ይ ፡ ሕ ፤ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሐከ ።

ይ ፡ ካ ፤ (ጸሎተ ፡ ንስሓ ፡ ይበል ።)

፲፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ነጽር ።

ይ ፡ ካ ፤ ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ፩ዱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፤ ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፤ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

የመድኃኔ፡ ዓለም፡ አገልጋዮች፡ የሚኾኑ፡ የመላእክት፡ ሰራዊት፡ ዬ፡ ዬ፡ ዬ፡ በመድኃኔ፡ ዓለም፡ ፊት፡ ይቆማሉ።

መድኃኔ፡ ዓለምን፡ ያመሰግኑታል፤ ዬ፡ ዬ፡ ዬ፡ የመድኃኔ፡ ዓለም፡ ሥጋውና፡ ደሙ።

ወደ፡ መድኃኔ፡ ዓለም፡ ፊት፡ እንቅረብ፤ ዬ፡ ዬ፡ ዬ፡ ርሱን፡ በማመን፡ ለክርስቶስ፡ እንገዛለን።

ሐዋርያት፡ ፍለጋውን፡ ተከተሉ። (የሚሉም፡ አሉ።)

## የቅዳሴ፡ እግዚእ፡ ሰራዊት፨

፳፬፤ ይ፡ ሕ፤ የመድኃኔ፡ ዓለም፡ የመላእክት፡ ሰራዊት፡ በመድኃኔ፡ ዓለም፡ ፊት፡ ይቆማሉ።

መድኃኔ፡ ዓለምን፡ ያመሰግኑታል፡ የመድኃኔ፡ ዓለም፡ ሥጋውና፡ ደሙ።

ወደ፡ መድኃኔ፡ ዓለም፡ ፊት፡ እንቅረብ፤ ርሱን፡ በማመን፡ ለክርስቶስ፡ እንገዛለን።

፳፭፤ ይ፡ ዲ፤ (ሲገባ።) መኳንንት፡ ደጆችን፡ ክፈቱ።

ይ፡ ዲ፤ የቆማችኹ፡ ሰዎች፥ ራሳችኹን፡ ዝቅ፡ ዝቅ፡ አድርጉ።

ይ፡ ዲ፤ በፍርሀት፡ ኹናችኹ፡ ለእግዚአብሔር፡ ስገዱ።

ይ፡ ሕ፤ አቤቱ፡ በፊትኽ፡ እንሰግዳለን፥ እናመሰግንኻለንም።

ይ፡ ካ፤ (የንስሓ፡ ጸሎትን፡ ይበል።)

፳፮፤ ይ፡ ዲ፤ ተመልከት።

ይ፡ ካ፤ ቅድሳት፡ ለቅዱሳን።

ይ፡ ሕ፤ ቅዱስ፡ አብ፡ አንድ፡ ነው፤ ቅዱስ፡ ወልድም፡ አንድ፡ ነው፤ መንፈስ፡ ቅዱስም፡ አንድ፡ ነው።

ይ ፡ ካ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፻፳ ፤ ይ ፡ ካ ፤ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፤

እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፤

እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፤

(፫ት ፡ ጊዜ ፡ በልዑል ፡ ዜማ ። ፲ት ፡ ወ፪ት ፡ ጊዜ ፡ በንኡስ ፡ ዜማ ።)

እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ከማሁ ።)

ይ ፡ ካ ፤ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ። (፫ት ፡ ጊዜ ።)

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ። (፮ት ፡ ጊዜ ።)

፻፲ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እለ ፡ ውስተ ፡ ንስሓ ፡ ሀለውክሙ ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

፻፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፤ እግዚኦ ፡ ተሣሀለነ ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ካ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከኹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

፳፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፤

አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፤

አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፤

(፫ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ዜማ ፡ አሰምቶ ፡ ይበል ፤ ፲፭ ፡ ጊዜም ፡ በንኡስ ፡ ዜማ ።)

አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ።

ይ ፡ ሕ ፤ (እንደ ፡ ርሱ ።)

ይ ፡ ካ ፤ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ። (ሦስት ፡ ጊዜ ።)

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ። (ኹለት ፡ ጊዜ ።)

፳፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በንስሓ ፡ ውስጥ ፡ ያላችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።

፳፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኹላችኹ ፡ ይኹን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

ሀ ፤

(ወእምቅድመ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባን ፡ ይበሉ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነሥኡ ፡ እምስጢር ፡ ቅዱስ ።)

ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አኮ ፡ ዘይደልወኒ ፡ ትባእ ፡ ታሕተ ፡ ጠፈረ ፡ ቤትየ ፡ ርኩስት ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አስተቈጣዕኩከ ፤ ወገበርኩ ፡ እኩየ ፡ በቅድሜከ ፡ ወአርኰስኩ ፡ ነፍስየ ፡ ወሥጋየ ፡ ዘፈጠርከ ፡ በአርኣያከ ፡ ወበአምሳሊከ ፡ በዐሊወ ፡ ትእዛዝከ ፤ ወአልብየ ፡ ምግባር ፡ ወኢምንትኒ ።

ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ተኪንዎትከ ፡ ወበእንተ ፡ ትስብእትከ ፡ በእንተ ፡ መድኀኒትየ ፡ ወበእንተ ፡ መስቀልከ ፡ ክቡር ፡ ወበእንተ ፡ ሞትከ ፡ ማሕየዊት ፡ ወበእንተ ፡ ትንሣኤከ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ እስእለከ ፡ ወአስተበቍዐከ ፡ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ከመ ፡ ታንጽሐኒ ፡ እምኵሉ ፡ አበሳ ፡ ወመርገም ፡ ወእምኵሉ ፡ ኀጢአት ፡ ወርኵስ ።

ወሶበ ፡ እትሜጠዎ ፡ ለምስጢረ ፡ ቅድሳቲከ ፡ ኢይኩነኒ ፡ ለቅሥት ፡ ወኢለኵነኔ ፤ አላ ፡ መሐረኒ ፡ ወተሣሀለኒ ። ወሀበኒ ፡ ቦቱ ፡ ስርየተ ፡ ኀጢአትየ ፡ ወሕይወተ ፡ ነፍስየ ፡ ኦ ፡ ሕይወተ ፡ ዓለም ፡ በስእለታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፤ ማርያም ፡ ወላዲትከ ፡ ወዮሐንስ ፡ መጥምቅ ። ወበጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰማዕት ፡ ወጻድቃን ፡ መስተጋድላን ፡ ለሠናይ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

(ቅድመ ፡ ይቅረቡ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስ ፡ ቆጶሳት ። ወእምድኅሬሆሙ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወካዕበ ፡ ኵሎሙ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዕደው ፡ ይትመጠዋ ፡ አንስት ፡ ሕፃናትሰ ፡ እለ ፡ ይጠመቁ ፡ ይትመጠዉ ፡ እምቅድመ ፡ ሕዝብ ።)

ሀ፩ (ወእምዝ ፡ በተባርዮ ፡ ኵሎሙ ፡ ይበሉ ።)

እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ። (ሠለስተ ፡ ጊዜ)

በእንተ ፡ ማርያም ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ። (ሠለስተ ፡ ጊዜ)

ይ ፡ ዲ ፤ ጸልዩ ፡ በእንቲኣነ ፡ ወበእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ይቤሉነ ፡ ግበሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ በሰላም ፤ ወበፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰብሑ ፡ ወዘምሩ ።

፹

(ቊርባኑን ፡ ከመቀበል ፡ አስቀድሞ ፡ ከቅዱስ ፡ ምስጢር ፡ የሚቀበሉ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይበሉ ።)

አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ፤ ርኵስት ፡ ከኾነች ፡ ከቤቴ ፡ ጠፈር ፡ በታች ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባኝ ፡ አይደለም ። እኔ ፡ አሳዝኜኻለኹና ፥ በፊትኽም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቻለኹና ፥ ባርኣያኽና ፡ ባምሳልኽ ፡ የፈጠርኸው ፡ ሥጋዬንና ፡ ነፍሴን ፡ ትእዛዝኽን ፡ በማፍረስ ፡ አሳድፌአለኹና ፥ ሥራም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የለኝምና ።

ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ መፍጠርኽና ፡ እኔን ፡ ለማዳን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መኾንኽ ፥ ስለ ፡ ክቡር ፡ መስቀልኽም ፥ ማሕየዊት ፡ ስለምትኾን ፡ ስለ ፡ ሞትኽ ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መነሣትኽም ፥ ጌታዬ ፡ ሆይ፤ ከበደልና ፡ ከመርገም ፡ ኹሉ ፡ ከኀጢአትና ፡ ከርኵሰትም ፡ ኹሉ ፡ ታነጻኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ፤ እማልድኻለኹ ።

የቅድስናኽንም ፡ ምስጢር ፡ በተቀበልኩት ፡ ጊዜ ፡ ለወቀሳ ፡ ለመፈራረጃ ፡ አይኹንብኝ፤ ማረኝ ፥ ይቅርም ፡ በለኝ ፡ እንጂ ። የዓለም ፡ ሕይወት ፡ ሆይ፤ በርሱ ፡ የኀጢአቴን ፡ ስርየት ፡ የነፍሴንም ፡ ሕይወት ፡ ስጠኝ ፡ እንጂ ። በኹለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ በምትኾን ፡ በወለደችኽ ፡ በእምቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ማርያም ፥ በመጥምቁ ፡ በዮሐንስም ፡ አማላጅነት፤ ክቡራን ፡ በሚኾኑ ፡ በመላእክትም ፡ በሰማዕታትና ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ በሚጋደሉ ፡ በጻድቃንም ፡ ኹሉ ፡ ጸሎት ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ፤ አሜን ።

(አስቀድሞ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፥ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ይቅረቡ ። ዳግመኛም ፥ ኹሉ ፡ በየማዕርጋቸው ፡ ይቅረቡ ። ከወንዶችም ፡ በኋላ ፡ ሴቶች ፡ ይቀበሉ፤ የሚጠመቁ ፡ ሕሕፃናት ፡ ግን ፥ ከሕዝቡ ፡ አስቀድሞ ፡ ይቀበሉ ።)

፹፩

(ከዚህ ፡ በኋላ ፥ ኹሉም ፡ እየተቀባበሉ ፡ ይበሉ ።)

አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ። (ሦስት ፡ ጊዜ)

ስለናትኽ ፡ ስለ ፡ ማርያም ፡ ብለኽ ፡ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ። (ሦስት ፡ ጊዜ)

ይ ፡ ዲ፤ ስለኛና ፡ መታሰቢያቸውን ፡ አድርጉ ፡ ስላሉን ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ጸልዩ፤ በሰላም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ፍቅር ፡ አመስግኑ ፥ ዘምሩም ።

፴፩ ፤ ይ ፡ ሐ ፤

(ወእምድኅረ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባን ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በአፉሁ ፡ ይበል ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩፩ ።)

ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ዘኢይትነገር ፤ ሀበኒ ፡ ከመ ፡ እንሣእ ፡ ለሕይወት ፡ ዘንተ ፡ ሥጋ ፡ ወደመ ፡ ዘእንበለ ፡ ኵነኔ ፤ ሀበኒ ፡ እግበር ፡ ፍሬ ፡ ዘያሠምረከ ፡ ከመ ፡ አስተርኢ ፡ በስብሐቲከ ፡ ወእሕየው ፡ ለከ ፡ እንዘ ፡ እገብር ፡ ዘዚኣከ ፡ ፈቃደ ።

በተአምኖ ፡ እጼውዐከ ፡ አብ ፡ ወእጼውዕ ፡ መንግሥተከ ፡ ይትቀደስ ፡ እግዚኦ ፡ ስምከ ፡ በላዕሌነ ።

ይ ፡ ሐ ፤ እስመ ፡ ኃያል ፡ አንተ ፡ እኵት ፡ ወስቡሕ ፡ ወለከ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

(ወእምዝ ፡ ይብላዕ ፡ ዘተመጠዎ ፡ ወጊዜ ፡ ተመጥዎቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ያንብር ፡ እዴሁ ፡ ዲበ ፡ አፉሁ ፡ ወይሐሊ ፡ በለ<sup></sup>ዋሳስ ፡ እስከ ፡ ያጸሬ ፡ አፉሁ ፡ በፍርሀት ፡ ወበረዓድ ።)

፴፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ነአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅድሳቶ ፡ ነሢአነ ፤ ከመ ፡ ለሕይወት ፡ ነፍስ ፡ ይኩነነ ፡ ፈውሰ ። ዘተመጦነ ፡ ንስእል ፡ ወንትመሐጸን ፡ እንዘ ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ስብሐት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግር ፡ አፉየ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ይባርክ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሐ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

ይ ፡ ዲ ፤ ተመጦነ ፡ እምሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ወእምደሙ ፡ ክቡር ፡ ለክርስቶስ ።

ይ ፡ ካ ፤ ስብሐት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግር ፡ አፉየ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ይባርክ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም

ይ ፡ ሐ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

ይ ፡ ዲ ፤ ወናእኵቶ ፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንሳተፍ ፡ ምስጢረ ፡ ክብርት ፡ ወቅድስት ።

ይ ፡ ካ ፤ ስብሐት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግር ፡ አፉየ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ይባርክ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሐ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

፴፪ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ (ቍርባን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፥ ባፉ ፡ ሳለ ፡ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ እንዲህ ፡ ይበል ።)

የማይነገር ፡ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ሦስት ፡ የምትኾን ፥ ይህን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ሕይወት ፡ ሊኾነኝ ፡ ሳይፈረድብኝ ፡ እቀበል ፡ ዘንድ ፡ ስጠኝ ። በጌትነትኽ ፡ እንድገለጽ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ ፍሬ ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ ስጠኝ ።

በማመን ፡ አባት ፡ ብዬ ፡ እጠራኻለኹ ፤ መንግሥትኽንም ፡ እጠራለኹ ። አቤቱ ፤ ስምኽ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ይመስገን ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስጉን ፡ ክቡር ፡ የምትኾን ፡ ኀያል ፡ አንተ ፡ ነኽና ፤ ላንተ ፡ ክብር ፡ ይገባኻል ፥ ለዘላለሙ ።

(ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተቀበለውን ፡ ይብላ ፤ በሚቀበልበትም ፡ ጊዜ ፥ እጁን ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ አኑሮ ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ያላምጥ ፥ በመፍራትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ኹኖ ፡ አፉን ፡ እስኪያጸራ ፡ ድረስ ።)

፴፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ሥጋውን ፥ ደሙን ፡ ተቀብለን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግነዋለን ፤ ለነፍሳችን ፡ አነዋወር ፡ መድኀኒት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የተቀበልን ፡ እኛ ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያምሰገንን ፡ እንለምናለን ፤ ዐደራም ፡ እንላለን ።

፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፤ አንደበቴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራል ። የሥጋ ፡ ፍጥረትም ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናል ፡ ለዘላለሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በሰማይ ፡ ያለኽ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ።

ይ ፡ ዲ ፤ ከክርስቶስ ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋውና ፡ ከክቡር ፡ ደሙም ፡ ተቀበልን ።

ይ ፡ ካ ፤ አንደበቴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራል ። የሥጋ ፡ ፍጥረትም ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናሉ ፤ ለዘላለሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በሰማይ ፡ ያለኽ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ።

ይ ፡ ዲ ፤ ክብርት ፡ ቅድስት ፡ የምትኾን ፡ ምስጢርን ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባናል ።

ይ ፡ ካ ፤ አንደበቴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራል ። የሥጋ ፡ ፍጥረትም ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ስሙን ፡ ያመሰግናል ፤ ለዘላለሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በሰማይ ፡ ያለኽ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፤ አቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ።

ሀ፯ ፤ ይ ፡ ካ ፤ (በእሑድ ፡ ወበዐበይት ፡ በዓላት ።) አሌዕለከ ፡ ንጉሥየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ወእባርክ ፡ ለስምከ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

ሀ፰ ፤ ይ ፡ ካ ፤ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ እባርከከ ፡ ወእሴብሕ ፡ ለስምከ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

ይ ፡ ካ ፤ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነግር ፡ አፉየ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ይባርክ ፡ ለስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፤ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ።

ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ።

(ወይበሉ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ወሰላመ ፡ ገብርኤል ።)

ሀ፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በእንተ ፡ አኰቴትነ ፡ ዓስተበቍዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ይጽሐፍ ፡ ስእለተነ ፤ ወአምላክ ፡ ዘለዓለም ፡ ይዘከረነ ፡ በምዕራፈ ፡ ቅዱሳን ፡ በዘዚኣሁ ፡ ብርሃን ።

በእንተ ፡ እለ ፡ ተድኅሩ ፡ አበዊነ ፡ ወአኀዊነ ፡ ዓስተበቍዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸግዎሙ ፡ ጽሒቀ ፡ ወያስተሐምም ፡ ለኵሉ ፡ ወይሚጥ ፡ እምኔሆሙ ፡ ማእሰረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወይሀቦሙ ፡ ግዕዘ ፡ ወፍቅረ ፡ አሚነ ፡ ወተስፋ ፡ ሠናየ ፡ በእንተ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ፡ ወአሜን ፤ ለይኩን ፤ ለይኩን ።

ሀ፲ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ ኦ ፡ ንጉሠ ፡ ሰላም ፡ ሰላማዊ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላመከ ፡ ሀበነ ፡ ወአጽንዕ ፡ ለነ ፡ ሰላመከ ። ወስረይ ፡ ለነ ፡ ኀጣውኢነ ፡ ወረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ ወንእቱ ፡ ውስተ ፡ አብያቲነ ፡ በሰላም ።

፴፭፤ ይ፡ ካ፤

(በእሑድና፡ በታላላቅ፡ በዓላት።)

ገዢዬና፡ አምላኬ፥ ክፍ፡ ከፍ፡ አደርግኻለኹ፤ ለስምኽም፡ ምስጋናን፡ አቀርባለኹ፥ ለዘላለሙ።

ይ፡ ሕ፤ በሰማይ፡ ያለኽ፡ አባታችን፡ ሆይ፤ አቤቱ፥ ወደ፡ ፈተና፡ አታግባን።

፴፮፤ ይ፡ ካ፤ ቀኑን፡ ኹሉ፡ አመሰግንኻለኹ፤ ለስምኽም፡ ምስጋና፡ አቀርባለኹ፥ ለዘላለሙ፤ አሜን።

ይ፡ ሕ፤ በሰማይ፡ ያለኽ፡ አባታችን፡ ሆይ፤ አቤቱ፥ ወደ፡ ፈተና፡ አታግባን።

ይ፡ ካ፤ አንደበቴ፡ የእግዚአብሔርን፡ ምስጋና፡ ይናገራል። የሥጋ፡ ፍጥረትም፡ ኹሉ፡ ቅዱስ፡ የሚኾን፡ ስሙን፡ ያመሰግናል፥ ለዘላለሙ።

ይ፡ ሕ፤ በሰማይ፡ ያለኽ፡ አባታችን፡ ሆይ፤ አቤቱ፥ ወደ፡ ፈተና፡ አታግባን።

ይ፡ ሕ፤ አሜን።

(አባታችን፡ ሆይንና፡ እመቤታችን፡ ማርያም፡ ሆይን፡ ይድገሙ።)

፴፯፤ ይ፡ ዲ፤ ስለ፡ ማመስገናችን፡ እንማልዳለን፤ እግዚአብሔር፡ በሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ልመናችንን፡ ይጽፍ፡ ዘንድ፥ ለዘላለሙ፡ የሚኖር፡ አምላክም፡ በቅዱሳን፡ ማደሪያ፡ በርሱ፡ ብርሃን፡ ያስበን፡ ዘንድ።

ወደ፡ ኋላ፡ ስላሉ፡ አባቶቻችንና፡ ወንድሞቻችን፥ ስለ፡ እኅቶቻችንም፡ እንማልዳለን፤ እግዚአብሔር፡ ትጋትን፡ ይሰጣቸው፡ ዘንድ፤ ለኹሉም፡ ያስብ፡ ዘንድ። የዚህን፡ ዓለም፡ ማሰሪያን፡ ከነርሱ፡ ይመልስ፡ ዘንድ፥ ሥርዐትን፡ ፍቅርንና፡ ማመንን፥ በጎ፡ ተስፋንም፡ ይሰጣቸው፡ ዘንድ፥ ስለ፡ እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ሥጋና፡ ደም፡ ለዘላለሙ፤ አሜን፤ ይኹን፤ ይኹን።

፴፰፤ ይ፡ ሕ፤ የፍቅር፡ ባለቤት፥ የሰላም፡ ንጉሥ፥ ሰላማዊ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፤ ሰላምኽን፡ ስጠን፤ ሰላምኽንም፡ አጽናልን፥ ኀጢአታችንንም፡ ይቅር፡ በለን፤ በሰላም፡ ወደ፡ ቤታችን፡ ኼደን፡ እንገባ፡ ዘንድ፡ የበቃን፡ አድርገን።

፻፶ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ አድኅኑ ፡ አርእስቲክሙ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ በእደ ፡ ገብሩ ፡ ካህን ፡ ከመ ፡ ይባርክሙ ።

፻፶፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርከነ ።

፻፶፮ ፤ ይ ፡ ካ ፤

(ቡሩኬ)

እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፻፶፪ ፤ ይ ፡ ሕ ፤ አሜን ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርከነ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ በሰላም ፡ ስርየተ ፡ ይኩነነ ፡ ዘተመጦነ ፡ ሥጋከ ፡ ወደመከ ፡ አብሐነ ፡ በመንፈስ ፡ ንኪድ ፡ ኵሎ ፡ ኀይሎ ፡ ለጸላኢ ። በረከተ ፡ እዴከ ፡ ቅድስተ ፡ እንተ ፡ ምልእተ ፡ ምሕረት ፡ ኪያሃ ፡ ንሴፎ ፡ ኵልነ ፡ እምኵሉ ፡ ምግባረ ፡ እኩይ ፡ አግኅሠነ ፡ ወውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ደምረነ ።

፻፶፫ ፤ ቡሩክ ፡ ዘወሀበነ ፡ ሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ወደሞ ፡ ክቡረ ፤ ጸጋ ፡ ነሣእነ ፡ ወሕይወተ ፡ ረከብነ ፡ በኀይለ ፡ መስቀሉ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ኪያከ ፡ እግዚኦ ፡ ነአኵቶ ፡ ነሢአነ ፡ ጸጋ ፡ ዘእመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ይ ፡ ዲ ፤ እትወ ፡ በሰላም ፨

፴፱፤ ይ፡ ዲ፤ ባምላካችን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ራሳችኹን፡ ዝቅ፡ ዝቅ፡ አድርጉ፤ አገልጋዩ፡ በሚኾን፡ በካህኑ፡ እጅ፡ ይባርካችኹ፡ ዘንድ።

፵፤ ይ፡ ሕ፤ አሜን፤ እግዚአብሔር፡ ይባርከን።

፵፩፤ ይ፡ ካ፤

(ቡራኬ)

እግዚአብሔር፡ ከኹላችኹም፡ ጋራ፡ ይኑር።

ይ፡ ሕ፤ ከመንፈስኽ፡ ጋራ።

፵፪፤ ይ፡ ሕ፤ አሜን፤ እግዚአብሔር፡ እኛን፡ ባሮቹን፡ በሰላም፡ ይባርከን። የተቀበልነው፡ ሥጋኽና፡ ደምኽ፡ ለስርየት፡ ይኹነን። የጠላትን፡ ኀይል፡ ኹሉ፡ በመንፈስ፡ እንረግጥ፡ ዘንድ፡ አሠልጥነን። ምሕረትን፡ የተመላች፡ ክብርት፡ የምትኾን፡ የእጅኽን፡ በረከት፡ ኹላችን፡ ተስፋ፡ እናደርጋለን፤ ከክፉ፡ ሥራ፡ ኹሉ፡ አርቀን፤ በበጎውም፡ ሥራ፡ ኹሉ፡ አንድ፡ አድርገን።

፵፫፤ ቅዱስ፡ ሥጋውን፥ ክቡር፡ ደሙንም፡ የሰጠን፡ ቡሩክ፡ ነው። ጸጋን፡ ተቀበልን፤ ደኅንነትንም፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ፡ ኀይል፡ አገኘን። አቤቱ፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ የተገኘ፡ ጸጋን፡ ተቀብለን፡ አንተን፡ እናመሰግናለን።

ይ፡ ዲ፤ በሰላም፡ ግቡ ❖

## ቅዳሴ ፡ እግዚእ ✠

፩ ፤ እመጽሐፊ ፡ ኪዳን ፡ ዘነገሮሙ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምቅድመ ፡ ዕርገቱ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ እምድኅረ ፡ ትንሣኤሁ ፡ እሙታን ፡ በረከት ፡ ጸጋሁ ፡ ወሀብተ ፡ ረድኤቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ እገሌ ፡ ወምስለ ፡ ኵልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በሰማይ ፡ የሀሉ ፡ ልብክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፤ እወ ፡ በሰማይ ፡ የሀሉ ፡ ልብነ ፤ በእንተ ፡ ስምከ ፡ አጽንዐነ ፡ ወረስየነ ፡ ድልዋነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ።

፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ወለእመቦ ፡ ዘተሐየሰ ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ፡ ይኅድግ ፡ ሎቱ ።

ይ ፡ ሕ ፤ (ለለ ፡ ምዕራፉ ።)

በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ። (ሠለስተ ፡ ጊዜ ።)

፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ዘኀለየ ፡ በልቡ ፡ ኑፋቄ ፡ ይትጋነይ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ነውረ ፡ ኅሊና ፡ ዘቦ ፡ ኢይቅረብ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ዘወደቀ ፡ በኀጢአት ፡ ኢይርሳዕ ፥ እስመ ፡ ዘኢይትረሳዕ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ድውየ ፡ ኅሊና ፡ ዘቦ ፥ ኢይቅረብ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ሥኡብ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ይትገሐሥ ።

## የጌታ ፡ ቅዳሴ ፨

፩ ፤ ጌታችንና ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፥ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከማረጉ ፡ በፊት ፥ ለሐዋርያት ፡ ከነገራቸው ፡ ከመጽሐፈ ፡ ኪዳን ። የጸጋው ፡ በረከት ፥ የረድኤቱም ፡ ሀብት ፡ በርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በአባ ፡ እገሌ ፡ በኹላችንም ፡ ላይ ፡ ይኑር ፥ ለዘላለሙ ፤ አሜን ።

፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ልቡናችኹ ፡ በሰማይ ፡ ይኑር ።

ይ ፡ ሕ ፤ አዎን ፥ ልቡናችን ፡ በሰማይ ፡ ይኑር ። ስለ ፡ ስምኽ ፡ አጽናን ፥ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ የተዘጋጀንም ፡ አድርገን ።

፫ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ከወንድሙ ፡ ጋራ ፡ የተጣላ ፡ ቢኖር ፡ ይተውለት ።

ይ ፡ ሕ ፤ (በየምዕራፉ ።) አምላካችን ፡ ሆይ ፤ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይኹን ። (ሦስት ፡ ጊዜ ።)

፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በልቡ ፡ መጠራጠርን ፡ ያሰበ ፡ ቢኖር ፥ ይመን ።

ይ ፡ ሕ ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፤ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይኹን ።

፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ የሐሳብ ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ቢኖር ፥ አይቅረብ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፤ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይኹን ።

፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ በኀጢአት ፡ የወደቀ ፡ ቢኖር ፥ አይርሳ ፤ የማይረሳ ፡ ነውና ።

ይ ፡ ሕ ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፤ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይኹን ።

፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ሐሳቡ ፡ ድውይ ፡ የኾነ ፡ ቢኖር ፥ አይቅረብ ።

ይ ፡ ሕ ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፤ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይኹን ።

፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ ኀጢአትን ፡ የሚሠራ ፡ ንጹሕም ፡ ያልኾነ ፡ ቢኖር ፥ ይወገድ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ነኪር ፡ እምትእዛዙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ይትከላዕ ።

ይ ፡ ሕ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፥ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ።

፲ ፤ ይ ፡ ዲ ፤ እመቦ ፡ ዘያስተሐቅር ፡ ነቢያተ ፥ ያግሕሥ ፡ ርእሶ ፡ እመዓተ ፡ ዋሕድ ፡ ወያድኅን ፡ ነፍሶ ።

፲፩ ፤ መስቀለ ፡ ኢይግፋዕ ፡ ወይጐየይ ፡ እመዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ዘይሬእየነ ፡ ብነ ፡ አብ ፡ ብርሃን ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ ወመላእክቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ይሔውጹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፪ ፤ ነጽሩ ፡ ነፍሰክሙ ፡ ወአንጽሑ ፡ ነፍስተክሙ ፤ ወለቢጽክሙሂ ፡ ኢትዝክሩ ፡ አበሳሁ ፤ ርእዩ ፡ ከመ ፡ መኑሂ ፡ ኢየሀሉ ፡ በመዓት ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ።

፲፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይሬኢ ፤ አልዕሉ ፡ አልባቢክሙ ፤ ንቅረብ ፡ ለመድኀኒተ ፡ ሕይወት ፡ ወቅድሳት ፡ በጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንንሣእ ፡ ዘተውህበ ፡ ለነ ፡ ጸጋ ።

(ወደ ፡ ገጽ ፡ 34 ፡ ይመለሷል ።)

## መልክአ ፡ ቍርባን ✤

ይ ፡ ካ ፤ ሰላም ፡ ለኪ ፥ እንዘ ፡ ንሰግድ ፡ ንብለኪ ፥ ማርያም ፡ እምነ ፥ ናስተበቍዓኪ ፤ እምአርዌ ፡ ነዓዊ ፡ ተማሐጸነብኪ ፤ በእንተ ፡ ሃና ፡ እምኪ ፡ ወኢያቄም ፡ አቡኪ ፥ ማኅበረነ ፡ ዮም ፡ ድንግል ፡ ባርኪ ።

እግዚኦ ፡ ሰላመከ ፡ ሀባ ፡ ለሀገር ፥ ጽድቀከኒ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። አግርር ፡ ፀሩ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሃ ፤ ዕቀብ ፡ ሕዝባ ፡ ወሰራዊታ ፡ ለሀገሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ።

(ወደ ፡ ገጽ ፡ 46 ፡ ይመለሷል ።)

ይ፡ ሕ፤ አምላካችን፡ ሆይ፤ እንደ፡ ቸርነትኽ፡ ነው፡ እንጂ፥ እንደ፡ በደላችን፡ አይኹን ።

፱፤ ይ፡ ዲ፤ ከኢየሱስ፡ ትእዛዝ፡ ልዩ፡ የኾነ፡ ቢኖር፥ ይከልከል ።

ይ፡ ሕ፤ አምላካችን፡ ሆይ፤ እንደ፡ ቸርነትኽ፡ ነው፡ እንጂ፥ እንደ፡ በደላችን፡ አይኹን ።

፲፤ ይ፡ ዲ፤ ነቢያትን፡ የሚያቃልል፡ ቢኖር፥ ከዋሕድ፡ (ከወልድ)፡ መዓት፡ ራሱን፡ ያርቅ፥ ነፍሱንም፡ ያድን ።

፲፩፤ መስቀልን፡ አይበድል፤ ከእግዚአብሔርም፡ መዓት፡ ይራቅ ። የሚያየን፡ ብርሃን፡ አብ፡ ከልጁ፡ ጋራ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንን፡ ከሚጎበኙ፡ ከቅዱሳን፡ መላእክትም፡ ጋራ፡ አለና ።

፲፪፤ ነፍሳችኹን፡ ተመልከቱ፥ ሰውነታችኹንም፡ ንጹሕ፡ አድርጉ፤ የባልንጀራችኹንም፡ በደል፡ አታስቡ፤ ማንም፡ ከወንድሙ፡ ጋራ፡ በቍጣ፡ እንዳይኖር፡ አስተውሉ ።

፲፫፤ እግዚአብሔር፡ ያያል፤ ልቡናችኹን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጉ ። ወደ፡ ሕይወት፡ መድኀኒት፡ እንቅረብ፤ ጸጋ፡ ኹኖ፡ የተሰጠንንም፡ ሥጋውንና፡ ደሙን፡ በእግዚአብሔር፡ ጥበብ፡ እንቀበል ።

(ወደ፡ ገጽ፡ 35፡ ይመለሷል ።)

## መልክአ፡ ቍርባን ✥

ይ፡ ካ፤ እናታችን፡ ማርያም፡ ሆይ፤ ሰላም፡ ላንቺ፡ ይኹን፡ እያልን፡ እንሰግድልሻለን፤ ከዐዳኝ፡ አውሬ፡ ታድኚን፡ ዘንድ፡ ተማጽነንብሻል፥ ስለናትሽ፡ ስለ፡ ሃና፡ ብለሽ፤ ስላባትሽ፡ ስለ፡ ኢያቄም፡ ብለሽ፥ ድንግል፥ ማኅበራችንን፡ ዛሬ፡ ባርኪልን ።

አቤቱ፡ ጌታ፡ ሆይ፤ ለሀገራችን፡ ሰላምኽን፡ ስጣት፤ ጽድቅኽንም፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዐድላት ። የሀገራችን፥ የኢትዮጵያ፡ ጠላቶችን፡ ከእግሮቿ፡ በታች፡ አስገዛላት፤ ሕዝቧንና፡ ሰራዊቷን፡ ጠብቃቸው ።

(ወደ፡ ገጽ፡ 47፡ ይመለሷል ።)

| ምስባካት ፡ ዘበዓላት ፤ | የበዓላት ፡ ምስባኮች ፤ |
|---|---|
| ፩ ፡ ዘልደት ፤ | ፩ ፡ የልደት ፤ |
| ነገሥተ ፡ ተርሴስ ፡ ወደስያት ፡ አምኃ ፡ ያበውኡ ።<br>ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዐረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ።<br>ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ።<br>መዝ. ፡ ፸፩(፸፪)፥ ፲ ። | የተርሴስና ፡ የደሴቶች ፡ ነገሥታት ፡ ስጦታን ፡ ያመጣሉ ፤<br>የዐረብና ፡ የሳባ ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ያቀርባሉ ።<br>ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ይሰግዱለታል ።<br>መዝ. ፡ ፸፩(፸፪)፥ ፲ ። |
| ፪ ፡ ዘልደት ፤ | ፪ ፡ የልደት ፤ |
| የሐዩ ፡ ወይውህብዎ ፡ እምወርቀ ፡ ዐረብ ፤<br>ወዘልፈ ፡ ይጼልዩ ፡ በእንቲኣሁ ።<br>ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይድኅርዎ ።<br>መዝ. ፡ ፸፩(፸፪)፥ ፲፭ ። | ርሱ ፡ ይኖራል ፥ ከዐረብም ፡ ወርቅ ፡ ይሰጡታል ፤<br>ኹል ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይጸልያሉ ፤<br>ዘወትርም ፡ ይባርኩታል ።<br>መዝ. ፡ ፸፩(፸፪)፥ ፲፭ ። |
| ፫ ፡ ዘትንሣኤ ፤ | ፫ ፡ የትንሣኤ ፤ |
| ወተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ዘንቃህ ፡ እምንዋም ።<br>ወከመ ፡ ኀያል ፡ ወኅዳገ ፡ ወይን ።<br>ወቀተለ ፡ ፀሮ ፡ በድኅሬሁ ።<br>መዝ. ፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፭ ። | እግዚአብሔርም ፥ ከንቅልፍ ፡ እንደሚነቃ ፡ ተነሣ ፤<br>የወይን ፡ ስካር ፡ እንደ ፡ ተወው ፡ እንደ ፡ ኀያልም ፡ ሰው ።<br>ጠላቶቹንም ፡ በኋላቸው ፡ መታ ፤<br>መዝ. ፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፭ ። |
| ፬ ፡ ዘጸሎተ ፡ ኀሙስ ፤ | ፬ ፡ የጸሎተ ፡ ኀሙስ ፤ |
| ወሠራዕከ ፡ ማእደ ፡ በቅድሜየ ።<br>በአንጻሪሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩኒ ።<br>ወአጽሐድከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ ።<br>መዝ. ፡ ፳፪ (፳፫)፥ ፭ ። | በፊቴ ፡ ገበታን ፡ አዘጋጀኽልኝ ፤<br>በጠላቶቼ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤<br>ራሴን ፡ በዘይት ፡ ቀባኽ ፥<br>መዝ. ፡ ፳፪ (፳፫)፥ ፭ ። |
| ፭ ፡ ዘነገሥት ፤ | ፭ ፡ የነገሥት ፤ |
| እግዚኦ ፡ በኀይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሥ ።<br>ዘብዙኅ ፡ ይትሐሠይ ፡ በአድኅኖትከ ።<br>ፍትወተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሀብኮ ።<br>መዝ. ፡ ፳(፳፩)፥ ፩ ። | አቤቱ ፥ በኀይልኽ ፡ ንጉሥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤<br>በማዳንኽ ፡ እጅግ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋል ።<br>የልቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠኸው ።<br>መዝ. ፡ ፳(፳፩)፥ ፩ ። |
| ፮ ፡ ዘመላእክት ፤ | ፮ ፡ የመላእክት ፤ |
| ይትዐየን ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐውዶሙ ፥<br>ለእለ ፡ ይፈርህዎ ፤ ወያድኅኖሙ ።<br>ጠዐሙ ፡ ወታእምሩ ፡ ከመ ፡ ኄር ፡ እግዚአብሔር ።<br>መዝ. ፡ ፴፫(፴፬)፥ ፯ ። | የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በሚፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ዙሪያ ፡ ይሰፍራል ፤ ያድናቸውማል ።<br>እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅመሱ ፥ እዩም ።<br>መዝ. ፡ ፴፫(፴፬)፥ ፯ ። |

**፯፡ ዘማርያም፤**

እስመ፡ ኀረያ፡ እግዚአብሔር፡ ለጽዮን።
ወአብደራ፡ ከመ፡ ትኩኖ፡ ማኀደሮ።
ዛቲ፡ ይእቲ፡ ምዕራፍየ፡ ለዓለም።
መዝ.፡ ፻፴፩(፻፴፪)፥ ፲፫።

**፯፡ የማርያም፤**

እግዚአብሔር፡ ጽዮንን፡ መርጧታልና፥
ማደሪያውም፡ ትኾነው፡ ዘንድ፡ ወዷታልና፤
እንዲህ፡ ብሎ፡— ይህች፡ ለዘላለም፡ ማረፊያዬ፡ ናት፤
መዝ.፡ ፻፴፩ (፻፴፪)፥ ፲፫።

**፰፡ ዘመላእክት፤**

በቅድመ፡ መላእክቲከ፡ እዜምር፡ ለከ።
ወእሰግድ፡ ውስተ፡ ጽርሐ፡ መቅደስከ።
ወእገኒ፡ ለስምከ።
መዝ.፡ ፻፴፯(፻፴፰)፥ ፩።

**፰፡ የመላእክት፤**

በመላእክት፡ ፊት፡ እዘምርልኻለኹ።
ወደ፡ ቅዱስ፡ መቅደስኽ፡ እሰግዳለኹ፤
ስለ፡ ምሕረትኽና፡ ስለ፡ እውነትኽ፡ ስምኽንም፡ አመሰግናለኹ።
መዝ.፡ ፻፴፯(፻፴፰)፥ ፩።

**፱፡ ዘማርያም፤**

ወትቀውም፡ ንግሥት፡ በየማንከ።
በአልባሰ፡ ወርቅ፡ ዑጽፍት፡ ወሑብርት።
ስምዒ፡ ወለትየ፥ ወርእዪ፤ ወአጽምዒ፡ እዝነኪ።
መዝ.፡ ፵፬(፵፭)፥ ፱።

**፱፡ የማርያም፤**

በወርቅ፡ ልብስ፡ ተጐናጽፋና፡ ተሸፋፍና፥
ንግሥቲቱ፡ በቀኝኽ፡ ትቆማለች።
ልጄ፡ ሆይ፤ ስሚ፥ እዪ፤ ዦሮሽንም፡ አዘንብዪ።
መዝ.፡ ፵፬(፵፭)፥ ፱።

**፲፡ ዘጥምቀት፤**

ባሕርኒ፡ ርእየት፡ ወጐየት፤
ወዮርዳኖስኒ፡ ገብአ፡ ድኅሬሁ።
አድባር፡ አንፈርዐጹ፡ ከመ፡ ሐራጊት፤
መዝ.፡ ፲፫(፲፬)፥ ፫።

**፲፡ የጥምቀት፤**

ባሕር፡ አየች፥ ሸሸችም፤
ዮርዳኖስም፡ ወደ፡ ኋላው፡ ተመለሰ።
ተራሮች፡ እንደ፡ ኮርማዎች፡ ዘለሉ፤
መዝ.፡ ፲፫(፲፬)፥ ፫።

**፲፩፡ ዘጥምቀት፤**

ርእዩከ፡ ማያት፡ እግዚኦ።
ርእዩከ፡ ማያት፤ ወፈርሁ።
ደንገፁ፡ ቀላያተ፡ ማያት፤ ወደምፁ፡ ማያቲሆሙ።
መዝ.፡ ፸፮(፸፯)፥ ፲፮።

**፲፩፡ የጥምቀት፤**

አቤቱ፥ ውሆች፡ አዩኽ፥
ውሆችም፡ አይተውኽ፡ ፈሩ፤
ጥልቆች፡ ተነዋወጡ፥ ውሆችም፡ ጮኹ።
መዝ.፡ ፸፮(፸፯)፥ ፲፮።

**፲፪፡ ዘትንሣኤ፤**

ይትነሣእ፡ እግዚአብሔር፥ ወይዘረዉ፡ ፀሩ።
ወይጕየዩ፡ ጸላእቱ፡ እምቅድመ፡ ገጹ።
ከመ፡ የኀልቅ፡ ጢስ፡ ከማሁ፡ የኀልቁ።
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፩።

**፲፪፡ የትንሣኤ፤**

እግዚአብሔር፡ ይነሣ፥ ጠላቶቹም፡ ይበተኑ፤
የሚጠሉትም፡ ከፊቱ፡ ይሸሹ።
ጢስ፡ እንደሚበን፡ እንዲሁ፡ ይብነኑ፤
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፩።

**፲፫፡ ዘልደት፤**

በከመ፡ ሰማዕነ፡ ከማሁ፡ ርኢነ።
በሀገረ፡ እግዚአ፡ ኀያላን፥ በሀገረ፡ አምላክነ።
እግዚአብሔር፡ ሣረራ፡ ለዓለም።
መዝ.፡ ፵፯(፵፰)፥ ፰።

**፲፫፡ የልደት፤**

እንደ፡ ሰማን፡ እንዲሁ፡ አየን።
በሰራዊት፡ ጌታ፡ ከተማ፥ ባምላካችን፡ ከተማ፤
እግዚአብሔር፡ ለዘላለም፡ ያጸናታል።
መዝ.፡ ፵፯(፵፰)፥ ፰።

| | |
|---|---|
| ፲፬ ፡ ዘዐውደ ፡ ዓመት ፤ | ፲፬ ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፤ |
| ወትባርክ ፡ አክሊለ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረትከ ።<br>ወይጸግቡ ፡ ጠላተ ፡ ገዳም ።<br>ወይረውዩ ፡ አድባረ ፡ በድው ።<br>መዝ. ፡ ፷፬(፷፭)፥ ፲፩ ። | በቸርነትኽ ፡ ዓመትን ፡ ታቀዳጃለኽ ፤<br>ምድረ ፡ በዳውም ፡ ስብን ፡ ይጠግባሉ ።<br>የምድረ ፡ በዳ ፡ ተራሮች ፡ ይረካሉ ፤<br>መዝ. ፡ ፷፬(፷፭)፥ ፲፩ ። |
| ፲፭ ፡ ዘዐውደ ፡ ዓመት ፤ | ፲፭ ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፤ |
| ሣህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልአ ፡ ምድረ ።<br>ወበቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንዓ ፡ ሰማያት ።<br>ወእምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ኀይሎሙ ።<br>መዝ. ፡ ፻፪(፻፫)፥ ፳ ። | የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ምድርን ፡ ሞላች ።<br>በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰማዮች ፡ ጸኑ ፤<br>ሰራዊታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ባፉ ፡ እስትንፋስ ፤<br>መዝ. ፡ ፻፪(፻፫)፥ ፳ ። |
| ፲፮ ፡ ዘቅዱሳን ፤ | ፲፮ ፡ የቅዱሳን ፤ |
| እስመ ፡ መምህረ ፡ ሕግ ፡ ይውህብ ፡ በረከተ ።<br>ወየሐውር ፡ እምኀይል ፡ ውስተ ፡ ኀይል ።<br>ወያስተርኢ ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ በጽዮን ።<br>መዝ. ፡ ፹፫(፹፬)፥ ፯ ። | የሕግ ፡ መምህር ፡ በረከትን ፡ ይሰጣልና ፤<br>ከኀይል ፡ ወደ ፡ ኀይል ፡ ይኼዳሉ ፤<br>የአማልክት ፡ አምላክ ፡ በጽዮን ፡ ይታያል ።<br>መዝ. ፡ ፹፫(፹፬)፥ ፯ ። |
| ፲፯ ፡ ዘዕርገት ፤ | ፲፯ ፡ የዕርገት ፤ |
| ዐርገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይባቤ ።<br>ወእግዚእነ ፡ በቃለ ፡ ቀርን ።<br>ዘምሩ ፡ ለአምላክነ ፥ ዘምሩ ።<br>መዝ. ፡ ፵፮(፵፯)፥ ፭ ። | አምላክ ፡ በዕልልታ ፥<br>እግዚአብሔር ፡ በመለከት ፡ ድምፅ ፡ ዐረገ ።<br>ዘምሩ ፥ ላምላካችን ፡ ዘምሩ ፤<br>መዝ. ፡ ፵፮(፵፰)፥ ፭ ። |
| ፲፰ ፡ ዘደብረ ፡ ታቦር ፤ | ፲፰ ፡ የደብረ ፡ ታቦር ፤ |
| ታቦር ፡ ወአርሞንኤም ፡ በስመ ፡ ዚኣከ ፡ ይትፌሥሑ ።<br>ወይሴብሑ ፡ ለስምከ ።<br>መዝራዕትከ ፡ ምሰለ ፡ ኀይል ።<br>መዝ. ፡ ፹፰(፹፱)፥ ፲፪ ። | ታቦርና ፡ አርሞንኤም ፡ በስምኽ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤<br>ክንድኽ ፡ ከኀይልኽ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤<br>እጅኽ ፡ በረታች ፥ ቀኝኽም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።<br>መዝ. ፡ ፹፰(፹፱)፥ ፲፪ ። |
| ፲፱ ፡ ዘሐዋርያት ፤ | ፲፱ ፡ የሐዋርያት ፤ |
| አልቦ ፡ ነገር ፡ ወአልቦ ፡ ነቢብ ፥ ዘኢተሰምዐ ፡ ቃሎሙ ።<br>ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወፅአ ፡ ነገሮሙ ።<br>ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ በጽሐ ፡ ነቢቦሙ ።<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፫ ። | ነገር ፡ የለም ፥ መናገርም ፡ የለም ፤ ድምፃቸውም ፡ አይሰማም ።<br>ድምፃቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ቃላቸውም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ወጣ ።<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፫ ። |
| ፳ ፡ ዘመላእክት ፤ | ፳ ፡ የመላእክት ፤ |
| ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ።<br>ወለእለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ነደ ፡ እሳት ።<br>ሣረራ ፡ ለምድር ፡ ወአጽንዓ ።<br>መዝ. ፡ ፻፫(፻፬)፥ ፬ ። | መላእክቱን ፡ መንፈስ ፡ የሚያደርግ ፥<br>አገልጋዮቹንም ፡ የሳት ፡ ነበልባል ።<br>ምድርን ፡ በመሠረቷ ፡ ላይ ፡ መሠረታት ።<br>መዝ. ፡ ፻፫(፻፬)፥ ፬ ። |

| | |
|---|---|
| **፳፩፡ ዘሰማዕታት፤** | **፳፩፡ የሰማዕታት፤** |
| በቀለ፡ ደሞሙ፡ ለአግብርቲከ፡ ዘተክዕወ ።<br>ይባእ፡ ቅድሜከ፡ ገዓሮሙ፡ ለሙቁሐን፤<br>ወበከመ፡ ዕበየ፡ መዝራዕትከ፡<br>መዝ.፡ ፸፰(፸፱)፥ ፲ ። | የፈሰሰውን፡ የባሮችኽን፡ ደም፡ ተበቀል፤<br>የስረኞች፡ ጩኸት፡ ወደ፡ ፊትኽ፡ ይግባ፤<br>እንደ፡ ክንድኽም፡ ታላቅነት፡<br>መዝ.፡ ፸፰(፸፱)፥ ፲ ። |
| **፳፪፡ ዘጻድቃን፤** | **፳፪፡ የጻድቃን፤** |
| ዝክረ፡ ጻድቅ፡ ለዓለም፡ ይሄሉ ።<br>ወኢይፈርህ፡ እምነገር፡ እኩይ ።<br>ጥቡዕ፡ ልቡ፡ ለተወክሎ፡ በእግዚአብሔር ።<br>መዝ.፡ ፻፲፩(፻፲፪)፥ ፮ ። | የጻድቅ፡ መታሰቢያ፡ ለዘላለም፡ ይኖራል ።<br>ከክፉ፡ ነገር፡ አይፈራም፤<br>በእግዚአብሔር፡ ለመታመን፡ ልቡ፡ የጸና፡ ነው ።<br>መዝ.፡ ፻፲፩(፻፲፪)፥ ፮ ። |
| **፳፫፡ ዘሰማዕታት፤** | **፳፫፡ የሰማዕታት፤** |
| ወይርአዩ፡ አሕዛብ፡ በቅድመ፡ አዕይንቲነ ።<br>በቀለ፡ ደሞሙ፡ ለአግብርቲከ፡ ዘተክዕወ ።<br>ይባእ፡ ቅድሜከ፡ ገዓሮሙ፡ ለሙቁሐን፤<br>መዝ.፡ ፸፰(፸፱)፥ ፲ ። | የፈሰሰውን፡ የባሮችኽን፡ ደም፡ በቀል ።<br>በዐይኖቻችን፡ ፊት፡ አሕዛብ፡ ይወቁ ።<br>የስረኞቹ፡ ጩኸት፡ ወደ፡ ፊትኽ፡ ይግባ፤<br>መዝ.፡ ፸፰(፸፱)፥ ፲ ። |
| **፳፬፡ ዘመስቀል፤** | **፳፬፡ የመስቀል፤** |
| ወወሀብኮሙ፡ ትእምርተ፡ ለእለ፡ ይፈርሁከ ።<br>ከመ፡ ያምሥጡ፡ እምገጸ፡ ቀስት፤<br>ወይድኅኑ፡ ፍቁራኒከ ።<br>መዝ.፡ ፶፱(፷)፥ ፬ ። | ከቀስት፡ ፊት፡ ያመልጡ፡ ዘንድ፥<br>ለሚፈሩኽ፡ ምልክትን፡ ሰጠኻቸው፤<br>ወዳጆችኽ፡ እንዲድኑ ።<br>መዝ.፡ ፶፱(፷)፥ ፬ ። |
| **፳፭፡ ዘመላእክት፤** | **፳፭፡ የመላእክት፤** |
| እስመ፡ ለመላእክቲሁ፡ ይኤዝዞሙ፡ በእንቲአከ ።<br>ከመ፡ ይዕቀቡከ፡ በኵሉ፡ ፍናዊከ፤<br>ወበእደዊሆሙ፡ ያነሥኡከ፡<br>መዝ.፡ ፺(፺፩)፥ ፲፩ ። | በመንገድኽ፡ ኹሉ፡ ይጠብቁኽ፡ ዘንድ፥<br>መላእክቱን፡ ስላንተ፡ ያዛቸዋልና፥<br>እግርኽም፡ በድንጋይ፡ እንዳትሰናከል፡<br>መዝ.፡ ፺(፺፩)፥ ፲፩ ። |
| **፳፮፡ ዘጥምቀት፤** | **፳፮፡ የጥምቀት፤** |
| ወመንፈስከ፡ ቅዱሰ፡ ኢታውፅእ፡ እምላዕሌየ ።<br>ዕስየኒ፡ ፍሥሓ፡ ወአድኅኖተከ ።<br>ወበመንፈስ፡ ዐዚዝ፡ አጽንዐኒ፡<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፩ ። | ቅዱስ፡ መንፈስኽንም፡ ከኔ፡ ላይ፡ አትውሰድብኝ ።<br>የማዳንኽን፡ ደስታ፡ ስጠኝ፥<br>በእሽታ፡ መንፈስም፡ ደግፈኝ ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፩ ። |
| **፳፯፡ ዘኪዳነ፡ ምሕረት፤** | **፳፯፡ የኪዳነ፡ ምሕረት፤** |
| እስመ፡ ትቤ፡ ለዓለም፡ አሐንጽ፡ ምሕረተ ።<br>በሰማይ፡ ጸንዐ፡ ጽድቅከ ።<br>ኪዳነ፡ ተካየድኩ፡ ምስለ፡ ኅሩያንየ ።<br>መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፪ ። | እንዲህ፡ ብለኻልና ፦ ምሕረት፡ ለዘላለም፡<br>ይመሠረታል ።<br>እውነትኽም፡ በሰማይ፡ ይጸናል ።<br>ከመረጥኹት፡ ጋራ፡ ቃል፡ ኪዳኔን፡ አደረግኹ፤<br>መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፪ ። |

| | |
|---|---|
| ፳፰ ፡ ዘመድኃኔ ፡ ዓለም ፤ | ፳፰ ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፤ |
| እግዚአብሔርሰ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።<br>ወገብረ ፡ መድኀኒተ ፡ በማእከለ ፡ ምድር ።<br>አንተ ፡ አጽናዕካ ፡ ለባሕር ፡ በኀይልከ ።<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፪ ። | እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከዓለም ፡ አስቀድሞ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤<br>በምድርም ፡ መካከል ፡ መድኀኒትን ፡ አደረገ ።<br>አንተ ፡ ባሕርን ፡ በኀይልኽ ፡ አጸናኻት ፤<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፪ ። |
| ፳፱ | ፳፱ |
| አፉሁ ፡ ለጻድቅ ፡ ይትሜሀር ፡ ጥበበ ።<br>ወልሳኑ ፡ ይነብብ ፡ ጽድቀ ።<br>ወሕገ ፡ አምላኩ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ።<br>መዝ. ፡ ፴፮(፴፯)፥ ፴ ። | የጻድቅ ፡ አፍ ፡ ጥበብን ፡ ያስተምራል ፤<br>አንደበቱም ፡ ፍርድን ፡ ይናገራል ።<br>ያምላኩ ፡ ሕግ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።<br>መዝ. ፡ ፴፮(፴፯)፥ ፴ ። |
| ፴ | ፴ |
| ክቡር ፡ ሞቱ ፡ ለጻድቅ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።<br>እግዚኦ ፥ አነ ፡ ገብርከ ።<br>ገብርከ ፡ ወልደ ፡ አመትከ ።<br>መዝ. ፡ ፻፲፭(፻፲፮)፥ ፮ ። | የቅዱሳኑ ፡ ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የከበረ ፡ ነው ።<br>አቤቱ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ነኝ ፤<br>ባሪያኽ ፡ ነኝ ፥ የሴት ፡ ባሪያኽም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ።<br>መዝ. ፡ ፻፲፭(፻፲፮)፥ ፮ ። |
| ፴፩ ፡ ዘሆሳዕና ፤ | ፴፩ ፡ የሆሳዕና ፤ |
| እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሎከ ፡ ስብሐት ፡ በእንተ ፡ ጸላኢ ።<br>ከመ ፡ ትንሥቶ ፡ ለጸላኢ ወለገፋዒ ።<br>መዝ. ፡ ፰ ፥ ፪ ። | ከሕፃናትና ፡ ከሚጠቡ ፡ ልጆች ፡ አፍ ፡ ምስጋናን ፡ አዘጋጀኽ ፡ ስለ ፡ ጠላትኽ ፥<br>ጠላትንና ፡ ቂመኛን ፡ ለማጥፋት ።<br>መዝ. ፡ ፰ ፥ ፪ ። |
| ፴፪ | ፴፪ |
| ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።<br>ነገሥተ ፡ ምድር ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።<br>ወዘምሩ ፡ ለአምላክነ ።<br>መዝ. ፡ ፷፯(፷፰)፥ ፴፩ ። | ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ።<br>የምድር ፡ ነገሥታት ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀኙ ፥<br>ለጌታም ፡ ዘምሩ ።<br>መዝ. ፡ ፷፯(፷፰)፥ ፴፩ ። |
| ፴፫ | ፴፫ |
| ወውእቱሰ ፡ ከመ ፡ መርዓዊ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምጽርሑ ።<br>ይትፌሣሕ ፡ ከመ ፡ ያርብሕ ፡ ዘይሜርድ ፡ ፍኖቶ ።<br>እምአጽናፈ ፡ ሰማይ ፡ ሙፃኡ ።<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፭ ። | ርሱም ፡ እንደ ፡ ሙሽራ ፡ ከዕልፍኙ ፡ ይወጣል ፤<br>እንደ ፡ ዐርበኛ ፡ በመንገዱ ፡ ለመሮጥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።<br>አወጣጡ ፡ ከሰማያት ፡ ዳርቻ ፡ ነው ፤<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፭ ። |

| ምስባካት ፡ ዘሰንበታት ፤ | የሰንበት ፡ ምስባኮች ፤ |
|---|---|
| **መስከረም ፤** | |
| ፩) ሣህል ፡ ወርትዕ ፡ ተራከባ ።<br>ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ተሳዐማ ።<br>ርትዕሰ ፡ እምድር ፡ ሠረጸት ።<br>መዝ. ፡ ፹፬(፹፭)፥ ፲ ። | ፩) ምሕረትና ፡ እውነት ፡ ተገናኙ ፤<br>ጽድቅና ፡ ሰላም ፡ ተሰማሙ ።<br>እውነት ፡ ከምድር ፡ በቀለች ፥<br>መዝ. ፡ ፹፬(፹፭)፥ ፲ ። |
| ፪) ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።<br>እስመ ፡ ተዘከረ ፡ ዘይትኃሠሥ ፡ ደሞሙ ።<br>ወኢረስዐ ፡ ዐውያቶሙ ፡ ለነዳያን ።<br>መዝ. ፡ ፱፥ ፲፩–፲፪ ። | ፪) ባሕዛብም ፡ መካከል ፡ አደራረጉን ፡ ንገሩ ፤<br>ደማቸውን ፡ የሚመራመር ፡ ርሱ ፡ ዐስቧልና ።<br>የድኾችንም ፡ ጩኸት ፡ አልረሳምና ።<br>መዝ. ፡ ፱፥ ፲፩–፲፪ ። |
| ፫) ምድርኒ ፡ ወሀበት ፡ ፍሬሃ ።<br>ወይባርከነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።<br>ወይባርከነ ፡ እግዚአብሔር ።<br>መዝ. ፡ ፷፮(፷፯)፥ ፮ ። | ፫) ምድር ፍሬዋን ሰጠች ፤<br>እግዚአብሔር ፡ አምላካችንም ፡ ይባርከናል ።<br>እግዚአብሔር ይባርከናል ፤<br>መዝ. ፡ ፷፮(፷፯)፥ ፮ ። |
| ፬) ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ዘአፍቀረ ።<br>ሐነጸ ፡ መቅደሶ ፡ በአርያም ።<br>ወሣረራ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ዘለዓለም ።<br>መዝ. ፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፰ ። | ፬) የወደደውን ፡ የጽዮንን ፡ ተራራ ።<br>መቅደሱን ፡ እንደ ፡ አርያም ፡ ሠራ ፤<br>ለዘላለምም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ መሠረታት ።<br>መዝ. ፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፰ ። |
| ፭) ወወሀብኮሙ ፡ ትእምርተ ፡ ለእለ ፡ ይፈርሁከ ።<br>ከመ ፡ ያምሥጡ ፡ እምገጸ ፡ ቀስት ።<br>ወይድኅኑ ፡ ፍቁራኒከ ።<br>መዝ. ፡ ፶፱(፷)፥ ፬ ። | ፭) ከቀስት ፡ ፊት ፡ ያመልጡ ፡ ዘንድ ፥ ለሚፈሩኽ ፡<br>ምልክትን ፡ ሰጠኻቸው ፤<br>ወዳጆችኽም ፡ እንዲድኑ ።<br>መዝ. ፡ ፶፱(፷)፥ ፬ ። |
| ፮) ወአጽንዖ ፡ እግዚኦ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘሠራዕከ ፡ ለነ ።<br>ውስተ ፡ ጽርሕከ ፡ ዘኢየሩሳሌም ።<br>ለከ ፡ ያመጽኡ ፡ ነገሥት ፡ አምኃ ።<br>መዝ. ፡ ፷፯(፷፰)፥ ፳፰ ። | ፮) አቤቱ ፥ ይህንም ፡ ለኛ ፡ የሠራኸውን ፡<br>አጽናው ።<br>በኢየሩሳሌም ፡ ስላለው ፡ መቅደስኽ ፡<br>ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ላንተ ፡ ያመጣሉ ።<br>መዝ. ፡ ፷፯(፷፰)፥ ፳፰ ። |
| **ጥቅምት ፤** | |
| ፯) አንተ ፡ ፈጠርከ ፡ ፀሐየ ፡ ወወርኀ ።<br>ወአንተ ፡ ገበርከ ፡ አድባረ ፡ ወምድረ ፡ ኲሎ ።<br>ክረምተ ፡ ወሐጋየ ፡ ዘአንተ ፡ ፈጠርከ ።<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፯ ። | ፯) አንተ ፡ ፀሐዩንና ፡ ጨረቃውን ፡ አዘጋጀኽ ።<br>አንተ ፡ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ሠራኽ ፤<br>በጋንም ፡ ክረምትንም ፡ አንተ ፡ አደረግኽ ።<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፯ ። |
| ፰) ፍሬ ፡ ጻማከ ፡ ተሴሰይ ።<br>ብፁዕ ፡ አንተ ፤ ወሠናይ ፡ ለከ ።<br>ብእሲትከ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ስሙር ፡ ውስተ ፡<br>ጽርሐ ፡ ቤትከ ።<br>መዝ. ፡ ፻፳፯(፻፳፰)፥ ፪ ። | ፰) የድካምኽን ፡ ፍሬ ፡ ትመገባለኽ ፤<br>ምስጉን ፡ ነኽ ፥ መልካምም ፡ ይኾንልኻል ።<br>ሚስትኽ ፡ በቤትኽ ፡ ዕልፍኝ ፡ ውስጥ ፡<br>እንደሚያፈራ ፡ ወይን ፡ ናት ፤<br>መዝ. ፡ ፻፳፯(፻፳፰)፥ ፪ ። |

| | |
|---|---|
| ፱) ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ንሕነ ።<br>ወሰብእሰ ፡ ከመ ፡ ሣዕር ፡ መዋዕሊሁ ።<br>ወከመ ፡ ጽጌ ፡ ገዳም ፡ ከማሁ ፡ ይፈሪ ።<br>መዝ. ፡ ፺፪(፺፫)፥ ፲፬ ። | ፱) አቤቱ፥ እኛ ፡ ዐፈር ፡ እንደኾን ፡ ዐስብ ።<br>ሰውስ ፡ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ነው ፤<br>እንደ ፡ ዱር ፡ አበባ ፡ እንዲሁ ፡ ያብባል ፤<br>መዝ. ፡ ፺፪(፺፫)፥ ፲፬ ። |
| ፲) ጻድቅሰ ፡ ከመ ፡ በቀልት ፡ ይፈሪ ።<br>ወይበዝኅ ፡ ከመ ፡ ዘግባ ፡ ዘሊባኖስ ።<br>ትኩላን ፡ እሙንቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።<br>መዝ. ፡ ፺፩(፺፪)፥ ፲፪ ። | ፲) ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ያፈራል ፤<br>እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባም ፡ ያድጋል ።<br>በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተተክለዋል ፤<br>መዝ. ፡ ፺፩(፺፪)፥ ፲፪ ። |
| ፲፩) ወይከውን ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡ ትክልት ፡ ኀበ ፡ ሙሓዘ ፡ ማይ ።<br>እንተ ፡ ትውህብ ፡ ፍሬሃ ፡ በበ ፡ ጊዜሃ ።<br>ወቈጽላኒ ፡ ኢይትነገፍ ።<br>መዝ. ፡ ፩፥ ፫ ። | ፲፩) ርሱም ፡ በውሀ ፡ ፈሳሾች ፡ ዳር ፡ እንደተተከለች፥<br>ፍሬዋን ፡ በየጊዜው ፡ እንደምትሰጥ፥<br>ቅጠሏም ፡ እንደማይረግፍ ፡ ዛፍ ፡ ይኾናል ፤<br>መዝ. ፡ ፩፥ ፫ ። |
| ፲፪) ዐጸደ ፡ ወይን ፡ አፍለስከ ፡ እምግብጽ ።<br>ሰደድከ ፡ አሕዛበ ፡ ወተከልከ ፡ ኪያሃ ።<br>ወጼሕከ ፡ ፍኖተ ፡ ቅድሜሃ ።<br>መዝ. ፡ ፸፱(፹)፥ ፰ ። | ፲፪) ከግብጽ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ አመጣኽ ።<br>አሕዛብን ፡ አባረርኽ፥ ርሷንም ፡ ተከልኽ ።<br>በፊቷም ፡ ስፍራን ፡ አዘጋጀኽ ፤<br>መዝ. ፡ ፸፱(፹)፥ ፰ ። |

ኅዳር ፤

| | |
|---|---|
| ፲፫) ኢትዝክር ፡ ለነ ፡ አበሳነ ፡ ዘትካት ።<br>ፍጡነ ፡ ይርከበነ ፡ ሣህልከ ፡ እግዚኦ ።<br>እስመ ፡ ተመንደብነ ፡ ፈድፋደ ።<br>መዝ. ፡ ፸፰(፹፱)፥ ፰ ። | ፲፫) የቀደመውን ፡ በደላችንን ፡ አታስብብን ፤<br>ምሕረትኽ ፡ በቶሎ ፡ ታግኘን፥<br>እጅግ ፡ ተቸግረናልና ።<br>መዝ. ፡ ፸፰(፹፱)፥ ፰ ። |
| ፲፬) ኵሎ ፡ ዘፈቀደ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ።<br>በሰማይኒ ፡ ወበምድርኒ ።<br>በባሕርኒ ፡ ወበኵሉ ፡ ቀላያት ።<br>መዝ. ፡ ፻፴፬(፻፴፭)፥ ፮–፯ ። | ፲፬) በሰማይና ፡ በምድር ፡ በባሕርና ፡ በጥልቆች ፡ ኹሉ፥<br>እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።<br>ከምድር ፡ ዳር ፡ ደመናትም ፡ ያወጣል ፤<br>መዝ. ፡ ፻፴፬(፻፴፭)፥ ፮–፯ ። |
| ፲፭) ቅረቡ ፡ ኀቤሁ ፤ ወያበርህ ፡ ለክሙ ።<br>ወኢይትኀፈር ፡ ገጽክሙ ።<br>ዝንቱ ፡ ነዳይ ፡ ጸርሐ ፤ ወእግዚአብሔር ፡ ሰምዖ ።<br>መዝ. ፡ ፴፫(፴፬)፥ ፭ ። | ፲፭) ወደ ፡ ርሱ ፡ ቅረቡ ፤ ያበራላችኹማል ።<br>ፊታችኹም ፡ አያፍርም ።<br>ይህ ፡ ችግረኛ ፡ ጮኸ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰማው ።<br>መዝ. ፡ ፴፫(፴፬)፥ ፭ ። |
| ፲፮) ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ታከብዱ ፡ ልበክሙ ።<br>ለምንት ፡ ታፈቅሩ ፡ ከንቶ ፤ ወተኀሡ ፡ ሐሰተ ።<br>አእምሩ ፡ ከመ ፡ ተሰብሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጻድቁ ።<br>መዝ. ፡ ፬፥ ፪ ። | ፲፮) እናንተ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ልባችኹን ፡ ታከብዳላችኹ ።<br>ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ለምን ፡ ትወዳላችኹ ፤ ሐሰትንም ፡ ለምን ፡ ትሻላችኹ ።<br>እግዚአብሔር ፡ በጻድቁ ፡ እንደተገለጠ ፡ ዕወቁ ።<br>መዝ. ፡ ፬፥ ፪ ። |
| ፲፯) ወለነዳያኒሃኒ ፡ ኣጸግቦሙ ፡ እክለ ።<br>ወለካህናቲሃኒ ፡ ኣለብሶሙ ፡ ሕይወተ ።<br>ወጻድቃኒሃኒ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ይትፌሥሑ ።<br>መዝ. ፡ ፻፴፩(፻፴፪)፥ ፲፭ ። | ፲፯) ድኾቿንም ፡ እንጀራ ፡ አጠግባለኹ ።<br>ካህናቶቿንም ፡ ደኅንነትን ፡ አለብሳቸዋለኹ ።<br>ቅዱሳኖቿም ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።<br>መዝ. ፡ ፻፴፩(፻፴፪)፥ ፲፭ ። |

## ታኅሣሥ፤

፲፰) ፈኑ፡ እዴከ፡ እምአርያም ።
አድኅነኒ፡ ወባልሐኒ፡ እማይ፡ ብዙኅ ።
ወእምእዴሆሙ፡ ለደቂቀ፡ ነኪር ።
መዝ.፡ ፻፵፫(፻፵፬)፥ ፯ ።

፲፰) እጅኽን፡ ከአርያም፡ ላክ ።
አድነኝም፡ ከብዙ፡ ውሆች፤
አፋቸውም፡ ምናምንን፡ ከሚናገር ።
መዝ.፡ ፻፵፫(፻፵፬)፥ ፯ ።

፲፱) ፈኑ፡ ብርሃነከ፡ ወጽድቀከ ። እማንቱ፡
ይምርሐኒ፡ ወይሰዳኒ፡ ደብረ፡ መቅደስከ ።
ወውስተ፡ አብያቲከ፡ እግዚኦ ።
መዝ.፡ ፵፪(፵፫)፥ ፫ ።

፲፱) ብርሃንኽንና፡ እውነትኽን፡ ላክ ።
እነርሱ፡ ይምሩኝ፤ ወደ፡ ቅድስናኽ፡ ተራራና፡
ወደ፡ ማደሪያኽ፡ ይውሰዱኝ ።
መዝ.፡ ፵፪(፵፫)፥ ፫ ።

፳) ኖላዊሆሙ፡ ለእስራኤል፡ አጽምዕ፤
ዘይርዕዮሙ፡ ከመ፡ አባግዐ፡ ዮሴፍ ።
ዘይነብር፡ ላዕለ፡ ኪሩቤል፡ አስተርአየ ።
መዝ.፡ ፸፱(፹)፥ ፩ ።

፳) ዮሴፍን፡ እንደ፡ መንጋ፡ የምትመራ፡
የእስራኤል፡ ጠባቂ፡ ሆይ፤ አድምጥ፤
በኪሩቤል፡ ላይ፡ የምትቀመጥ፥ ተገለጥ ።
መዝ.፡ ፸፱(፹)፥ ፩ ።

## ጥር፤

፳፩) ወአነሂ፡ በኵርየ፡ እሬስዮ ።
ወልዑል፡ ውእቱ፡ እምነገሥተ፡ ምድር ።
ወለዓለም፡ አዐቅብ፡ ሎቱ፡ ሣህልየ ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፳፯ ።

፳፩) እኔም፡ ደግሞ፡ በኵሬ፡ አደርገዋለኹ ።
ከምድር፡ ነገሥታትም፡ ከፍ፡ ይላል ።
ለዘላለምም፡ ምሕረቴን፡ ለርሱ፡ እጠብቃለኹ ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፳፯ ።

፳፪) ናሁ፡ ሰማዕናሁ፡ በኤፍራታ ።
ወረከብናሁ፡ ውስተ፡ ዖመ፡ ገዳም ።
ንበውእ፡ እንከሰ፡ ውስተ፡ አብያቲሁ፡
ለእግዚአብሔር ።
መዝ.፡ ፻፴፩(፻፴፪)፥ ፮ ።

፳፪) እነሆ፡ በኤፍራታ፡ ሰማነው፥
በዱር፡ ውስጥም፡ አገኘነው ።
ወደ፡ ማደሪያዎቹ፡ እንገባለን፤
መዝ.፡ ፻፴፩(፻፴፪)፥ ፮ ።

፳፫) እስመ፡ መምህረ፡ ሕግ፡ ይውህብ፡ በረከተ ።
ወየሐውር፡ እምኀይል፡ ውስተ፡ ኀይል ።
ወያስተርኢ፡ አምላከ፡ አማልክት፡ በጽዮን ።
መዝ.፡ ፹፫(፹፬)፥ ፯ ።

፳፫) የሕግ፡ መምህር፡ በረከትን፡ ይሰጣልና ።
ከኀይል፡ ወደ፡ ኀይል፡ ይኼዳሉ፤
ያማልክት፡ አምላክ፡ በጽዮን፡ ይታያል ።
መዝ.፡ ፹፫(፹፬)፥ ፯ ።

፳፬) እግዚአብሔር፡ እግዚእ፡ አስተርአየ፡ ለነ ።
ግበሩ፡ በዓለ፡ በትፍሥሕት፡ በኀበ፡ እለ፡
ያስተሐምምዋ ።
እስከ፡ አቅርንቲሁ፡ ለምሥዋዕ ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፯ ።

፳፬) እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ነው፤ ለኛም፡
በራልን ።
እስከ፡ መሠዊያው፡ ቀንዶች፡ ድረስ፡
የበዓሉን፡ መሥዋዕት፡ በገመድ፡ እሰሩት ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፯ ።

፳፭) በከመ፡ ሰማዕነ፡ ከማሁ፡ ርኢነ ።
በሀገረ፡ እግዚአ፡ ኀያላን፡ በሀገረ፡ አምላክነ ።
እግዚአብሔር፡ ሣረራ፡ ለዓለም ።
መዝ.፡ ፵፯(፵፰)፥ ፰ ።

፳፭) እንደ፡ ሰማን፡ እንዲሁ፡ አየን፥
በሰራዊት፡ ጌታ፡ ከተማ፥ ባምላካችንም፡ ከተማ፤
እግዚአብሔር፡ ለዘላለም፡ ያጸናታል ።
መዝ.፡ ፵፯(፵፰)፥ ፰ ።

፳፮) እግዚአብሔር፡ ስቡሕ፡ በምክረ፡ ቅዱሳን ።
ዐቢይ፡ ወግሩም፡ ዲበ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ዐውዱ ።
እግዚኦ፡ አምላከ፡ ኀያላን፡ መኑ፡ ከማከ ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፯ ።

፳፮) በቅዱሳን፡ ክብር፡ እግዚአብሔር፡ ክቡር፡ ነው ።
በዙሪያው፡ ባሉት፡ ኹሉ፡ ላይ፡ ታላቅና፡ ግሩም፡ ነው ።
አቤቱ፡ የሰራዊት፡ አምላክ፥ እንዳንተ፡ ያለ፡ ማን፡ ነው ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፯ ።

፳፯) ትሴብሐ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብሔር ።
ወሰብሒዮ ፡ ለአምላክኪ ፡ ጽዮን ።
እስመ ፡ አጽንዐ ፡ መናሥግተ ፡ ኆኃትኪ ።
መዝ. ፡ ፻፵፯(፻፵፰)፥ ፩ ።

፳፯) ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኚ፤
ጽዮንም ፡ ሆይ፤ ላምላክሽ ፡ ዕልል ፡ በዪ፤
የደጆችሽን ፡ መወርወሪያ ፡ አጽንቷልና፤
መዝ. ፡ ፻፵፯(፻፵፰)፥ ፩ ።

የካቲት፤

፳፰) አግረረ ፡ ለነ ፡ አሕዛበ ፡ ወሕዝበ ፡ ታሕተ ፡ እገሪነ ።
ወኀረየነ ፡ ሎቱ ፡ ለርስቱ ።
ሥኖ ፡ ለያዕቆብ ፡ ዘአፍቀረ ።
መዝ. ፡ ፵፮(፵፯)፥ ፬ ።

፳፰) አሕዛብን ፡ ከእግራችን ፡ በታች ፡ አስገዛልን ።
ለርስቱ ፡ እኛን ፡ መረጠን፥
የወደደውን ፡ የያዕቆብን ፡ ውበት ።
መዝ. ፡ ፵፮(፵፯)፥ ፬ ።

ዘዐቢይ ፡ ጾም፤

፳፱) ተቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሀት ።
ወተሐሠዩ ፡ ሎቱ ፡ በረዓድ ።
አጽንዕዋ ፡ ለጥበብ ፡ ከመ ፡ ኢይትመዐዕ ፡ እግዚአብሔር ።
መዝ. ፡ ፪፥ ፲፩ ።

፳፱) ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሀት ፡ ተገዙ፤
በረዓድም ፡ ድስ ፡ ይበላችኹ ።
ተግሣጹን ፡ ተቀበሉ፥ ጌታ ፡ እንዳይቈጣ፤
መዝ. ፡ ፪፥ ፲፩ ።

፴) እግዚአብሔርሰ ፡ ሰማያተ ፡ ገብረ ።
አሚን ፡ ወሠናይት ፡ ቅድሜሁ ።
ቅድሳት ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ውስተ ፡ መቅደሱ ።
መዝ. ፡ ፺፭(፺፮)፥ ፮ ።

፴) እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰማያትን ፡ ሠራ ።
ምስጋናና ፡ ውበት ፡ በፊቱ፥
ቅዱስነትና ፡ ግርማ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ናቸውና ።
መዝ. ፡ ፺፭(፺፮)፥ ፮ ።

፴፩) እስመ ፡ ቅንአተ ፡ ቤትከ ፡ በልዐኒ ።
ትዕይርቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔየሩከ ፡ ወድቀ ፡ ላዕሌየ ።
ወቀጻዕክዋ ፡ በጾም ፡ ለነፍስየ ።
መዝ. ፡ ፷፰(፷፱)፥ ፱ ።

፴፩) የቤትኽ ፡ ቅንአት ፡ በልታኛለችና፥
የሚሰድቡኽም ፡ ስድብ ፡ በላዬ ፡ ወድቋልና ።
ነፍሴን ፡ በጾም ፡ አስመረርኋት፥
መዝ. ፡ ፷፰(፷፱)፥ ፱ ።

፴፪) እግዚአብሔር ፡ ይረድኦ ፡ ውስተ ፡ ዐራተ ፡ ሕማሙ ።
ወይመይጥ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ምስካቢሁ ፡ እምደዌሁ ።
አንሰ ፡ እቤ ፡— እግዚኦ ፡ ተሣሀለኒ ።
መዝ. ፡ ፵(፵፩)፥ ፫ ።

፴፪) እግዚአብሔር ፡ በደዌው ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ይረዳዋል፤
መኝታውን ፡ ኹሉ ፡ በበሽታው ፡ ጊዜ ፡ ያነጥፍለታል ።
እኔስ ፡— አቤቱ ፡ ማረኝ ፡ እላለኹ፤
መዝ. ፡ ፵(፵፩)፥ ፫ ።

፴፫) እግዚአብሔርሰ ፡ ገሃደ ፡ ይመጽእ ።
ወአምላክነሂ ፡ ኢያረምም ።
እሳት ፡ ይነድድ ፡ ቅድሜሁ ።
መዝ. ፡ ፵፱(፶)፥ ፪ ።

፴፫) እግዚአብሔር ፡ ግልጥ ፡ ኾኖ ፡ ይመጣል ።
አምላካችን ፡ ይመጣል፤ ዝምም ፡ አይልም ።
እሳት ፡ እፊቱ ፡ ይቃጠላል ።
መዝ. ፡ ፵፱(፶)፥ ፪ ።

፴፬) ከመ ፡ እንግር ፡ ፈቃደከ ፡ መከርኩ ፡ አምላኪየ ።
ወሕግከኒ ፡ በማእከለ ፡ ከርሥየ ።
ዜኖኩ ፡ ጽድቀከ ፡ በማኅበር ፡ ዐቢይ ።
መዝ. ፡ ፴፱(፵)፥ ፰ ።

፴፬) አምላኬ ፡ ሆይ፤ ፈቃድኽን ፡ ለማድረግ ፡ ወደድኹ፤
ሕግኽም ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
በታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ጽድቅን ፡ አወራኹ፤
መዝ. ፡ ፴፱(፵)፥ ፰ ።

፵፭) ሐወጽከኒ፡ ሌሊተ፤ ወፈተንኮ፡ ለልብየ።
አመከርከኒ፤ ወኢተረክበ፡ ዐመፃ፡ በላዕሌየ።
ከመ፡ ኢይንብብ፡ አፉየ፡ ግብረ፡ ዕጓለ፡
እመሕያው።
መዝ.፡ ፲፮(፲፯)፥ ፫።

፵፭) ልቤን፡ ፈተንኸው፤ በሌሊትም፡ ጐበኘኸኝ፤
ፈተንኸኝ፤ ምንም፡ አላገኘኽብኝም።
የሰውን፡ ሥራ፡ አፌ፡ እንዳይናገር፡ ፈቃዴ፡ ነው።
መዝ.፡ ፲፮(፲፯)፥ ፫።

፵፮) ንፍኁ፡ ቀርነ፡ በዕለተ፡ ሠርቅ።
በእምርት፡ ዕለት፡ በዓልነ።
እስመ፡ ሥርዐቱ፡ ለእስራኤል፡ ውእቱ።
መዝ.፡ ፹(፹፩)፥ ፫።

፵፮) በመባቻ፡ ቀን፥ በከፍተኛው፡ በዓላችን፡ ቀን፡
መለከትን፡ ንፉ፤
ለእስራኤል፡ ሥርዐቱ፡ ነውና፤
መዝ.፡ ፹(፹፩)፥ ፫።

፵፯) ቡሩክ፡ ዘይመጽእ፡ በስመ፡ እግዚአብሔር።
ባረክናክሙ፡ እምቤተ፡ እግዚአብሔር።
እግዚአብሔር፡ እግዚእ፡ አስተርአየ፡ ለነ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፮።

፵፯) በእግዚአብሔር፡ ስም፡ የሚመጣ፡ ቡሩክ፡
ነው። ከእግዚአብሔር፡ ቤት፡ መረቅናችኹ።
እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ነው፤ ለኛም፡ በራልን።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፮።

፵፰) ተፈሣሕኩ፡ እስመ፡ ይቤሉኒ፡ ቤተ፡
እግዚአብሔር፡ ነሐውር።
ወቆማ፡ እገሪነ፡ ውስተ፡ አዕጻድኪ፡ ኢየሩሳሌም።
ኢየሩሳሌምሰ፡ ሕንጽት፡ ከመ፡ ሀገር፡ እለ፡ ከማሃ፡
ወኅቡረ፡ ምስሌሃ።
መዝ.፡ ፻፳፩(፻፳፪)፥ ፩።

፵፰) ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ቤት፡ እንኺድ፡ ባሉኝ፡
ጊዜ፡ ደስ፡ አለኝ። ኢየሩሳሌም፡ ሆይ፤
እግሮቻችን፡ ባደባባይሽ፡ ቆሙ።
ኢየሩሳሌም፡ ርስ፡ በርሷ፡ እንደተገጠገጠች፡
ከተማ፡ ተሠርታለች።
መዝ.፡ ፻፳፩(፻፳፪)፥ ፩።

፵፱) ትሴብሖ፡ ኢየሩሳሌም፡ ለእግዚአብሔር።
ወሰብሒዮ፡ ለአምላክኪ፡ ጽዮን።
እስመ፡ አጽንዐ፡ መናሥግተ፡ ኆኃትኪ።
መዝ.፡ ፻፵፯(፻፵፰)፥ ፩።

፵፱) ኢየሩሳሌም፡ ሆይ፤ እግዚአብሔርን፡
አመስግኚ። ጽዮንም፡ ሆይ፤ ላምላክሽ፡ ዕልል፡
በዪ፤ የደጆችሽን፡ መወርወሪያ፡ አጽንቷልና።
መዝ.፡ ፻፵፯(፻፵፰)፥ ፩።

፶) ግበሩ፡ በዓለ፡ በትፍሥሕት፡ በኀበ፡ እለ፡
ያስተሐምምዎ።
እስከ፡ አቅርንቲሁ፡ ለምሥዋዕ።
አምላኪየ፡ አንተ፡ እገኒ፡ ለከ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፮–፳፯።

፶) ለርሱ፡ ከሚያስተነትኑት፡ በደስታ፡ በዓልን፡
አደረገ።
እስከ፡ መሠዊያው፡ ቀንዶች፡ ድረስ።
አንተ፡ አምላኬ፡ ነኽ፥ አመሰግንኻለኹ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፮–፳፯።

፶፩) ሀቡ፡ አኰቴተ፡ ለእግዚአብሔር።
ላዕለ፡ እስራኤል፡ ዐቢይ፡ ስብሐቲሁ።
ወኀይሉሂ፡ እስከ፡ ደመናት።
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፴፬።

፶፩) ለእግዚአብሔር፡ ክብርን፡ ስጡ።
ግርማው፡ በእስራኤል፡ ላይ፥
ኀይሉም፡ በደመናት፡ ላይ፡ ነው።
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፴፬።

፶፪) ዘምሩ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘየኀድር፡ ውስተ፡
ጽዮን፤ ወንግርዎሙ፡ ለአሕዛብ፡ ምግባሮ፤
እስመ፡ ተዘከረ፡ ዘይትኃሠሥ፡ ደሞሙ።
መዝ.፡ ፱፥ ፲፩።

፶፪) በጽዮን፡ ለሚኖር፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘምሩ፤
ባሕዛብም፡ መካከል፡ አደራረጉን፡ ንገሩ፤
ደማቸውን፡ የሚመራመር፡ ርሱ፡ ዐስቧልና።
መዝ.፡ ፱፥ ፲፩።

፶፫) እምአፈ፡ ደቂቅ፡ ወሕፃናት፡ አስተዳሎከ፡
ስብሐተ፡ በእንተ፡ ጸላኢ።
ከመ፡ ትንሥቶ፡ ለጸላኢ፡ ወለገፋዒ።
መዝ.፡ ፰፥ ፪።

፶፫) ከሕፃናትና፡ ከሚጠቡ፡ ልጆች፡ አፍ፡
ምስጋናን፡ አዘጋጀኽ፡ ስለ፡ ጠላትኽ።
ጠላትንና፡ ቂመኛን፡ ለማጥፋት።
መዝ.፡ ፰፥ ፪።

፵፬) እምሥራቀ፡ ፀሓይ፡ እስከነ፡ ዐረብ።
ወእምጽዮን፡ ሥነ፡ ስብሐቲሁ።
እግዚአብሔርሰ፡ ገሃደ፡ ይመጽእ።
መዝ.፡ ፵፱(፶)፥ ፩።

፵፬) ከፀሓይም፡ መውጫ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ መግቢያዋ፡ ድረስ፡ ምድርን፡ ጠራት።
ከክብሩ፡ ውበት፡ ከጽዮን፡ እግዚአብሔር፡ ግልጥ፡ ኾኖ፡ ይመጣል።
መዝ.፡ ፵፱(፶)፥ ፩።

፵፭) ንፍኁ፡ ቀርነ፡ በዕለተ፡ ሠርቅ።
በእምርት፡ ዕለት፡ በዓልነ።
እስመ፡ ሥርዐቱ፡ ለእስራኤል፡ ውእቱ።
መዝ.፡ ፹(፹፩)፥ ፫።

፵፭) በመባቻ፡ ቀን፥ በከፍተኛው፡ በዓላችን፡ ቀን፡ መለከትን፡ ንፉ፤ ለእስራኤል፡ ሥርዐቱ፡ ነውና፤
መዝ.፡ ፹(፹፩)፥ ፫።

፵፮) እምአፈ፡ ደቂቅ፡ ወሕፃናት፡ አስተዳሎከ፡
ስብሐተ፡ በእንተ፡ ጸላኢ።
ከመ፡ ትንሥቶ፡ ለጸላኢ፡ ወለገፋዒ።
መዝ.፡ ፰፥ ፪።

፵፮) ከሕፃናትና፡ ከሚጠቡ፡ ልጆች፡ አፍ፡
ምስጋናን፡ አዘጋጀኽ፡ ስለ፡ ጠላትኽ።
ጠላትንና፡ ቂመኛን፡ ለማጥፋት።
መዝ.፡ ፰፥ ፪።

ዘትንሣኤ፤

፵፯) አንሰ፡ ሰከብኩ፤ ወኖምኩ።
ወተንሣእኩ፡ እስመ፡ እግዚአብሔር፡ አንሥአኒ።
ኢይፈርህ፡ እምአእላፍ፡ አሕዛብ፡
መዝ.፡ ፫፥ ፭።

፵፯) እኔ፡ ተኛኹ፤ አንቀላፋኹም።
እግዚአብሔር፡ ደግፎኛልና፥ ነቃኹ።
ከሚከቡኝ፡ ከአእላፍ፡ ሕዝብ፡ አልፈራም።
መዝ.፡ ፫፥ ፭።

፵፰) ወተንሥአ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ዘንቃህ፡ አምንዋም።
ወከመ፡ ኃያል፡ ወኅዳገ፡ ወይን።
ወቀተለ፡ ፀሮ፡ በድኅሬሁ።
መዝ.፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፭።

፵፰) እግዚአብሔርም፡ ከንቅልፍ፡ እንደሚነቃ፡ ተነሣ፥
የወይን፡ ስካር፡ እንደ፡ ተወው፡ እንደ፡ ኀያልም፡ ሰው፤
ጠላቶቹን፡ በኋላቸው፡ መታ።
መዝ.፡ ፸፯(፸፰)፥ ፷፭።

፵፱) ዛቲ፡ ዕለት፡ እንተ፡ ገብረ፡ እግዚአብሔር።
ንትፈሣሕ፡ ወንትሐሠይ፡ ባቲ።
ኦ፡ እግዚኦ፡ አድኅንሶ።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፬።

፵፱) እግዚአብሔር፡ የሠራት፡ ቀን፡ ይህች፡ ናት፤
ሐሴትን፡ እናድርግ፥ በርሷም፡ ደስ፡ ይበለን።
አቤቱ፥ እባክኽ፥ አኹን፡ አድን።
መዝ.፡ ፻፲፯(፻፲፰)፥ ፳፬።

፶) ይትነሣእ፡ እግዚአብሔር፡ ወይዘረዉ፡ ፀሩ።
ወይጉየዩ፡ ጸላእቱ፡ እምቅድመ፡ ገጹ።
ከመ፡ የኀልቅ፡ ጢስ፡ ከማሁ፡ የኀልቁ።
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፩።

፶) እግዚአብሔር፡ ይነሣ፤ ጠላቶቹም፡ ይበተኑ፤
የሚጠሉትም፡ ከፊቱ፡ ይሸሹ።
ጢስ፡ እንደሚበን፡ እንዲሁ፡ ይብነኑ፤
መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፩።

፶፩) እምሥራቀ፡ ፀሓይ፡ እስከነ፡ ዐረብ።
ይትአኰት፡ ስሙ፡ ለእግዚአብሔር።
ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ መልዕልተ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ።
መዝ.፡ ፻፲፪(፻፲፫)፥ ፫።

፶፩) ከፀሓይም፡ መውጫ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ መግቢያዋ፡ ድረስ፡
የእግዚአብሔር፡ ስም፡ ይመስገን።
እግዚአብሔር፡ ባሕዛብ፡ ኹሉ፡ ላይ፡ ከፍተኛ፡ ነው።
መዝ.፡ ፻፲፪(፻፲፫)፥ ፫።

፶፪) ይእዜ፡ እትነሣእ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር።
እሬሲ፡ መድኀኒተ፡ ወአግህድ፡ ቦቱ።
ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል፡ ንጹሕ።
መዝ.፡ ፲፩(፲፪)፥ ፮።

፶፪) እግዚአብሔር፡ አኹን፡ እነሣለኹ፡ ይላል፤
መድኀኒትን፡ አደርጋለኹ፥ በላዩም፡ እገለጣለኹ።
በምድር፡ ላይ፡ እንደ፡ ተጣራ፡ ብር፡
የእግዚአብሔር፡ ቃላት፡ የነጹ፡ ቃላት፡ ናቸው።
መዝ.፡ ፲፩(፲፪)፥ ፮።

| | |
|---|---|
| ፶፫) አንሰ፡ ሰከብኩ፤ ወኖምኩ።<br>ወተንሣእኩ፡ እስመ፡ እግዚአብሔር፡ አንሥአኒ።<br>ኢይፈርህ፡ እምአእላፍ፡ አሕዛብ።<br>መዝ.፡ ፫፥ ፬። | ፶፫) እኔ፡ ተኛኹ፤ አንቀላፋኹም።<br>እግዚአብሔር፡ ደግፎኛልና፥ ነቃኹ።<br>ከሚከቡኝ፡ ካእላፍ፡ ሕዝብ፡ አልፈራም።<br>መዝ.፡ ፫፥ ፬። |
| ፶፬) በልዑ፡ ወጸግቡ፡ ጥቀ።<br>ወወሀቦሙ፡ ለፍትወቶሙ።<br>ወኢያኅጥኦሙ፡ እምዘፈቀዱ።<br>መዝ.፡ ፸፯(፸፰)፥ ፳፱። | ፶፬) በሉ፤ እጅግም፡ ጠገቡ፤<br>ምኞታቸውንም፡ ሰጣቸው።<br>ከወደዱትም፡ አላሳጣቸውም።<br>መዝ.፡ ፸፯(፸፰)፥ ፳፱። |
| ፶፭) እስመ፡ ሰበረ፡ ኆኀተ፡ ብርት።<br>ወቀጥቀጠ፡ መናሥግተ፡ ዘኀጺን።<br>ወተወክፎሙ፡ እምፍኖተ፡ ጌጋዮሙ።<br>መዝ.፡ ፻፮(፻፯)፥ ፲፮–፲፯። | ፶፭) የናሱን፡ ደጆች፡ ሰብሯልና፥<br>የብረቱንም፡ መወርወሪያ፡ ቈርጧልና።<br>ስለ፡ ዐመፃቸው፡ ሰነፉ፥ ስለ፡ ኀጢአታቸውም፡ ተቸገሩ።<br>መዝ.፡ ፻፮(፻፯)፥ ፲፮–፲፯። |
| ፶፮) ዐርገ፡ እግዚአብሔር፡ በይባቤ።<br>ወእግዚእነ፡ በቃለ፡ ቀርን።<br>ዘምሩ፡ ለአምላክነ፡ ዘምሩ።<br>መዝ.፡ ፵፮(፵፯)፥ ፭–፮። | ፶፮) አምላክ፡ በዕልልታ፥<br>እግዚአብሔር፡ በመለከት፡ ድምፅ፡ ዐረገ።<br>ዘምሩ፥ ላምላካችን፡ ዘምሩ።<br>መዝ.፡ ፵፮(፵፯)፥ ፭–፮። |
| ፶፰) ዐረገ፡ ውስተ፡ አርያም፡ ፄዊወከ፡ ፄዋ።<br>ወወሀብከ፡ ጸጋከ፡ ለዕጓለ፡ እመሕያው።<br>እስመ፡ ይክሕዱ፡ ከመ፡ ይኅድሩ።<br>መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፲፰። | ፶፰) ወደ፡ ላይ፡ ዐረግኽ፤ ምርኮን፡ ማረክ፤<br>ስጦታንም፡ ለሰዎች፡ ሰጠኽ፥<br>ደግሞም፡ ላመፀኞች፡ በዚያ፡ ያድሩ፡ ዘንድ።<br>መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፲፰። |

ዘዘመነ፡ ትንሣኤ፤

| | |
|---|---|
| ፶፱) ልበ፡ ንጹሐ፡ ፍጥር፡ ሊተ፡ እግዚኦ።<br>መንፈሰ፡ ርቱዐ፡ ሐድስ፡ ውስተ፡ ከርሥየ።<br>ኢትግድፈኒ፡ እምቅድመ፡ ገጽከ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲። | ፶፱) አቤቱ፡ ንጹሕ፡ ልብን፡ ፍጠርልኝ፤<br>የቀናውንም፡ መንፈስ፡ በውስጤ፡ ዐድስ።<br>ከፊትኽ፡ አትጣለኝ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲። |
| ፷) ኢትግድፈኒ፡ እምቅድመ፡ ገጽከ።<br>ወመንፈሰከ፡ ቅዱሰ፡ ኢታውፅእ፡ እምላዕሌየ።<br>ዕስየኒ፡ ፍሥሓ፡ ወአድኅኖተከ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፩። | ፷) ከፊትኽ፡ አትጣለኝ፤<br>ቅዱስ፡ መንፈስኽንም፡ ከኔ፡ ላይ፡ አትውሰድብኝ።<br>የማዳንኽን፡ ደስታ፡ ስጠኝ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፩። |
| ፷፩) ወበመንፈስ፡ ዐዚዝ፡ አጽንዐኒ፡<br>ከመ፡ እምሀሮሙ፡ ለኃጥኣን፡ ፍኖተከ።<br>ወረሲዓን፡ ይትመየጡ፡ ኀቤከ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፪። | ፷፩) በእሺታ፡ መንፈስም፡ ደግፈኝ።<br>ለሕግ፡ ተላላፎች፡ መንገድኽን፡ አስተምራለኹ።<br>ኀጢአተኞችም፡ ወዳንተ፡ ይመለሳሉ።<br>መዝ.፡ ፶(፶፩)፥ ፲፪። |

ዘአስተምሕሮ፤

| | |
|---|---|
| ፷፪) ሠረገላቲሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ምእልፊተ፡ አእላፍ፡ ፍሡሓን።<br>እግዚአብሔር፡ ውስቴቶን፡ በሲና፡ መቅደሱ።<br>ዐረገ፡ ውስተ፡ አርያም፡ ፄዊወከ፡ ፄዋ።<br>መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፲፯–፲፰። | ፷፪) የእግዚአብሔር፡ ሠረገላዎች፡ የብዙ፡ ብዙ፡ ሺሕ፡ ናቸው፤<br>ጌታ፡ በመቅደሱ፡ በሲና፡ በመካከላቸው፡ ነው።<br>ወደ፡ ላይ፡ ዐረግኽ፤ ምርኮን፡ ማረክኽ።<br>መዝ.፡ ፷፯(፷፰)፥ ፲፯–፲፰። |

| | |
|---|---|
| ፺፫) እስመ ፡ መምህረ ፡ ሕግ ፡ ይውህብ ፡ በረከተ ።<br>ወየሐውር ፡ እም ፡ ኀይል ፡ ውስተ ፡ ኀይል ።<br>ወያስተርኢ ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ በጽዮን ።<br>መዝ. ፡ ፹፫(፹፬)፥ ፮ ። | ፺፫) የሕግ ፡ መምህር ፡ በረከትን ፡ ይሰጣልና ።<br>ከኀይል ፡ ወደ ፡ ኀይል ፡ ይኼዳሉ ፤<br>ያማልክት ፡ አምላክ ፡ በጽዮን ፡ ይታያል ።<br>መዝ. ፡ ፹፫(፹፬)፥ ፮ ። |
| ፺፬) አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ መሓሪ ፡ ወመሰተሣህል ።<br>ርሑቀ ፡ መዓት ፡ ወብዙኀ ፡ ምሕረት ፡ ወጻድቅ ።<br>ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወተሣሀለኒ ።<br>መዝ. ፡ ፹፭(፹፮)፥ ፲፭ ። | ፺፬) አቤቱ፥ አንተ ፡ ግን ፡ መሐሪና ፡ ርኅሩኅ ፡<br>አምላክ ፡ ነኽ ፤<br>መዓትኽ ፡ የራቀ ፡ ምሕረትኽም ፡ እውነትኽም ፡<br>የበዛ ፤ ወደኔ ፡ ተመልከት፥ ማረኝም ።<br>መዝ. ፡ ፹፭(፹፮)፥ ፲፭ ። |
| ፺፭) አንተ ፡ ፈጠርከ ፡ ፀሓየ ፡ ወወርኀ ።<br>ወአንተ ፡ ገበርከ ፡ አድባረ ፡ ወምድሮ ፡ ኵሎ ፤<br>ክረምተ ፡ ወሐጋየ ፡ ዘአንተ ፡ ፈጠርከ ።<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፯ ። | ፺፭) አንተ ፡ ፀሓዩንና ፡ ጨረቃውን ፡ አዘጋጀኽ ።<br>አንተ ፡ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ሠራኽ ፤<br>በጋንም ፡ ክረምትንም ፡ አንተ ፡ አደረግኽ ።<br>መዝ. ፡ ፸፫(፸፬)፥ ፲፯ ። |

ዘክረምት ፤

| | |
|---|---|
| ፺፮) ዘይገለብቦ ፡ ለሰማይ ፡ በደመና ።<br>ወያስተዴሉ ፡ ክረምተ ፡ ለምድር ።<br>ዘያበቍል ፡ ሣዕረ ፡ ውስተ ፡ አድባር ።<br>መዝ. ፡ ፻፵፮(፻፵፯)፥ ፰ ። | ፺፮) ሰማዩን ፡ በደመናት ፡ ይሸፍናል ፤<br>ለምድርም ፡ ዝናምን ፡ ያዘጋጃል ፤<br>ሣርን ፡ በተራሮች ፡ ላይ ፡ ያበቅላል ፤<br>መዝ. ፡ ፻፵፮(፻፵፯)፥ ፰ ። |
| ፺፯) አርውዮ ፡ ለትለሚሃ ።<br>ወአስምሮ ፡ ለማእረራ ።<br>ወበነጠብጣብከ ፡ ትበቍል ፡ ተፈሢሓ ።<br>መዝ. ፡ ፷፬(፷፭)፥ ፲ ። | ፺፯) ትልሟን ፡ ታረካለኽ ፤<br>ቦይዋንም ፡ ታስተካክላለኽ ፤<br>በነጠብጣብ ፡ ታለሰልሳታለኽ ፤<br>መዝ. ፡ ፷፬(፷፭)፥ ፲ ። |
| ፺፰) አልቦ ፡ ነገር ፡ ወአልቦ ፡ነቢብ ፡ ዘኢተሰምዐ ፡<br>ቃሎሙ ።<br>ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወፅአ ፡ ነገሮሙ ።<br>ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ በጽሐ ፡ ነቢቦሙ ።<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፬ ። | ፺፰) ነገር ፡ የለም ፡ መናገርም ፡ የለም ፤<br>ድምፃቸውም ፡ አይሰማም ።<br>ድምፃቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ኹሉ፥<br>ቃላቸውም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ወጣ ።<br>መዝ. ፡ ፲፰(፲፱)፥ ፬ ። |
| ፺፱) ዘያበቍል ፡ ሣዕረ ፡ ለእንስሳ ።<br>ወሐመልማለ ፡ ለቅኔ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።<br>ከመ ፡ ያውፅእ ፡ እክለ ፡ እምድር ።<br>መዝ. ፡ ፻፫(፻፬)፥ ፲፬ ። | ፺፱) እንጀራን ፡ ከምድር ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ፥<br>ለምለሙን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ጥቅም፥<br>ሣርንም ፡ ለንስሳ ፡ ያበቅላል ።<br>መዝ. ፡ ፻፫(፻፬)፥ ፲፬ ። |
| ፻) ቃለ ፡ ወሀቡ ፡ ደመናት ፤ አሕጻከ ፡ ይወፅኡ ።<br>ቃለ ፡ ነጐድጓድከ ፡ በሠረገላት ።<br>አስተርአየ ፡ መባርቅቲሁ ፡ ለዓለም ።<br>መዝ. ፡ ፸፮(፸፯)፥ ፲፯ ። | ፻) ደመኖች ፡ ድምፅን ፡ ሰጡ፥ ፍላጾችኽም ፡<br>ወጡ ።<br>የነጐድጓድኽ ፡ ድምፅ ፡ በዐውሎ ፡ ነበር ፤<br>መብረቆች ፡ ለዓለም ፡ አበሩ ፤<br>መዝ. ፡ ፸፮(፸፯)፥ ፲፯ ። |

| | |
|---|---|
| ፳፩) ያዐርግ፡ ደመናተ፡ እምአጽናፈ፡ ምድር።<br>ወገብረ፡ መብረቀ፡ ለጊዜ፡ ዝናም።<br>ዘያወፅኦሙ፡ ለነፋሳት፡ እመዛግብቲሆሙ።<br>መዝ.፡ ፻፴፬(፻፴፭)፥ ፯። | ፳፩) ከምድር፡ ዳር፡ ደመናትን፡ ያወጣል፤<br>በዝናብ፡ ጊዜ፡ መብረቅን፡ አደረገ፤<br>ነፋሳትንም፡ ከመዛግብቱ፡ ያወጣል።<br>መዝ.፡ ፻፴፬(፻፴፭)፥ ፯። |
| ፳፪) ሐወጽካ፡ ለምድር፤ ወአርወይካ።<br>ወአብዛኅኮ፡ ለብዕላ።<br>ፈለገ፡ እግዚአብሔር፡ ምሉእ፡ ማያተ።<br>መዝ.፡ ፷፬(፷፭)፥ ፱። | ፳፪) ምድርን፡ ጐበኘኻት፥ አጠጣኻትም፤<br>ብልጥግናዋንም፡ እጅግ፡ አበዛኽ፤<br>የእግዚአብሔር፡ ወንዝ፡ ውሃን፡ የተመላ፡ ነው፤<br>መዝ.፡ ፷፬(፷፭)፥ ፱። |
| ፳፫) እምነ፡ ጽዮን፡ ይብል፡ ሰብእ።<br>ወብእሲ፡ ተወልደ፡ በውስቴታ።<br>ወውእቱ፡ ልዑል፡ ሣረራ።<br>መዝ.፡ ፹፮(፹፯)፥ ፭። | ፳፫) ሰው፡ እናታችን፡ ጽዮን፡ ይላል፤<br>በውስጧም፡ ሰው፡ ተወለደ፤<br>ርሱ፡ ራሱም፡ ልዑል፡ መሠረታት።<br>መዝ.፡ ፹፮(፹፯)፥ ፭። |
| ፳፬) ዘይውህብ፡ሲሳየ፡ ለኵሉ፡ ዘሥጋ።<br>እስመ፡ ለዓለም፡ ምሕረቱ።<br>ግነዩ፡ ለአምላከ፡ ሰማይ።<br>መዝ.፡ ፻፴፭(፻፴፮)፥ ፳፭–፳፮። | ፳፬) ለሥጋ፡ ኹሉ፡ ምግብን፡ የሚሰጥ፤<br>ምሕረቱ፡ ለዘላለም፡ ነውና።<br>የሰማይን፡ አምላክ፡ አመስግኑ።<br>መዝ.፡ ፻፴፭(፻፴፮)፥ ፳፭–፳፮። |
| ፳፭) ዐይነ፡ ኵሉ፡ ነፍስ፡ ይሴፎ፡ ኪያከ።<br>አንተ፡ ትውህቦሙ፡ ሲሳዮሙ፡ በጊዜሁ።<br>ትሰፍሕ፡ የማነከ፤ ወታጸግብ፡ ለኵሉ፡ እንስሳ፡<br>ዘበሥርዐትከ።<br>መዝ.፡ ፻፵፬(፻፵፭)፥ ፲፭–፲፮። | ፳፭) የኹሉ፡ ዐይን፡ አንተን፡ ተስፋ፡ ያደርጋል፤<br>አንተም፡ ምግባቸውን፡ በየጊዜው፡ ትሰጣቸዋለኽ።<br>አንተ፡ እጅኽን፡ ትከፍታለኽ፥ ሕይወት፡ ላለውም፡<br>ኹሉ፡ መልካምን፡ ታጠግባለኽ።<br>መዝ.፡ ፻፵፬(፻፵፭)፥ ፲፭–፲፮። |
| ፳፮) ወሐመልማለ፡ ለቅኔ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው።<br>ዘይውህቦሙ፡ ሲሳዮሙ፡ ለእንስሳ።<br>ወለዕጕለ፡ ቋዓት፡ እለ፡ ይጼውዕዎ።<br>መዝ.፡ ፻፵፮(፻፵፯)፥ ፰–፱። | ፳፮) ለምለሙንም፡ ለሰው፡ ልጆች፡ ጥቅም።<br>ለሚጠሩት፡ ለቍራዎች፡ ጫጩቶች፥<br>ለንስሶችም፡ ምግባቸውን፡ ይሰጣል።<br>መዝ.፡ ፻፵፮(፻፵፯)፥ ፰–፱። |
| ፳፯) እስመ፡ ኀቤከ፡ እጼሊ፡ እግዚኦ።<br>በጽባሕ፡ ስምዐኒ፡ ቃልየ።<br>በጽባሕ፡ እቀውም፡ ቅድሜከ፡ ወአስተርኢ፡ ለከ።<br>መዝ.፡ ፭፥ ፪–፫። | ፳፯) አቤቱ፥ ወዳንተ፡ እጸልያለኹና።<br>በማለዳ፡ ድምፅን፡ ትሰማለኽ፥<br>በማለዳ፡ በፊትኽ፡ እቆማለኹ፥ እጠብቃለኹም።<br>መዝ.፡ ፭፥ ፪–፫። |
| ፳፰) እግዚአብሔርሰ፡ ገሃደ፡ ይመጽእ።<br>ወአምላክነሂ፡ ኢያረምም።<br>እሳት፡ ይነድድ፡ ቅድሜሁ።<br>መዝ.፡ ፵፱(፶)፥ ፪። | ፳፰) እግዚአብሔር፡ ግልጥ፡ ኾኖ፡ ይመጣል።<br>አምላካችን፡ ይመጣል፥ ዝምም፡ አይልም፤<br>እሳት፡ በፊቱ፡ ይቃጠላል፥<br>መዝ.፡ ፵፱(፶)፥ ፪። |

ዘጸመ፡ ፍልሰታ፡ ለማርያም

| | |
|---|---|
| ፳፱) ወእነግር፡ ስምዐከ፡ በቅድመ፡ ነገሥት፤<br>ወኢይትኀፈር።<br>ወአነብብ፡ ትእዛዘከ፡ ዘአፍቀርኩ፡ ጥቀ።<br>ወአነሥእ፡ እደውየ፡ ኀበ፡ ትእዛዝከ፡ ዘአፍቀርኩ።<br>መዝ.፡ ፻፲፰(፻፲፱)፥ ፵፮–፵፰። | ፳፱) በነገሥታት፡ ፊት፡ ምስክርኽን፡ እናገራለኹ፥<br>አላርፍምም፤ እጅግም፡ በወደድኋቸው፥<br>በትዛዛትኽ፡ ደስ፡ ይለኛል።<br>እጆቼንም፡ ወደወደድኋቸው፡ ወደ፡ ትእዛዛትኽ፡<br>አነሣለኹ፤<br>መዝ.፡ ፻፲፰(፻፲፱)፥ ፵፮–፵፰። |

| | |
|---|---|
| ፹) ወይወስዱ ፡ ለንጉሥ ፡ ደናግለ ፡ ድኅሬሃ ።<br>ወቢጻሂ ፡ ይወስዱ ፡ ለከ ።<br>ወይወስድዎን ፡ በትፍሥሕት ፡ ወበሐሴት ።<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፬–፲፭ ። | ፹) በኋላዋ ፡ ደናግሉን ፡ ለንጉሥ ፡ የወስዳሉ ፥<br>ባልንጀሮቿንም ፡ ወዳንተ ፡ ያቀርባሉ ፤<br>በደስታና ፡ በሐሴት ፡ ይወስዷቸዋል ፥<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፬–፲፭ ። |
| ፹፩) ወይሰግዳ ፡ ሎቱ ፡ አዋልደ ፡ ጢሮስ ፡ በአምኃ ።<br>ወለገጽኪ ፡ ይትማሐለሉ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡<br>ብዑላነ ፡ ምድር ።<br>ኵሉ ፡ ክብራ ፡ ለወለተ ፡ ንጉሥ ፡ ሀሴቦን ።<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፪–፲፫ ። | ፹፩) የጢሮስ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡<br>ይዘው ፡ ይሰግዱለታል ።<br>የምድር ፡ ባለጠጎች ፡ አሕዛብ ፡ በፊትሽ ፡<br>ይማለላሉ ።<br>ለሀሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ክብሯ ፡ ነው ፤<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፪–፲፫ ። |
| ፹፪) እግዚኦ ፡ በኀይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሥ ።<br>ወብዙኀ ፡ ይትሐሠይ ፡ በአድኅኖትከ ።<br>ፍትወተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሀብኮ ።<br>መዝ. ፡ ፳(፳፩)፥ ፩–፪ ። | ፹፪) አቤቱ ፡ በኀይልኽ ፡ ንጉሥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤<br>በማዳንኽ ፡ እጅግ ፡ ሐሴትን ፡ ያደርጋል ።<br>የልቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠኸው ።<br>መዝ. ፡ ፳(፳፩)፥ ፩–፪ ። |
| ፹፫) ወትሠይመኒ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ሕዝብ ።<br>ሕዝብ ፡ ዘኢየአምር ፡ ተቀንየ ፡ ሊተ ።<br>ውስተ ፡ ምስማዐ ፡ ዕዝን ፡ ተሠጥዉኒ ።<br>መዝ. ፡ ፲፯(፲፰)፥ ፵፫–፵፬ ። | ፹፫) የአሕዛብም ፡ ራስ ፡ አድርገኽ ፡ ትሾመኛለኽ ፥<br>የማላውቀው ፡ ሕዝብም ፡ ይገዛልኛል ።<br>በጕሮ ፡ ሰምተው ፡ ተገዙልኝ ፤<br>መዝ. ፡ ፲፯(፲፰)፥ ፵፫–፵፬ ። |
| ፹፬) ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘአንተ ፡ ገሠጽኮ ፡ እግዚኦ ፡<br>ወዘመሀርኮ ፡ ሕገከ ።<br>ከመ ፡ ይትገሐሥ ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያት ።<br>መዝ. ፡ ፺፫(፺፬)፥ ፲፫ ። | ፹፬) ከክፉዎች ፡ ዘመናት ፡ ይወገድ ፡ ዘንድ ፥<br>አቤቱ ፥ አንተ ፡ የገሠጽኸው ፡ ሕግኽንም ፡<br>ያስተማርኸው ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።<br>መዝ. ፡ ፺፫(፺፬)፥ ፲፫ ። |
| ፹፭) ወድቀት ፡ እሳት ፤ ወኢርኢክዋ ፡ ለፀሓይ ።<br>ዘእንበለ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሦክክሙ ፡ ኀለተ ፡ ኮነ ።<br>ከመ ፡ ሕያዋን ፡ በመዓቱ ፡ ይውኅጠክሙ ።<br>መዝ. ፡ ፶፯(፶፰)፥ ፱–፲ ። | ፹፭) እሳት ፡ ወደቀች ፥ ፀሓይንም ፡ አላይዋትም ።<br>ሾኻችኹ ፡ ሳይታወቅ ፡ በትር ፡ ኾነ ፤<br>ሕያዋን ፡ ሳላችኹ ፥ በመዓቱ ፡ ይነጥቃች኿ል ።<br>መዝ. ፡ ፶፯(፶፰)፥ ፱–፲ ። |
| ፹፮) ወትቀውም ፡ ንግሥት ፡ በየማንከ ።<br>በአልባሰ ፡ ወርቅ ፡ ዑጽፍት ፡ ወሑብርት ።<br>ስምዒ ፡ ወለትየ ፥ ወርእዪ ፤ ወአጽምዒ ፡ እዝነኪ ።<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፱ ። | ፹፮) በወርቅ ፡ ልብስ ፡ ተጐናጽፋና ፡ ተሸፋፍና ፥<br>ንግሥቲቱ ፡ በቀኝኽ ፡ ትቆማለች ።<br>ልጄ ፡ ሆይ ፤ ስሚ ፥ እዩ ፤ ጕሮሽንም ፡ አዘንብዪ ።<br>መዝ. ፡ ፵፬(፵፭)፥ ፱ ። |

፹፯) ተዘከር፡ ማኅበረከ፡ ዘአቅደምከ፡ ፈጢረ ።
ወአድኅንከ፡ በትረ፡ ርስትከ ።
ደብረ፡ ጽዮን፡ ዘኀደርከ፡ ውስቴታ ።
መዝ.፡ ፸፫(፸፬)፥ ፪ ።

፹፯) አስቀድመኽ፡ የፈጠርኻትን፡ ማኅበርኽን፥
የተቤዠኻትንም፡ የርስትኽን፡ በትር፥
በርሷ፡ ያደርኽባትን፡ የጽዮንን፡ ተራራ፡ ዐስብ ።
መዝ.፡ ፸፫(፸፬)፥ ፪ ።

፹፰) ህየንተ፡ አበውኪ፡ ተወልዱ፡ ለኪ፡ ደቂቅ ።
ወትሠይሚዮሙ፡ መላእክተ፡ ለኵሉ፡ ምድር ።
ወይዘክሩ፡ ስመኪ፡ በኵሉ፡ ትውልደ፡ ትውልድ ።
መዝ.፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፮ ።

፹፰) ባባቶችሽ ፋንታ፡ ልጆች፡ ተወለዱልሽ፥
በምድርም፡ ኹሉ፡ ላይ፡ ገዥች፡ አድርገሽ፡
ትሾሚያቸዋለሽ ።
ለልጅ፡ ልጅ፡ ኹሉ፡ ስምሽን፡ ያሳስባሉ ።
መዝ.፡ ፵፬(፵፭)፥ ፲፮ ።

፹፱) እግዚኦ፡ ኵነኔከ፡ ሀቦ፡ ለንጉሥ ።
ወጽድቀከኒ፡ ለወልደ፡ ንጉሥ ።
ከመ፡ ይኰንኖሙ፡ ለሕዝብከ፡ በጽድቅ ።
መዝ.፡ ፸፩(፸፪)፥ ፩ ።

፹፱) አቤቱ፥ ፍርድኽን፡ ለንጉሥ፡ ስጥ ።
ጽድቅኽንም፡ ለንጉሥ፡ ልጅ፥
ሕዝብኽን፡ በጽድቅ፥ ችግረኞችኽንም፡ በፍርድ፡
ይዳኝ፡ ዘንድ ።
መዝ.፡ ፸፩(፸፪)፥ ፩ ።

፺) ታቦር፡ ወአርሞንኤም፡ በስመ፡ ዚኣከ፡
ይትፌሥሑ ።
ወይሴብሑ፡ ለስምከ ።
መዝራዕትከ፡ ምሰለ፡ ኀይል ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፲፪ ።

፺) ታቦርና፡ አርሞንኤም፡ በስምኽ፡ ደስ ይላቸዋል፤
ክንድኽ፡ ከኀይልኽ፡ ጋራ፡ ነው፤
እጅኽ፡ በረታች፥ ቀኝኽም፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ ።
መዝ.፡ ፹፰(፹፱)፥ ፲፪ ።

፺፩) ዘአዘዝከ፡ መድኀኒቶ፡ ለያዕቆብ ።
ብከ፡ ንወግኦሙ፡ ለኵሎሙ፡ ፀርነ ።
ወበስምከ፡ ናኀስሮሙ፡ ለእለ፡ ቆሙ፡ ላዕሌነ ።
መዝ.፡ ፵፫(፵፬)፥ ፬–፭ ።

፺፩) አምላኬና፡ ንጉሤ፡ አንተ፡ ነኽ፤
ለያዕቆብ፡ መድኀኒትን፡ እዘዝ ።
ባንተ፡ ጠላቶቻችንን፡ እንወጋቸዋለን፥
በስምኽም፡ በላያችን፡ የቆሙትን፡
እናዋርዳቸዋለን ።
መዝ.፡ ፵፫(፵፬)፥ ፬–፭ ።

፺፪) ውስተ፡ ኵሉ፡ ምድር፡ ወፅአ፡ ነገሮሙ ።
ወእስከ፡ አጽናፈ፡ ዓለም፡ በጽሐ፡ ነቢቦሙ ።
ወውስተ፡ ፀሓይ፡ ሤመ፡ ጽላሎቶ ።
መዝ.፡ ፲፰(፲፱)፥ ፬ ።

፺፪) ድምፃቸው፡ ወደ፡ ምድር፡ ኹሉ፥
ቃላቸውም፡ እስከ፡ ዓለም፡ ዳርቻ፡ ወጣ፤
በነርሱ፡ ውስጥ፡ የፀሓይን፡ ድንኳን፡ አደረገ፥
መዝ.፡ ፲፰(፲፱)፥ ፬ ።

፺፫) ቀደሰ፡ ማኅደሮ፡ ልዑል ።
እግዚአብሔር፡ ውስተ፡ ማእከላ፡ ኢትትሀወክ ።
ወይረድኣ፡ እግዚአብሔር፡ ፍጽመ ።
መዝ.፡ ፵፭(፵፮)፥ ፬ ።

፺፫) ልዑል፡ ማደሪያውን፡ ቀደሰ ።
እግዚአብሔር፡ በመካከሏ፡ ነው፤ አትናወጥም ።
እግዚአብሔርም፡ ፈጥኖ፡ ይረዳታል ።
መዝ.፡ ፵፭(፵፮)፥ ፬ ።

፺፬) ወተዝያነዉ፡ ዳኅናሃ፡ ለኢየሩሳሌም ።
ወፍሥሓሆሙ፡ ለእለ፡ ያፈቅሩ፡ ስመከ ።
ይኩን፡ ሰላም፡ በኀይልከ ።
መዝ.፡ ፻፳፩(፻፳፪)፥ ፮–፯ ።

፺፬) ለኢየሩሳሌም፡ ሰላምን፡ ለምኑ፤
አንተንም፡ ለሚወዱ፡ ልማት፡ ይኹን ።
በኀይልኽ፡ ሰላም፥ በጌጠኛ፡ ቤትኽም፡ ልማት፡
ይኹን ።
መዝ.፡ ፻፳፩(፻፳፪)፥ ፮–፯ ።

# ማውጫ ፤


| | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም ፤ | 1 |
| ተሰጥዎ ፤ | 4 |
| ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ | 4 |
| ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ | 24 |
| የሐዋርያት ፡ አመክንዮ ፤ | 26 |
| የሃይማኖት ፡ ጸሎት ፤ | 30 |
| የሐዋርያት ፡ ቅዳሴ ፤ | 34 |
| የጌታ ፡ ቅዳሴ ፡ ሰራዊት ፤ | 42 |
| የጌታ ፡ ቅዳሴ ፤ | 54 |
| የበዓላት ፡ ምስባኮች ፤ | 58 |
| የሰንበት ፡ ምስባኮች ፤ | 63 |
| ማውጫ ፤ | 74 |
| የበዓላትና ፡ የአጽዋማት ማውጫ ፤ | 75 |

## የአጽዋማትና ፡ የበዓላት ፡ ማውጫ ።

| ጾም ፤ በዓል | ፲፱፻፺፮ | ፲፱፻፺፯ | ፲፱፻፺፰ | ፲፱፻፺፱ | ፳፻ |
|---|---|---|---|---|---|
| ዐዲስ ፡ ዓመት | መስከረም ፡ ፩ | | | | |
| መስቀል | መስከረም ፡ ፲፯ | | | | |
| ሚካኤል | ኅዳር ፡ ፲፪ | | | | |
| የልደት ፡ ጾም | ኅዳር ፡ ፲፭ | | | | |
| ኅዳር ፡ ጽዮን | ኅዳር ፡ ፳፩ | | | | |
| በአታ ፡ ለማርያም | ታኅሣሥ ፡ ፫ | | | | |
| ገብርኤል | ታኅሣሥ ፡ ፲፱ | | | | |
| ተክለ ፡ ሃይማኖት | ታኅሣሥ ፡ ፳፬ | | | | |
| ዐማኑኤል | ታኅሣሥ ፡ ፳፰ | | | | |
| ልደት | ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ (ታኅሣሥ ፡ ፳፰ ፡ በዘመነ ፡ ዮሐንስ) | | | | |
| ግዝረት | ጥር ፡ ፮ | | | | |
| ሥላሴ | ጥር ፡ ፯ | | | | |
| ጾመ ፡ ገሃድ | ጥር ፡ ፲ | | | | |
| ጥምቀት | ጥር ፡ ፲፩ | | | | |
| ቃና ፡ ዘገሊላ | ጥር ፡ ፲፪ | | | | |
| አስተርእዮ ፡ ማርያም | ጥር ፡ ፳፩ | | | | |
| ኪዳነ ፡ ምሕረት | የካቲት ፡ ፲፮ | | | | |
| ጾመ ፡ ነነዌ | ጥር ፡ ፳፬ | የካ. ፡ ፲፬ | የካ. ፡ ፮ | ጥር ፡ ፳፩ | የካ. ፡ ፲ |
| የዐድዋ ፡ ድል | የካቲት ፡ ፳፫ | | | | |
| ዐቢይ ፡ ጾም | የካ. ፡ ፰ | የካ. ፡ ፳፰ | የካ. ፡ ፳ | የካ. ፡ ፭ | የካ. ፡ ፳፬ |
| ደብረ ፡ ዘይት | መጋ. ፡ ፭ | መጋ. ፡ ፳፭ | መጋ. ፡ ፲፯ | መጋ. ፡ ፪ | መጋ. ፡ ፳፩ |

# ተሰጥዎ ፡ ሥርዐተ ፡ ቅዳሴ ✠

| ጾም ፥ በዓል | ፲፱፻፺፮ | ፲፱፻፺፯ | ፲፱፻፺፰ | ፲፱፻፺፱ | ፳፻ |
|---|---|---|---|---|---|
| አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ | መጋቢት ፡ ፭ | | | | |
| መድኃኔ ፡ ዓለም | መጋቢት ፡ ፳፯ | | | | |
| ትስብእቱ | መጋቢት ፡ ፳፱ | | | | |
| ሆሳዕና | መጋ. ፡ ፳፮ | ሚያ. ፡ ፲፮ | ሚያ. ፡ ፰ | መጋ. ፡ ፳፫ | ሚያ. ፡ ፲፬ |
| ስቅለት | ሚያ. ፡ ፩ | ሚያ. ፡ ፳፩ | ሚያ. ፡ ፲፫ | መጋ. ፡ ፳፰ | ሚያ. ፡ ፲፯ |
| ትንሣኤ | ሚያ. ፡ ፫ | ሚያ. ፡ ፳፫ | ሚያ. ፡ ፲፭ | መጋ. ፡ ፴ | ሚያ. ፡ ፲፱ |
| ጊዮርጊስ | ሚያዝያ ፡ ፳፫ | | | | |
| ልደታ ፡ ለማርያም | ግንቦት ፡ ፩ | | | | |
| ረክበ ፡ ካህናት | ግን. ፡ ፳፯ | ግን. ፡ ፲፯ | ግን. ፡ ፱ | ሚያ. ፡ ፳፬ | ግን. ፡ ፲፫ |
| ዕርገት | ግን. ፡ ፲፪ | ሠኔ ፡ ፪ | ግን. ፡ ፳፬ | ግን. ፡ ፱ | ግን. ፡ ፳፰ |
| ጰራቅሊጦስ | ግን. ፡ ፳፪ | ሠኔ ፡ ፲፪ | ሠኔ ፡ ፬ | ግን. ፡ ፲፱ | ግን. ፡ ፰ |
| ሚካኤል | ሠኔ ፡ ፲፪ | | | | |
| ጾመ ፡ ሐዋርያት | ግን. ፡ ፳፫ | ሠኔ ፡ ፲፫ | ሠኔ ፡ ፭ | ግን. ፡ ፳ | ሠኔ ፡ ፱ |
| በዓለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ | ሐምሌ ፡ ፯ | | | | |
| ገብርኤል | ሐምሌ ፡ ፲፱ | | | | |
| ጾመ ፡ ፍልሰታ ፡ ለማርያም | ነሐሴ ፡ ፩ | | | | |
| ፅንሰታ | ነሐሴ ፡ ፯ | | | | |
| ደብረ ፡ ታቦር | ነሐሴ ፡ ፲፫ | | | | |
| በዓለ ፡ ፍልሰታ ፡ ለማርያም | ነሐሴ ፡ ፲፮ | | | | |